
# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር 4

ኅዳር 1988 ዓ.ም



የአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን

- ወርኀ ጽጌ
- ምሥጢረ ቁርባን
- የእግዚአብሔር ሕግ
- እሱ ራስህን ይቀጠቅጣል
- ስደተኞች — የመጨረሻ ክፍል
- የዘመን አቈጣጠር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
- ቅዱስ ድሜጥሮስ
- ደካማ ጎንን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?
- በጸጋው መዳን እንዴት ነው?
- ንዝህላልነት እና ቸልተኝነት— በክርስትና ሕይወት
- መላእክት በምድር ላይ
- መጽሐፍ ቅዱስ

ከአንባብያን ለአንባብያን

እና ሌሎችም

©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## አቡጊዳ የግዕዝ ቋንቋ መማሪያ

የግዕዝን ቋንቋ ባለማወቅ የተነሣ በንግግሮች፣ በመገናኛ ብዙኃን፣ ወዘተ. በቃላት ነጠላና ብዙ ቁጥር አጠቃቀም ላይ ስህተት ሲሠራ ይታያል። ከዚህ ስህተት ለመቆጠብ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን በመግቢያነት እንመልከት።

| ነጠላ ቃላት | ትክክለኛው የብዙ | የተሳሳተ የብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| ቁጥር | አጠቃቀም | አጠቃቀም |
| ክቡር | ክቡራን/ክቡራት | ክቡራኖች |
| መልአክ | መላእክት | መላእክቶች |
| ጳጳስ | ጳጳሳት | ጳጳሳቶች |
| አባል | አባላት | አባላቶች |
| መምህር | መምህራን | መምህራኖች |
| ልዑክ | ልዑካን | ልዑካኖች |
| መዘምር | መዘምራን | መዘምራኖች |
| ጻድቅ | ጻድቃን | ጻድቃኖች |
| — | ሥላሴ | ሥላሴዎች |
| ጾም | አጽዋም/አጽዋማት | አጽዋማቶች |
| ደብር | አድባር/አድባራት | አድባራቶች |
| ርእስ | አርእስት | አርእስቶች |

## ይድረስ ለፈጣሪ

ይድረስ ለፈጣሪ መንበረ ጸባዖት
ከትልቁ ሥፍራ ከሰማዩ መንግሥት
ፍርድ ሳይዛነፍ ከሚፈጸምበት።
ላኪው በምድር ላይ ግፍ የደረሰብኝ
ጉስቋላ አገልጋይህ ደካማው ባሪያህ ነኝ።
ሳጥናኤል የሚሉት የቀድሞ ጠላቴ
ቂሙን ሳይዘነጋ እንደ አዳም አባቴ
ከገነት ሊያስቀረኝ ቀጥቅጦ ጥሎኛል
ከመርዘኛው ባሕር በቁሜ ዘፍቆኛል
በአፍና አፍንጫዬ ደግሞም በጆሮቼ
መርዙ ተጠቅጥቆ በየብልቶቼ
አውጣኝ እያልኩህ ነው እባሕር ገብቼ።
ደካማ ነኝና ራሴን አልቻልኩም
ለመታገል ሞከርኩ ከእጁም አልወጣሁም
ፍርድ ሰጭው ዳኛ ችግሬን ቃኝተኸው
መፍትሔ እንድትሰጠኝ ወዳንተ እጮኻለሁ።

ዲያቆን ያሬድ ገ/መድኅን

ዘፍቼ

## ስምዐ ጽድቅ

### ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

እግዚአብሔር አምላክ የሠራቸውን ድንቅ ገቢረ ተአምራት፣ በዘመናችን ለተነሡ የኑፋቄ ትምህርቶች መልስ፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት ለሚገጥሙ ችግሮች መፍትሔ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በሰፊው የያዘች ጋዜጣ ናትና አታምልጥዎት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ላሉ አንባብያን ለማዳረስ ተዘጋጅተናል።

በቅርቡም 3ኛ ዓመት ቁ.1 ዕትማችን በገበያ ላይ ትውላለች በውስጧም

- የአውሬው መንፈስ ምሥጢር ሲገለጥ በሚል ከስህተት ስለተመለሰ አንድ ሰው ታሪክ ታስነብበናለች
- ኮከብ ቆጠራ በክርስትና ትምህርት እንዴት ይታያል?
- ለምእመናን ችግር መፍትሔ የምትስጥ ‹ምሥጢሬን ላካፍላችሁ› የምትል መንፈሳዊ ስንቅም ሰንቃለች። ብቅ ብለው ይጠይቁን

ስልክ 55-00-99 Ext 46

ፖስታ – 80078

| ለደንበኝነት | | |
|---|---|---|
| ለክፍለ ሀገር | የዓመት | 15.00 |
| | የ6 ወር | 7.50 |
| ለአዲስ አበባ | የዓመት | 14.40 |
| | የ6 ወር | 7.20 |
| ከሀገር ውጪ | የዓመት | 12 ዶላር |
| | የ6 ወር | 6 ዶላር |

አድራሻ ለወ/ት ዓይናለም ታዬ ደመቀ

4 ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ – የሂሳብ ቁጥር 79808

ፖ.ሣ.ቁ – 80078

## እርምት

### በቃል ያለ ይረሳል

በሰንበት ት/ቤት መርሐ ግብሮችና በሥርክ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዙ ሰው ማስታወሻ መያዝን እየዘነጋው መጥቷል። ይህ ደግሞ ከትምህርቱ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ የነገረ ሃይማኖት ዕውቀታችን እንዳይ ዳብር ከማድረጉም በላይ ነገ ከነገ ወዲያ ለልጆቻችን የምናስረክበው ትምህርት እንዳናጣ ያሰጋል። ‹በቃል ያለ ይረሳል...› ነውና። አባቶቻችን ስንክሳርን ያህል መጽሐፍ እንዳላስረከቡን ምነው አንዲት ማስታወሻ መያዙ ከበደን!!

ነፃነት ለገሠ

ደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤል

ሰ/ት/ቤት– ሮቢ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመር

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር 4

ኅዳር 1988 ዓ.ም


## ይዘት


ከአዘጋጁ ............. 1

የማኅበሩ መልእክት ....... 2

ደብዳቤዎች ............. 3

ከሰሞኑ በረከት

❖ ወርኀ ጽጌ ............ 5

ትምህርተ ሃይማኖት

❖ ምሥጢረ ቁርባን ......... 7

❖ የእግዚአብሔር ሕግ ....... 8

❖ እሱ ራስህን ይቀጠቅጣል .... 11

ኪነ–ጥበብ

❖ ስደተኞች ............ 13

እናስተዋውቃችሁ

❖ የዘመን አቈጣጠር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ............ 16

❖ ቅዱስ ድሜጥሮስ ......... 19

ዓምደ ወራዙት

❖ ደካማ ጎንን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል? .............. 20

❖ በጸጋው መዳን እንዴት ነው? . 21

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

❖ ጥያቄዎቻችሁ .......... 22

❖ ንዝህላልነት እና ቸልተኝነት– በክርስትና ሕይወት ....... 26

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

❖ መላእክት በምድር ላይ ...... 29

❖ መጽሐፍ ቅዱስ ......... 31

ከአንባብያን ለአንባብያን



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


# ከአዘጋጁ

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን*

*እንኳን ለዘመነ ዮሐንስ በሰላምና በጤና አደረሳችሁ።*

*የዘመናት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ያለፈውን ዘመን አሳልፎ ለአዲሱ ዘመን ስላደረሰን ምስጋና ልናቀርብለት ይገባል።*

*በዘመናት ዑደት ትውልድ ሲያልፍ ትውልድ ሲተካ ሣሩ ሲጠወልግ አበቦችም ሲረግፉ ከጥንት ምድርን በውኃ ላይ ያጸና ሰማያትን ያለባላ ያቆመ ኤልሻዳይ የእጆቹ ሥራ ሲለዋወጡ እንደ ልብስ ሲያረጁ እንደ መጐናጸፊያም ሲጠቀልላቸው እርሱ ግን በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው ከክብሩ ሳይናወጽ ከባሕርዩ ሳይለወጥ በአምላክነቱ ጸንቶ ለዘለዓለም ይኖራል። ዘመኑ ከቶ አያልቅምና።*

*"ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል" 2ጴጥ.1, 24። ሳያረጅ ሳይለወጥ የሰዎችን አእምሮ እያደሰና ተስፋ ሕይወትን እያበሠረ ይኖራል።*

*መጽሔታችን ሐመርም ባለማለፍ ጸንቶ የሚኖረውን መንግሥተ እግዚአብሔርን እንወርስ ዘንድ ቃለ እግዚአብሔርን በመመገብ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ነች። በዚህ ዓመት የመጽሔታችን ጥራትና ውበት ካለፈው የበለጠ ያማረና የተዋበ እንዲሆን የሁላችን ተሳትፎ ወሳኝነት ስላለው እንዳለፈው ሁሉ ተሳትፎችሁ አይለየን። ሊታረምና ሊስተካከል የሚገባውን ሁሉ ጠቁሙን። መጽሔትዋ የሁላችንም የሥራ ውጤት ናትና።*

*በሚቀጥለው ዕትም እግዚአብሔር በሰላም ያገናኘን።*


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

ስልክ 55 00 99 Ext 46

ፖስታ 80078

አዲስ አበባ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## የሚገባንን በሚገባ እንወጣ

በቤተክርስቲያን ሊቃውንት አተረጓጐም ቤተክርስቲያን የሚለው ስያሜ በዘይቤም በምሥጢርም ሦስት ዓይነት አወጣጥ አለው። የመጀመሪያው ፍቺ የተወሰነ ቦታን ያመለክታል። ይኸውም የክርስቲያኖች ቤት፣ የክርስቲያኖች መኖሪያ ማለት ነው። 1ቆር.11፥18፤ 1ቆር.14፥19፤ 1ቆር.14፥35። «ቤተክርስቲያን እንሂድ» እንዲሉ። በሁለተኛው አፈታት ክርስቲያኖችም ቤተክርስቲያን ይባላሉ። ይኸውም ደግሞ ዘርን፣ ጎሳን፣ ወገንን፣ ዜግነትን ያመለክታል። ቤተ–ያዕቆብ፥ ቤተ–እሥራኤል እንደ ማለት ነው። ከያዕቆብ የተወለደ ሁሉ ቤተ–እሥራኤል እንዲባል በመንፈስና በምሥጢር ልደት ከክርስቶስ የተወለደ ምእመናንም ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ። ቤተክርስቶስ እንደ ማለት ነው። የክርስቶስ ወገኖች የመንግስቱ ዜጎች ናቸውና። የሐዋ.5፥11፤ የሐዋ.9፥13። ሦስተኛውና የመጨረሻው ፍቺ የክርስቲያኖች አንድነት፣ የክርስቲያኖች ማኅበር ማለት ነው። ቤተክርስቲያን ዘግብጽ ቤተክርስቲያን፥ ዘኢትዮጵያ የሚል ንባብ ቢገኝ፣ በግብጽ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ማኅበር፣ በኢትትዮጵያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች መኀበር ማለት ይሆናል። ይህም በቅዱስ ጴጥሮስ አነጋገር ይታወቃል። «በባቢሎን የምትገኝ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ታቀርብላችኋለች» ብሏል። 1ጴጥ.5፥13።

ይህች ቤተክርስቲያን በአንድ በክርስቶስ ደም የተቀደሰች አንዲት ናት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትና ለሐዋርያትም ሆነ ለተከታዮቻቸው እንዲጠብቋት አደራ ሰጥቷቸዋል። የሐዋ.20፥28።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸ ውን እንዳይተውአት በማስጠንቀቅ ‹ኢንኅድግ ማኅበርነ– መሰብሰባችንን እንተው› በማለት መልእክቱን አስተላልፏል። ዕብ.10፥25። ምክንያቱም መልካምና መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት የሚቻለው በቤተክርስቲያን ላይ በመመሥረት ነውና። ዮሐ.15፥5።

በመሆኑም ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ምእመናን ከእውነተኛው የወይን ግንድ ከክርስቶስ ጉባዔ እንዳይለዩ በአጥቢያቸው ሰበካ ጉባዔያትን በማዋቀር በጉጀን ከተኩላዎች ትጠብቃለች። አስተዳደራዊ መዋቅሯ በሆነውና ምእመናንን ከቤተክርስቲያን በጠበቀ ሁኔታ በሚያገናኘው ድል ድይ፥ በሰበካ ጉባዔ፥ አማካይነት ምእመናን የሚገባቸውን በሚገባ እንዲወጡ ታደርጋለች። ዘወትር በምታቀርበው የቅዳሴ ጸሎትም «ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባዔ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር– በእግዚአብሔር ዘንድ ስለቀናችው ሐዋርያት ስለሰበሰቡአት አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰላም ጸልዩ» ትላለች።

ይሁን እንጂ እንደዚህ ቤተክርስቲያን ምእመናንን ለመሰብ ሰብ በምታደርገው ጥረት ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ችግሮች አሉ። የመጀመሪያው በየአጥቢያው የሚገኙ የሰበካ ጉባዔያት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና መመሪያ መሠረት አለመሥራት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አንድዳንድ ምእመናን የሰበካ ጉባዔ አባላት ሳይሆኑ በስም ብቻ ክርስቲያን ሆኖ መኖር የሚቻል ስለሚመስ ላቸው ከሰበካ ጉባዔ አባልነት ውጪ ሆኖ መገኘት ነው።

ቤተክርስቲያን የሰበካ ጉባዔያትን ያዋቀረችበት ዋንኛ ዓላማ ልጆቿ ቃለ እግዚአብሔርን እየተመገቡ ራሳቸውን ከኃጢያት ጠብቀው እነርሱም የሚፈለግባቸውን አውቀው፣ ‹የቤተክርስ ቲያን ጉዳይ የመዳን ጉዳይ ነው› ብለው እንዲኖሩ ነው። ስለዚህም በሰበካ ጉባዔያት አማካይነት ምእመናን እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከካህናት ጋር በጠበቀ ሁኔታ በመገናኘት የቤተክርስቲያንን አስተዳደራዊ ጉዳይ ያከናውናሉ፤ ለቤተክርስቲያን ዕድገት እንዲሁም ለራሳቸው ድኅነት የሚፈለግባቸውን ይወጣሉ። ነገር ግን አንዳንድ በየአጥቢያቸው ያሉ የሰበካ ጉባዔያት ይህንን ካለማወቅ መሥራት የሚገባቸውን ትተው የማያስፈልጉ ነገሮችን ይሠራሉ። በአንዳንድ አጥቢያዎችም ተመርጠው ቃለ ዓዋዲው ከሚፈቅደው ውጪ ከአሥር ዓመት በላይ በመሥራታቸው፣ የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት መሆኑን ዘንግተው እንደየግል መተዳደሪያቸውና የገቢ ማግኛቸው በመቁጠር የቤተክርስቲያንን ገንዘብ ሲያባክኑና ፈላጭ ቆራጭ ሲሆኑም ይታያል። ከዚህም የተነሣ ለትምህርተ ወንጌል እንቅፋት በመሆን፣ የሰንበት ትምህ ርት ቤትንና የልማት እንቅስቃሴን በማዳከም ወዘተ. ለቤተክርስቲያን መሠራት የሚገባው ሥራ እንዳይሠራ ያደርጋሉ። ለዚህም ዋንኛው ምክንያት የሚመረጡት ሰዎች በቃለ እግዚአብ ሔር አለመታነጽ፣ ክርስቲያናዊ ሥነ–ምግባር አለመኖርና በመንፈሳዊ ህይወት አለመብሰል ነው።

ከዚህም ሌላ ለአንድ ምእመን ቤተክርስቲያን ሕይወቱና የዘላለም ቤቱ ናት። በሰበካ ጉባዔያትም በመታቀፍ የሚፈለግበትን አስተዋጽዖ ያደርጋል፣ አሥራት ያወጣል፣ ዕለት ተዕለት የቤተክርስቲያንን ጉዳይ ይከታተላል፤ እርሱም የሚፈልገውን ያገኛል። ስለሆነም ‹ክርስቲያን ነኝ› የሚል ማንኛውንም ሰው ቤተክርስቲያን ልጁ መሆኑን ልታውቅ ይገባል። ዛሬ እየታየ የመጣው ግን ከዚህ ይለያል። አንዳንድ ምእመናን ወደ ቤተክር ስቲያን የሚመጡት ጉዳይ ሲኖራቸው ብቻ ነች። በጋብቻ ወቅት ለተክሊል፣ ልጅ ሲወልዱ ለክርስትና ከዚያም ሲሞቱ ለመቀበር። እንደዚህ ለችግሩ ብቻ ብቅ እያለ የሚጠፋን ሰው አውቃ ለማስተናገድ ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ ትቸገራለች። ከሃገራችን ህዝብ አብዛኛው የቤተክርስቲያን ልጅ ሲሆን ችግሩ ግን ‹እምነት በልብ ነው› እያለ በቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር በመታቀፍ በምግባር ስለማይገልጸው ክርስቲያንነቱን እርሱ እንጂ ቤተክርስቲያን አለማወቋ ነው። ምክንያቱም በእርሷ አማካይነት ከእግዚአብሔር በመንፈስና በምሥጢራዊ ልደት ከተወለደ በኋላ ዞር ብሎ አያያትም፤ አይጠይቃትም።

ስለዚህ ክርስቲያን ነን የምንል ሁሉ በየአጥቢያው ቤተክር ስቲያን ሰበካ ጉባዔና ሰንበት ት/ቤት ተሳታፊ በመሆን በመንፈሳዊ ሕይወታችን የበረታንና ቤተክርስቲያንም ከእኛ የምትፈልገውን አውቀን ልናበረክትና ለዘላለማዊ ድኅነታችን የሚያስፈልገንን ልናገኝ ይገባል። እንዲሁም በሰበካ ጉባዔያት ከታቀፍን በኋላም ቢሆን የተወሰነ ጊዜ ብቻ እየተገኘን ለሥራው የሚያስፈልጉትን ሰዎች መርጠን መሄድ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው እየተገኘን ልክ እንደ ቤታችን የተመረጡት ሰዎች ሥራቸውን በቃለ ዓዋዲው መሠረት ማከናወናቸውን መከታተልና መርዳት ይጠበቅብናል። እንደዚያ ከሆነ የሚገባንን በሚገባ ተወጥተናል፤ ከእግዚአብሔርም የሚገባንን እናገኛለን። 2ጢሞ.4፥7። ለሁሉም የድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን ረድኤት፣ አይለየን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ አሸጋገራችሁ

በምታቀርቧቸው ዓምዶች ተደስቻለሁ። በተለይ የእናስተዋውቃችሁን ዓምድ በጣም እወደዋለሁ። እኔም ብጠቁማችሁ ለሌሎች ታሳውቁበታላችሁና የምትችሉ ከሆነ በደቡብ ጐንደር በነፋስ መውጫ አካባቢ ብዙ ቅዱሳት ገዳማት አሉና ወደዚሁ ብቅ ብላችሁ ብታስተዋውቋቸው ጥሩ ነው። ለምሳሌ፥ የታወቀውን የድጓ መመረቂያ ቤተልሔምን፤ የዝማሬ መመረቂያውን ዙርአምባን፤ ሰጥላ ማርያምን ወዘተ.

ከንፈማርያም ኃይለ ጊዮርጊስ

ነፋስ መውጫ

ከአዘጋጁ

የላኩልን የእንኳን አደረሳችሁ የእንቁጣጣሽ አበባም ደርሶናል። እግዚአብሔር ይስጥልን እናመሰግናለን። በተረፈ አስተያየትዎንና ጥቆማዎን ተቀብለናል። ሁሉንም ቅዱሳት መካናት በአንድ ጊዜ ማዳረስ ስለማንችል ወደፊት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚሆን እናደርጋለን።

✣ ✣ ✣

ይድረስ ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች

በሐመር መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁ.2/87 «ኦርቶዶክሳዊ መዝሙርና መዘምራን» በሚለው ርዕስ ሥር መዝሙርን በተመለከተ ጠቃሚ ጽሑፍ ቀርቧል። የተጠቀሰውን የግጥም ቃላትና የዜማ ችግር ለማስቀረት ሳንሱር የሚያደርግና የሚቀርቡት መዝሙሮች ሳይታዩ እንዳይታተሙ የሚያደርግ፣ ፈቃድ የሚሰጥ ማዕከል ቢቋቋም ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ሊያስቀረው ይችላልና ይታሰብበት።

ዋስይሁን በቀለ — አዲስ አበባ

ከአዘጋጁ

ዳኛቸው ደብሮም እና እንደሻው በሮጀ (ሁለቱም ከአዲስ አበባ) የሰጣችሁን አስተያየት ከዚሁ ጋር ይመሳሰላል። አስተያየታችሁ ትክክለኛና እውነተኛ የቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ ሁሉ ሊሰማው የሚገባው ነው። ዋናው ችግር ግን ተከታትሎ ሳንሱር የሚያደርግ ክፍል አለመኖር ብቻ ሳይሆን የሚዘምሩት ሰዎች ራሳቸውን ለሳንሱር ያለማዘጋጀት ጉዳይ ነው። ስለዚህ ከየአቅጣጫው ያልታረሙ መዝሙሮች ሊወጡ ይችላሉ። በመሆኑም በእነዚህ ሳይታረሙ በሚወጡትና ስህተት ባለባቸው መዝሙሮች የሚጎዳው ትውልዱ ነውና የሚመለከተው ክፍል ያስብበት እንላለን።

✣ ✣ ✣

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች

የእግዚአብሔር ሰላም ይብዛላችሁ እያልኩ አንድ በአካባቢዬ የተፈጸመና ግራ የገባኝን ድርጊት መልስ እንድትሰጡኝ እጠይቃለሁ። ይኸውም በአንድ የገጠር ቀበሌ ገበሬው መሬቱን አለስልሶ ዘር ቢዘራም ዝናብ ባለመዝነቡ በቤተክርስቲያን አባቶች አሳሳቢነት ነዋሪዎቹ ገንዘብ አዋጥተው አንድ በሬ ገዝተው ከቤተክርስቲያኑ ቅጥር ውጭ ታርዶ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ተደረገ። እኔና አንድ ወንድሜ የበሬውን መታረድ አላስፈላጊነት አባቶችን ጠይቀናቸው «ደም በማፍሰስ ወደ እግዚአብሔር ጩኸን ዝናብ እንዲሰጠን እንለምናለን። ከዚህ ቀደምም ስናደርገው የቆየን ልማዳችን ነው» የሚል መልስ ሰጡን። እኛም በአንድ በኩል ስናስበው ባዕድ አምልኮ መሰለን። ግን ደግሞ የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩ ወደ እግዚአብሔር ነው የጮሁት ብለንም አሰብን፤ በዚህ ላይ በሬው ታርዶ ሥጋውን ተከፋፍለው ወደ ቤታቸው ነው የወሰዱት። እናም መሥዋዕቱ አስፈላጊ ነውን? አባቶቻችንስ ይህንን ማድረጋቸው ቤተ ክርስቲያናዊ መሠረትነት አለው? እባካችሁ ግራ ገብቶናልና መልሱን አንድ በሉን።

መልኩ ተዘራ— ቆላድባ

ከአዘጋጁ

ደም አፍስሶ መሥዋዕት ማቅረብ የኦሪት የመሥዋዕት ሥርዓት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን አንድ ጊዜ ስለዓለም ራሱን በመስቀል ላይ ቤዛ አድርጎ የሰጠን መሥዋዕታችን የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው። ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ስም ቢጠራበት የእንስሳትን ደም በአሁኑ ዘመን ለአምልኮት ማፍሰስ ከባዕድ አምልኮነት አያልፍም። እንዲያውም የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መሥዋዕት አድርገው (ቀድሰው)፤ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ ብለው ወደ ፈጣሪያቸው መጮህ ሲገባ፤ በዚህ እግዚአብሔር አይሰማንም ብሎ ሌላ መሥዋዕት ፍለጋ መሄድ የከፋ ኃጢአት ነው። ስለዚህ እናንተም እንደ ጀመራችሁት በእርጋታ የአካባቢውን ሰዎች ምከሯቸው፤ አስተምሯቸው። ካህናቱም እንዲህ ዓይነቱን ሥራ መሥራት ትተው ለሕዝቡም ትክክለኛውን ቃል እንዲያስተምሯቸው ያስፈልጋል። ማቴ.24፥20።

✣ ✣ ✣

ውድ የሐመር አዘጋጆች

ቸርነቱ የማያልቅበት ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁንና የምታዘጋጇት ምግበ ነፍስ ከደጋው እስከ ቆላው ዘልቃ ከእጃችን ትገባለች። በተለይም በእኛ አካባቢ ያለው ሕዝብ በተለያየ አምልኮ ጣዖት የተዋጠ ራሳቸውን ከስለትና ከእሳት ማዳን በማይቻላቸው የሥነ ፍጥረት ወገኖች የሚያመልክ በመሆኑ ለእንቅስቃሴአችን ችግር ቢፈጥርብንም ሐመርን በመያዝ እየተቋቋምን እንገኛለን። በመሆኑም መርከቢቷ ጉዞዋ እንዳይቋረጥ ባላችሁበት ጠንክራችሁ ፈተናውን ተቋቁማችሁ በሥራችሁ ግፉበት። አዲሱም ዓመት የሥራና የትጋት ዘመን ይሁንላችሁ።

ዘውዱ አላምረው -- ከምሥራቅ ጎጃም

(የዕድ ውኃ ኪዳነ ምሕረት ሰ/ት/ቤት)

ከአዘጋጁ

ስለአስተያየትዎና መልካም ምኞትዎ እግዚአብሔር ይስጥልን። በጸሎትዎ ያስቡን፤ በተሳትፎዎም አይለዩን።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች በሙሉ

እአስከ ዛሬ አንባቢ እንጂ በጽሑፍ ተሳታፊ አልነበርኩም። በዚህች የመጀመሪያዬ በሆነችው ደብዳቤዬ አንድ ጥያቄ እንድታብራሩልኝ እፈልጋለሁ። ይኸውም በአካባቢያችን የሚገኙ አንዳንድ ሰዎች በተጣሉና አበድረው በተከለከሉ ቁጥር መርፌ ወስደው በቤተክርስቲያን ግድግዳ ላይ ይተክሉና ይራገማሉ። ስለዚህ መርፌ መትከል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው ማለት ነው? ወይስ ባዕድ አምልኮ ነው?

ከበደ ጉርሙ

(ቦንጋ—ኪዳነ ምሕረት ሰ/ት/ቤት)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከአዘጋጁ

እርስዎ ያስተዋሉት በትክክል ብዙ ሰዎች ካለማወቅ የተነሣ እየፈጸሙት ያለ ነገር ነው። ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም። እንደዚህ ዓይነቱን ክፉ ምኞትና ከንቱ አምልኮ ልንቋቋመውና ልናስወግደው የሚገባን ሁላችንም በየአካባቢያችንና በምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስናስተምር ብቻ ነው።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል

እንኳን ለ1988 ዓ.ም አደረሳችሁ። ዘመኑ የሥራ የፍቅርና የመልካም ፍሬ ማፍርያ ዘመን ይሁንላችሁ። እያልኩ መጽሔታችሁ ለሕትመት ደርሳ ለንባብ ከበቃችበት ጊዜ አንሥቶ እየተከታተልኩ ሲሆን ለ3ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትማችሁ ስለጋብቻ ሥርዓት በዳሰሳችሁበት ጽሑፍ «ክርስቲያናዊ ጋብቻ ዘላለማዊ ነው» የሚለው አባባል አልገባኝም። ማለትም ከሞቱ በኋላ በአፀደ ነፍስም አብረው ይኖራሉ (ይገናኛሉ) ማለት ነው? አብራሩልኝ። በተረፈ ስደተኞችን በእንጥልጥል አታስቀሩብን። መጨረሻቸውን አሳውቁን። በዚህ አጋጣሚ አዘጋጁን በጣም አመስግኑልኝ።

መቅደስ ከበደ – ፍቼ

ከአዘጋጁ

አሜን። ‹ክርስቲያናዊ ጋብቻ ዘላለማዊ ነው› ማለት፤ ዛሬ ተገንብቶ ነገ የሚፈርስ የኮንትራት ኑሮ ወይም ጨዋታ አይደለም። ሁለቱም እስከ ዕለተ ሞታቸው አብረው ይኖራሉ፤ ማለት እንጂ በአፀደ ነፍስም ትዳር አለ ለማለት ተፈልጎ አይደለም። በአፀደ ነፍስና በትንሣኤ ማግባት መጋባት የለምና። ማቴ.22፥23–32። ለስደተኞች አዘጋጅ መልእክቱን አድርሰናል። የስደተኞቹም መጨረሻ በዚህ እትም ይታያልና ያንብቡት።

✦ ✦ ✦

ይድረስ ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል

አዲስ አበባ

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ሐመር መጽሔት መዘጋጀት ከጀመረች ጊዜ ጀምሮ ጽሑፎችን ከመጻፍ ተቆጥቤ አላውቅም እናንተ ግን ውጦ ዝም ሆናችሁ። እና ይህ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ከእንግዲህ ወዲህ ግን መጻፌን ላቆም ነውና እርምጃ ከመውሰዴ በፊት ቢያንስ የቴምብሩንና የኤሮግራሙን ዋጋ እንኳን አስባችሁ መልእክቴን በመጽሔታችሁ አውጡልኝ። የዘወትር ተሳታፊያችሁ።

ሙላት መኮንን

(ኮረም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት)

ከአዘጋጁ

ወንድማችን በጣም በመማረርዎ እናዝናለን። አስቀይመንዎትም ከሆነ ይቅርታ እንጠይቃለን። ነገር ግን ማንኛውም ጽሑፍ ሊወጣና ለንባብ ሊበቃ የሚችለው ለአንባቢያን ከሚያስተላልፈው መልእክት አንፃር እንጂ በሚወጣው ገንዘብ መጠን አይደለም። እንዲህ ዓይነት አስተያየት ያላቸው ብዙ ሰዎች ናቸው። አሁንም እኛ የሚደርሱንን ጽሑፎች አወዳድረን የተሻለውን ለንባብ እናበቃለን። ይህንን ተገንዝበው የጻፍኩት ሁሉ የግድ መውጣት አለበት ሳይሉ ለአንባብያን ይጠቅማል የሚሉትን ሁሉ ቢጽፉልን ለማስተናገድ ዝግጁ ነን። በተረፈ በተሳትፎዎ አይለዩን።

✣ ✣ ✣

እንኳን ለ1988 ዓ.ም በሰላም አደረሳችሁ።

ምንም እንኳን ከዚህ በፊት ግንኙነታችን በአንድ አቅጣጫ ማለትም በእኔ አንባቢነትና በእናንተ መልእክት አስተላላፊነት ቢሆንም ከዚህች ተሳትፎዬ ጀምሮ ግን እኔም እየጻፍኩኝ በሁለቱም በኩል እንገናኛለን። ለዛሬ ግን በጥያቄ ብጀምር እንደማትቀየሙኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ይኸውም:-

ለብዙ ዓመታት በሰንበት ት/ቤታችን ሲያገለግሉ የነበሩ ወጣቶች ዕድሜአችሁ ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ ሆኗልና መስበክም ሆነ መዘመር አትችሉም ተብለው ተከልክለዋልና እባካችሁ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ከሆነ ብታስረዱኝ።

ታሪኩ ኃ/ሥላሴ

(ከሻኪሶ ቅ/ማ/ሰ/ት/ቤት)

ከአዘጋጁ

ቤተ ክርስቲያን በሥልጣነ ክህነት ለሚያገለግሉ እንጂ ለሌላው አገልግሎት የዕድሜ ገደብ አላወጣችም። በተሰጠው ጸጋ እንደሚችለው ያገለግላል። እናንተ አካባቢ ያለው ግን ካለማወቅ ከሆነ ታርሞ ወጣቶቹ እስከመጨረሻው ከቤተክርስቲያን እንዳይለዩ ቢደረግ መልካም ነው። በተረፈ ወጣቶቹ በእላትነት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ ጠባያቸው ተለውጦ የሚናገሩትና የሚኖሩት አልገናኝ ካለ ከሚሠሩት የሚያጠፉት ይበልጣልና ምግባራቸው እስኪስተካከልና እስኪረጋጉ ድረስ አባቶች ሊከለክሉዋቸው ስለሚችሉ በቅድሚያ የሰ/ት/ቤቱን ወጣቶች ሥነ ምግባር ማስተካከል ያስፈልጋል። በተጨማሪም የከለከሏቸው ሰዎች አትችሉም ብሎ ከማባረር መምከርና ባሕሪያቸው እንዲስተካከል ማድረግ ይመረጣል። ግንቦት 1986 በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ የወጣው የሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ደንብ በሰ/ት/ቤት ለሚያገለግሉ ወጣቶች የዕድሜ ጣራ አላወጣምና ብትመለከቱት የተሻለ ነው። በተረፈ በተሳትፎህ አትለየን።

✣ ✣ ✣

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው የመጽሔታችን አንባቢዎች የእንኳን አደረሳችሁ የመልካም ምኞት መግለጫ ካርዶቻችሁ አስተያየቶቻችሁ፣ ጽሑፎቻችሁና ጥያቄዎቻችሁ ደርሰውናል። አስተያየቶቻችሁን ተቀብለናል፤ ጥያቄዎቻችሁና ጽሑፎቻችሁ ደግሞ ወደፊት ወቅቱን እየጠበቁ ይስተናገዳሉና በትዕግሥት ጠብቁን። በተረፈ በእናንተ ተሳትፎ ከስህተታችን እንታረማለን፣ ከድካማችን እንበረታለን የመጽሔቷንም የሥርጭት አድማስ እናውቃለንና በተሳትፎአችሁ አትለዩን።

ገ/ሕይወት አየነ (ከጅጅጋ)፣ ተማሪ መሠለች መኩሪያ (አላባ ቁሊቶ)፣ ወጣት ገረመው ገብሬ (ቴፒ)፣ ደረጀ መኩንን (ደብረ ሲና)፣ ዲ. ጌትነት አስፋው (ጎንደር)፣ ዲ.ሀብታሙ አበበ (ዲላ–ወናጎ)፣ ታምሩ እሸቱ (ምዕራብ ሸዋ –ቆኬ)፣ ሰሎሞን ሚደቅሳ (ደብረ ዘይት)፣ ኃይለ ሚካኤል ንጋቱ (ቡሬ)፣ ተማሪ ደሳለኝ ተሰማ (ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ)፣ ዲ. አካለወልድ (ገርበ ጉራቻ)፣ ዲ.ዳንኤል ተወዳጅ (ጎፋ ሳውላ)፣ ጥላሁን መለሰ (መነሲቡ)፣ ማርታ ዓለሙ (ከአሰላ ደ.መ.ቅ/ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት)፣ ኢሳይያስ ንዳው (አ.አ)፣ መሠለች ጌትዬ (አርሲ ኮፈሌ)፣ አለኸኝ አጥናፉ (ኢ.አ)፣ መምህር መሠረት ታደሰ (ሚዛን)፣ ተማሪ ታደሰ ከተማ (ጉሐጽዮን)፣ ኤርምያስ ጌጡ (የካቲት ወረቀት ሥራ ድርጅት)፣ ገብረየስ ገቢቶ (ከፌቾ ዞን ንግድ መምሪያ ቦንጋ)፣ ወ/ሚካኤል ኃ/ማርያም (ጉሬ)፣ አስፋው ዓለሙ (ሰላምበር)፣ በኃይሉ ተረፈ (ሻሸመኔ)፣ ተማሪ ብዙነህ የኋላሸት (ድርጋዓለም)፣ ሺመልስ ከሠተ (አ.አ)፣ ስብሐት ገ/ሚካኤል (ኢሉባቦር–ያዩ)፣ ተማሪ ጥበቡ ሰሎሞን (ጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ)፣ ወለተ መስቀል ክብረት (ፍቼ)፣ አቶ መሠረት ጥሩዬ (አዋሳ)፣ ወጣት ማንደፍሮ አድማሱ (ሻኪሶ) ጌታቸው ወጋሕታ (አላማጣ)፣ ዓባይነህ ደመረ (ጎባ ወረዳ ግብርና መምሪያ)፣ ዓይናለም ወ/አማኑኤል (ደብረ ዘይት) ፣ ዘውዱ ገ/ፃድቅ (ከከፋቾ) ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ከሰሞኑ በረከት

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከመስከረም 26 ቀን እስከ ኅዳር 6 ቀን ያለው ጊዜ ወርኀ ጽጌ ይባላል። ይህ ወቅት ምድር በአበቦች ቀለምና መዓዛ የምታጌጥበት በመሆኑ «የአበባ ወር» ወርኀ ጽጌ ተብሏል።

አበባ የፍሬ እናት ነው። አበባን ያየ ሰው ሕይወቱ በተስፋ ትሞላለች፤ መልካሙ ፍሬ ከአበባው ይገኛልና። እመቤታችንም የተባረከ ፍሬ መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘች አማናዊቷ አበባ ናት። የአዳም ተስፋ መፈጸሙን የነቢያት ትንቢት መድረሱን ያበሰረችን የድኅነት ምልክት እርስዋ ናት። «ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል» እንዳለ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ። ኢሳ.7፥14።

የአበቦች መፍካት የጥጋብ ዘመን መምጣቱን ያበሥራል። ወርኀ ክረምት ዘር ገና በምድር ላይ የሆነበት ዘመን ስለሆነ ጐተራው ይሟጠጣል፤ መሶቡ ደንገጥ ይላል። የክረምቱ ጊዜ በጎመኑና በቅጠላ ቅጠሉ በጥራጥሬው ጭምር ይወጣል። ከአዲሱ ዘመን መባቻ ጀምሮ ግን «የጎመን ምንቸት ውጣ፤ የገንፎ ምንቸት ግባ» በሚለው ባሕላዊ አገላለፅ የአዲስ እህል ሽታ ይሰማል፤ የእሸት ጊዜ ይታያል። ይህ ጊዜ ምድር በሥነ ጽጌያት (በአበቦች ኀብር) አጊጣ፣ ሰማይ በከዋክብት አሸብርቆ የሚታይበት፣ የጠራ ውኃ ከወንዞችና ጅረቶች የሚፈስበት፣ ንጹሕ አየር የሚነፍስበት፣ አዕዋፍ ከተሰደዱበት እየተመለሱ የሚዘምሩበት፣ እንስሳትና አራዊት ለምለሙን ሣር እየነጩ ጥሩውን ውኃ እየተጎነጩ የሚፈነድቁበት ጊዜ ስለሆነ ለፍጥረት ደስ ይላል። መኃልይ 2፥11–13።

«የዘንድሮን ክረምት ወጣናት በመላ፣ አንድ ቀን ስናድር አንድ ቀን ስንበላ»

«እኛስ ይህችን ክረምት ወጣናት በመላ በኩርማን እንጀራ ጐመን ተጠቅልላ»

እንደሚባለው ክረምት ያለችውን አበቃቅቶ የሚከረምበት ጊዜ ነው። አበቦች በጋራው በሸንተረሩ ሲፈነዱ ማሳውና ጓሮው ሲያብብ ግን የጥጋቡ የእህሉ ወቅት መምጣቱን ይናገራሉ።

የድኅነት ምግብ፣ የጽድቅ ውኃ አጥቶ በሲኦል በረሃ በኃጢአት ረሃብ ለተንገላታው የአዳም ዘር ነፍስ በእግዚአብሔር ቸርነት በጌታችን ሥጋና ደም፣ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የምትጠግብበት ዘመን መድረሱን ያበሠረችው ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ዛሬም ቢሆን የተስፋ መቁረጥና የጭንቀት፣ የደዌ ሥጋ እና የደዌ ነፍስ ረሃብ ለወደቀባቸው እመቤታችን የመዳን ተስፋቸው ናት።

በዚህም የተነሣ ቅዱሳን አበው እመቤታችንን በአበባ መስለው ምሥጢር ከምሳሌ በማስተባበር ስደቷን

## ወርኀ ጽጌ

በወርኀ ጽጌ ያስቡታል።

ይህ የእመቤታችን የስደቷ መታሰቢያ ወር በቤተ ክርስቲያናችን የሚከበረው በሚከተለው ሁኔታ ነው።

1. በማኅሌት
2. በቅዳሴ
3. በዝክር

### ማኅሌተ ጽጌ

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት

በአምላካችን ቤት በአደባባዮች የምትቆሙ እናንተ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁላችሁ በሌሊት በቤተ መቅደስ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ እግዚአብሔርንም ባርኩ። መዝ.133፥ 1 እና 2።

በማለት እንደተናገረው አባቶቻችን ከቅዳሜ ማታ እስከ እሑድ ጠዋት እንዲሁም በክብረ በዓላት እጆቻቸውን ለሽብሸባና ለጭብጨባ እንሥተው በከበሮና በጽናጽል እየወረቡ በመቋሚያ እየዘመሙ ያለ ድካምና መሰልቸት ሲዘምሩ ያድራሉ። ምእመናንም ዕንቅልፍ ሳያታልላቸው ድካም ሳይበግራቸው ከአባቶቻቸው ጋር በቤተ ክርስቲያን በመገኘት በዕልልታ፣ በዝማሬ እያጀቡ ያድራሉ።

በዚህ ወቅት የሚቀርበው ዝማሬ ሦስት ወገን ነው።

### 1. ከቅዱስ ያሬድ ድጓ

ቤተ ክርስቲያናችንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሳወቁአት ሊቃውንት ቤተክርስቲያን መካከል አንዱና ዋነኛው ቅዱስ ያሬድ ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከአርያም የተገኘ በመሆኑ ጊዜ የማይሽረው የማይለውጠው ታላቁ የቅድስት ቤተክርስቲያን አንጡራ ሀብት ነው።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ዓመቱን ክረምት፣ መጸው፣ ሐጋይ፣ ፀደይ ብሎ በመከፋፈል በየዘመኑ የሚዘመረውን መዝሙር አዘጋጅቷል። በወርኀ ጽጌም ቅዱስ ያሬድ የምድሪቱን በአበባ መሸለም፣ በቡቃያ ማማር፣ የክረምቱን የጭቃ፣ የድጥ ወቅት ማለፍ በተመለከተ እግዚአብሔርን ካመሰገነበት ድርሰቱ እየተውጣጣ ይዘመራል። በተለይ በወርኀ ጽጌ።

### 2. ማኅሌተ ጽጌ

ይህ መዝሙር የእመቤታችንን ታሪክ ከጽንሰቷ እስከ ልደቷ፣ ክብርዋን፣ ንጽሕናዋን፣ በሄሮድስ ምክንያት የደረሰባትን ስደትና መከራ፣ የበረሃውን ጉዞ እያነሣ የሚያመሰግን ታሪካዊ (Biographical) ይዘት ያለው ድርሰት ነው።

ማኅሌተ ጽጌን የደረሱት አባ ጽጌ ብርሃን የተባሉ ሊቅ መሆናቸው ይነገራል። ዘመኑም በ14ኛው መ/ክ/ዘመን ነው። አቡነ ዜና ማርቆስ የምሑርን ሕዝብ አስተምረው ወደ ይፋት በማምራት ወንጌልን በመስበክ ላይ እያሉ «ክርስቶስ ተወለደ፣ ሞተ፣ ተነሣ እያሉ እንዴት ያስተምራሉ?» በማለት አንድ አይሁዳዊ ሊቅ ጠየቃቸው። እርሳቸውም ኢሳ.11፥1 ላይ ያለውን የነቢዩን ቃል ጠቅሰው ስላብራሩለት በትምህርታቸው አምኖ ተጠምቆ ለመመንኰስ በቅቷል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስሙንም ጽጌ ብርሃን በማለት ሰይመውታል።

አባ ጽጌ ብርሃን ምሁረ ኦሪት ስለነበር አብሯቸው እየተዘዋወረ ሐዲስን ከብሉይ አስማምቶ ከተማረ በኋላ እንደ መዝሙረ ዳዊት 150 አድርጐ ማኅሌተ ጽጌን ከአማካሪው ከወረኢሉው ተወላጅ ከአባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ ጋር በመሆን አዘጋጀው። ድርሰቱም ቤት እየመታ በአምስት በአምስት ስንኝ የተከፈለ ነው።

አባጽጌ ብርሃንና አባ ገብረ ማርያም ከመስከረም 26 – ኅዳር 5 ማኅሌተ ጽጌን ለመቆምና የጽጌን ጾም ለመጾም በየዓመቱ በደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም እየመጡ ይሰነብቱና በዓለ ቍኢስቋምን ውለው ወደየቤታቸው ይመለሱ ነበር።

ለዚህም ማስረጃው በአፄ ሠይፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት አባ ጽጌ ብርሃን ለደብረ ብሥራትና ለደብረ ሐንታ ሊቀ ካህናት ሆኖ ተሾሞ እንደነበር ገድሉ ይናገራል። (ትንሣኤ ቁ. 61/1975 ገጽ 11–12)

በነገራችን ላይ የጽጌ ጾም የጌታንና የእመቤታችንን ስደትና መንገላታት በማሰብ ስለ ፍቅራቸው ባሕታውያን፣ መነኮሳትና አንዳንድ ምእመናን በፈቃዳቸው የሚጾሙት ነው።

## 3. ሰቆቃወ ድንግል

ሰቆቃ ማለት ለቅሶ ዋይታ ማለት ነው። እመቤታችን ልጇን ይገድሉ ብኛል ብላ የሄሮድስ ወታደሮች ሲከተሏት፣ የዮሴፍ ልጅ ዮሳዕ የቤተ ልሔም ሕፃናትን እልቂት ሲነግራት፣ ጥጦስና ዳክርስ የተባሉ ከግብፅ ወደ እሥራኤል በሚወስደው መንገድ በጋዛ በር የሚዘርፉ ሽፍቶች ሲያጋጥሟት ያለቀሰችውንና በተወደደ ልጅዋ ላይ የወረደውን መሪር ዕንባ በማስታወስ የሚዘመር ነው። ይህም መዝሙር በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደብረ ወርቅ ቤተ ክርስቲያን የድጓ መምህር በነበሩት በመምህር አርከሥሉስ እንደተደረሰ ይነገራል። (በቦታው ተገኝቼ የአካባቢው ሊቃውንት እንደነገሩኝ)

## ዝክር

ይህ ትውፊት በአሁኑ ወቅት በተለይም በከተሞች አካባቢ እየተረሳ የመጣ ይመስላል። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በወርኀ ጽጌ ዘወትር ቅዳሜ የአንድ አካባቢ ሰዎች ማዕከላዊ በሆነ ቦታ ተሰባስበው በእመቤታችን ስም ዝክር ይዘክራሉ። ዐቅመ ደካሞች፣ ድኾችና መንገደኞች ተጠርተው በእመቤታችን ስም እንዲበሉና እንዲጠጡ ይደረጋል። ይህም ትውፊት እመቤታችን ወደ ኢትዮጵያ በመጣች ጊዜ ኢትዮጵያውያን አባቶችና እናቶች ያደረጉላትን መስቱንግዶ ለማሰብ ነው።

## እመቤታችን በኢትዮጵያ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው የነቢዩ ሆሴዕ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ (ሆሴዕ 11፥1) ንጉሥ ሄሮድስ በቅንዐት መድኃኒታችንን ለመግደል በተነሣ ጊዜ ወደ ግብፅ በረሃ ተሰድዳለች። የስደትዋም ወቅት 3 ዓመት ከ6 ወር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ራእይ 12፥6።

በዚያን ዘመን ግብፃውያን መምለክያነ ጣኦት ስለነበሩ እመቤታችንን በስደትዋ ወቅት በሐዘን ላይ ሐዘን በችግር ላይ ችግር ፈጠሩባት እንጂ አላስተናገድዋትም። በዚህም የተነሣ ፈለገ ግዮንን (ዓባይን) ተከትላ ወደ ኢትዮጵያ መምጣትዋን የታሪክ፣ የሥነ ቅርስና የስያሜ ማስረጃዎች ይገልጣሉ። British Museum, Ethiopic MS.Add. 16-193 (Dillman, B.M. catalogue, xiii)

እመቤታችን የዓባይን ወንዝ ተከትላ ወደ ደቡብ ከወረደች በኋላ የመረብን ወንዝ በመያዝ ወደ ምሥራቅ አመራች። በመጀመሪያ ያረፈችውም በምዕራብ ኤርትራ በሚገኝ ሲሃት በተባለ ቦታ ነው። ከዚያም ተነሥታ ወደ ሐማሴን በመሄድ አስቀድማ ደብረ ዳሞን በኋላም የአኵስም ከተማን ባርካለች። ከአኵስም ተነሥታ ወደ ደቡብ በመጓዝ በተከዜ በረሃ በደብረ ዓባይ በኩል አድርጋ ዋልድባ ላይ ዐረፈች።

እመቤታችን በዋልድባ ገዳም በሚገኘው ዋሻ ውስጥ ለጥቂት ቀናት ከተቀመጠች በኋላ ከዋልድባ ወጥታ ወደ ምሥራቅ በመጓዝ ዛሬ ግብጣይት በሚባለው በጐንደር ክፍለ ሀገር በእስቴ አካባቢ በሚገኘው መንደር ተቀመጠች። በዚያ መንደር የነበሩ ሰዎችም እንግዳ ተቀባዮች ስለነበሩ ቤታቸውን ለቅቀው ምንጣፋቸውን አንጥፈው የሚበላ የሚጠጣ አቅርበው አስተናግደዋታል። ቦታዋ ግብጣይት የተባለችውም የእመቤታችንን ከግብፅ መጥታ በዚያ ቦታ ማረፍ ለማሰብ ነው።

ከዚህ በኋላ ወደ ሰሜን ጣና ጐርጐራ በመሄድ ከጣና ቂርቆስ አካባቢ ደረሰች። በዚያ ሃገር የነበረው ንጉሥም በእንግድነት ተቀብሎ ከቤቶቹ አንዱን ለቅቆ አስተናገዳቸው።

ጥንት የኢትዮጵያ መኳንንት ዘራቸውን የሚቆጥሩት ከንጉሥ ሰሎሞን ነበርና የመጡት ከኢየሩሳሌም መሆኑን ሲሰማ በእጅጉ ደስ አለው።

ሌሊትም በራእዩ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል በቤቱ ያስተናገዳቸው አምላክንና እናቱን መሆኑን ነገረው። እንግዶቹን ሊያዩ ከተሰባሰቡት የአካባቢው ሰዎችም መካከል ብዙ ድውያን ተፈወሱ። ይህን ድንቅ ተአምር ያዩ ሁሉ እጅ መንሻቸውን ይዘው እየመጡ የደስታው ተካፋይ መሆናቸውን በጣና ቂርቆስ የሚኖሩ አባቶችና ምእመናን ያረፈችበትን ቦታ ጭምር እያሳዩ እስከ ዛሬ ድረስ ይናገሩታል። እመቤታችን በጣና ቂርቆስ ለ3 ወራት ያህል ተቀምጣለች። (አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ፤ በሪሁን ከበደ፣ የዋልድባ ገዳም ታሪክ፣ ጥቅምት 1983 ዓ.ም)

ከዚህ በኋላ በቅዱስ ዑራኤል መሪነት ጣና ቂርቆስን ለቅቃ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ወደ ላዕላይ ግብፅ ሄደች። በዚያም የሄሮድስን መሞት መልአኩ አበሠራት።

አገራችን ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የአሥራት ሀገር ሆና የተሰጠችው በዚህ ጊዜ ነው። ከዚያን ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ለእናታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር አለን።

## ቍስቋም

እመቤታችን ከስደትዋ ተመልሳ በላዕላይ ግብፅ ደብረ ቍስቋም በተባለው ቦታ ማረፍዋን በማሰብ በየዓመቱ ኅዳር 6 ቀን በቤተ ክርስቲያናችን ይከበራል። የወርኀ ጽጌ ማብቂያም በዚሁ ቀን ነው።

እንግዲህ ወርኀ ጽጌን ስናከብር እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሊታወሱን ይገባል። ከአበው ጋር በማኅሌቱ ተገኝተን እየዘመርን ዝክሯን እየዘከርን ከእመቤታችን በረከት እንካፈል ዘንድ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። ✣

የእመቤታችን በረከት አይለየን

አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (እምነትና ቀኖና) የምንማርበት ነው።

**ባለፈው እትማችን ስለ ምሥጢረ ቁርባን ምንነት፣ በብሉይ ኪዳንም እንዴት በምሳሌ ተገልጾ እንደ ነበር፣ አንዳንድ ምሳሌዎችን በማንሣት፣ እንዲሁም በሐዲስ ኪዳን በአልዓዛር ቤት ጌታ እንደመሠረተው ተመልክተናል። ከዚያ የሚቀጥለውን ክፍል ደግሞ ዛሬ ይዘን ቀርበናል።**

## ምሥጢረ ቁርባን

### የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ

በምሴተ ሐሙስ ልዑለ ባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን፣ ወይኑን ባርኮ ቀድሶ አክብሮ ለውጦ ፍጹም ሥጋውና ደሙ አድርጐ ለደቀ መዛሙርቱ «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንሥቶ...ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» በማለት በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል የሚፈተት ሥጋውንና የሚፈስ ደሙን ሰጥቶአቸዋል። ማቴ.26፥26–29።

ይህን መሠረት በማድረግ ዛሬም ካህናት ኅብስቱንና ወይኑን በጸሎተ ቅዳሴ አመስግነው ሲባርኩት ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል። (ኵኵሐ ሃይማኖት ገጽ 109፣ የአሥራ አራቱ ቅዳሴ ትርጓሜ)

«ይህ ኅብስት የፈጣሪያችን የአማኑኤል ሥጋ ነው። ይህ ጽዋዕ የአማኑኤል ደም ነው» ብለው ሲያቀብሉን «የጌታ ሥጋና ደም ነው ማለት እንደ ምን ይቻላል?» ሳንል በእውነት አምነን የአምላካችንን ቃል መሠረት አድርገን እንቀበላለን። ባለቤቱ ራሱ ኅብስቱን «ሥጋዬ ነው» ወይኑንም «ደሜ ነው» ብሎ ለሐዋርያቱ አቀብሏልና።

ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ይህን የጌታን ቃል መሠረት አድርገው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን መስክረዋል። የቂሳርያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ባስልዮስ ውዳሴ አምላክ በተሰኘው ድርሳኑ:- «ጌታዬ ናፍቆቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በዚህ በቅዱስ ቁርባን በሥጋ በደም መለኮትህ እንደተዋሐደው ዐውቃለሁ ይህንንም ስላወቅሁ ከክብር ሁሉ ጋር የከበረ ሥጋህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ። በዚህ በሚታየው ኅብስት መልክ እንድቀበል አምናለሁ። ከክብር ሁሉ የከበረ ደምህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ በዚህ በሚታየው እንድቀበል አምናለሁ። ስግደት የሚገባው ግሩም መለኮትህንም እንድቀበል በፍጹም ልብ አምናለሁ። እንዲሁም ከሆነ አንድ ቀን ፈጣሪዬን ጠባቂዬን ፈራጀን መድኃኒቴን እቀበላለሁ። ዳግመኛም ይህንን ቅዱስ ቁርባን በኅብስትና በወይን አካል እንዳገኘው አምናለሁ ኅብስትና ወይን መሆን እንደሌለበትም አምናለሁ።

የዓለም ሁሉ ፈጣሪ በመንግሥተ ሰማይ ኪሩቤል ሱራፌል የሚሰግዱልህ ንጉሠ ነገሥት አንተ ተሠውረህበት እንዳለህ አውቄ አምኜ እቀበለዋለሁ።

አምላኬ ሆይ! ይህ ቃል እንደተናገርከው ነውና የአንተ ቃል ነው እንጂ የሌላ ቃል አይደለም። ያንተ ቃል ስለመሆኑ እናታችን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሁሉ አምናለሁ እውነተኛ ምሥጢር አይደለም ለሚለኝ ነፍሴን ለሞት እሰጥ በታለሁ።» ብሏል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ ይህን አስመልክቶ ሲያስተምር «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ከእዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» ብሏል። ዮሐ.6፥51። ዳሩ ግን ልባቸው በጥርጥር ማዕበል የተመታ አይሁድ ይህ የጌታ ትምህርት አልዋጥ ብሎአቸው በምጸት «ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?» በማለት ትምህርቱን ለማስተባበል ሞከሩ። ዮሐ.6፥52።

ዛሬም ቢሆን ተረፈ አይሁድ የጌታን ቃል ለማስተባበል የማይቆፍሩት የክህደት ጉድጓድ የማይፈነቅሉት የሐሰት ድንጋይ የለም ይህ መሆኑ ግን ሊያስደንቀን አይገባም።

ሁሉን ቻይ ጌታ ዘመን በማይሽረውና በማይለውጠው አማናዊ ቃሉ አስቀድሞ በአጽንዖት እንዲህ ብሎ አስገንዝቦናል «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» ዮሐ.6፥53።

ለዚህ ቅዱስ ቃል ተጻራሪ ሆኖ ሥጋ ወደሙ መታሰቢያ እንጂ አማናዊ (እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም) አይደለም ብሎ የሚያስተምር የክርስቶስ ጠላት ነው።

ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘትና የክርስቶስን መንግሥት ለመውረስ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የጌታን ሥጋና ደም መቀበል ግዴታ መሆኑን ጌታችን እንዲህ ሲል አረጋግጦልናል «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና» ዮሐ.6፥54 ና 55።

ጌታችን ራሱ በቃሉ ላስተማረውና ላረጋገጠው ዐቢይ ትምህርት ጀርባውን ሰጥቶ የጌታችንን ትዕዛዝ ጥሎ «ሥጋውና ደሙን መታሰቢያ ወይም ምሳሌ ነው፤ ለድኅነት አስፈላጊ አይደለም» የሚል ሁሉ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የወጣ ነው። ቁጥሩም የጌታን ትምህርት ይቃወሙ ከነበሩት ከአይሁድ እንጂ ከክርስቶሳውያን አይደለም።

«ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመስግኖ፥ ቆርሶም ...እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና» ብሏል 1ቆሮ.11፥23–26።

ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ ወይም ምሳሌ እንጂ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም አይደለም ብለው የሚክዱ ክፍሎች ለክህደታቸው አስረጅ አድርገው ለማቅረብ ከሚጠቃቅሱአቸው አንዱ «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚለው ነው። ዳሩ ግን ቃሉን በአንክሮ ለሚያጤነው ሰው ሁሉ የእነርሱን ስሕተታዊ ትምህርት የሚደግፍ ወይም የሚያንጸባርቅ አለመሆኑን ይገነዘባል። ይኸውም ስናስተውለው ሥጋውና ደሙን ስንቀበል መድኃኒታችን ለእኛ ድኅነት ሲል ከቤተልሔም ዋሻ እስከ ቀራንዮ ኮረብታ የደረሰበትን ፀዋትወ መከራ ሕማሙን ሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን እንድናስብና እንድናስተውል ለማስረዳት ነው።

ትክክለኛ የቃሉ ትርጉም ከላይ የተገለጸው ለመሆኑ የሐዋርያውን ትምህርት በድጋሚ ብንመለከት «...በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና» በማለት ያረጋግጥልናል።

ሥጋውን ደሙን በምንቀበልበት ጊዜ ሁሉ የጌታችንን መከራውን ሕማሙንና ሞቱን እናዘክራለን። ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ የሰጠንን የአምላካችንን ፍቅር በኅሊናችን ሰሌዳ ተሥሎ እስከ ዕለተ ሞታችን እንዲኖር ቅዱስ ቁርባን ታላቅ ማኅተም መሆኑን ማስገንዘቡ ነው። በቅዳሴአችንም «ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ፤ አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን» የምንለውም ይኸንኑ ቃል መሠረት አድርገን ነው።

በአጭር ቃል «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚለው መከራዬን ሕማሜን ቤዛነቴን እያሰባችሁ፤ አምናችሁ ሥጋዬንና ደሜን ተቀበሉ ማለቱ ነው። ✣

ይቀጥላል

## ከቅዱሳት መጻሕፍት

የሰውን ልጅ ለመዋጋት ሰይጣናት ለምን ይላካሉ?

1. ነፍሳችን ተጋድሎን (ዖርን) ትማር ዘንድ፤

2. ኃጢአትን በመቃወም ፈጣሪያችንን መውደዳችንን እንገልጽ ዘንድ፤

3. ያለ እግዚአብሔር አጋዥነት በራሳችን ችሎታ ብቻ ፈቃዱን መፈጸም እንደማንችል እናውቅ ዘንድ፤

4. ትሩፋት ሠርተን፣ መከራ ተቀብለን ኃጢአትን ድል በማድረግ ለመንግሥተ ሰማያት የበቃን እንሆን ዘንድ ነው።

1ጴጥ.4፥2፤ 1ጴጥ.4፥18፤ ዕብራ.12፥11፤ መጽሐፈ ፊልክስዩስ ገጽ 96።

## የእግዚአብሔር ሕግ

ከዲ.እሸቱ ታደሰ

መግቢያ

አምላካችን እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ የሚመዝንና የሚያስተውል አእምሮ ሰጥቶት በነፃነት የፈጠረው መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ስለዚህም በተሰጠው ነፃ አእምሮ ክፉውን ከመልካሙ በመለየት በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ መኖር ለሰው ልጅ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ የተሰጠው ጸጋ ነው። ይህንንም የጻድቃን አባቶቻችን ታሪክ በግልጥ የሚያስረዳ መሆኑን በመጽሐፍ ተጽፏል። በዚህ ተቃራኒ ደግሞ አእምሮአቸውን በሕገ ልቡና ከኃጢአት ለይተው መኖር የተሳናቸው ሰዎች ምን እንደተፈረደባቸው በሰብአ ትካት (በኖኅ ዘመን የጠፉ ሰዎች) እና በሰዶምና በገሞራ ሰዎች ታሪክ የታወቀ ነው።

አምላክ ለሰው ልጆች ላዘጋጀው ክብር እንበቁ መመሪያ የሚሆኑ የእምነትና የምግባር ሕግጋትን በሕገ–ልቡና ብቻ ሳይሆን በዓይን በሚታይና በእጅ በሚዳሰስ ሁኔታ በጣቶቹ በመጻፍ በነቢዩ በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሰጥቷል። ዘጸ.20፥1–17፤ ዘዳግ.5። እነዚህ ሕግጋት አሥር በመሆናቸው «አሠርቱ ትእዛዛት» በመባል ይታወቃሉ። በሌላ አነጋገርም «ትእዛዛተ ኦሪት» ይባላሉ። በዚህ ጽሑፍም በተከታታይ ስለእነዚሁ «አሠርቱ ትእዛዛት» ለመግለጽ ያቀድን በመሆኑ ለዛሬ መግቢያውን እነሆ።

አሠርቱን ትእዛዛት በጠቅላላው ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ዐበይት ነጥቦች እንድናስተውል ያደርጉናል።

### ሀ. አሠርቱ ትእዛዛት

### በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉ ኪዳናት ናቸው።

አሠርቱ ትእዛዛት የተሰጡት ለአለፉት በቀደምት ዘመናት ለነበሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆን እኛም የዚህ ዘመን ሰዎች ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በኋላም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካስተማሩት ርቱዕና ምሉዕ የክርስትና ሕግና ትምህርት ጋር በማዋሐድ እንድንመራባቸው ነው። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል የተደረጉ ኪዳናት መሆናቸውን መረዳት ይገባል። ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴም ይህንኑ ለማስረዳት «አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለነው ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለነው ከእኛ ከሁላችን ጋር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ብቻ ይህችን ቃል ኪዳን አላደረገም።» በማለት አስገንዝቧል። ዘዳ.5፥2–3። ከዚህ በመነሣት ነው አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸውን ጽላት «የቃል ኪዳኑ ጽላት» ብለን የምንጠራው። ዘዳ.9፥11። እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት መጽሐፍም «የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ» ተብሏል። ዘዳ.24፥7።

እንግዲህ እነዚህ ትእዛዛት እኛ እግዚአብሔርን ባመለክንበት ወይም እርሱን ባመንንበት ጊዜ በእኛና በእርሱ መካከል የተመሠረቱ ኪዳናት ናቸው። ልዑል እግዚአብሔርም እነዚህን ኪዳናት ከሰዎች ልጆች ጋር ባደረገ ጊዜ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ ሁኔታ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። በዚያን ጊዜ ተራራው ይናወጥ ነበር። የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር። ከእርሱም እንደ እቶን ያለ ጢስ ይወጣ ነበር። ዘዳ.19፥16–19። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ሁኔታ ሲገልጥ «ሙሴ እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ» ብሏል። ዕብ.12፥21።

## ለ. የትእዛዛቱ አስፈላጊነት

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በፈጣሪአችን በእግዚአብሔር አንደበት የተነገሩ በጣቶቹም የተጻፉና ከእርሱ የተሰጡ መሆናቸው አስፈላጊነታቸውን የጎላ ያደርገዋል። ዘጸ.20፥1። ዘዳ.9፥10። ነቢዩ ሙሴም አሠርቱን ትእዛዛት ተቀብሎ ሲወርድ ከተራራው በታች የሚቃጠል መሥዋዕት የደኅንነትም መሥዋዕት ከአቀረበ በኋላ ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በመቀጠልም «በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ» በማለት ተናግሯል። ዘዳ.24፥4–8።

አሠርቱ ትእዛዛት አስፈላጊ ከመሆናቸው የተነሣ በእግዚአብሔር ጣቶች ከአንድ ጊዜ በላይ ተጽፈዋል። ዘዳ.20፥2–17። ዘዳ.5፥6–21። እግዚአብሔርም ሁለት ጊዜ ጽፏቸዋል። መጀመሪያ ሙሴ በተቀበላቸውና ከእጁ ወድቀው በተሠበሩ ሁለቱ ጽላት ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ሙሴ በመጀመሪያዎቹ ዓይነት በቀረጻቸው ጽላት ላይ ነው። ዘዳ.10፥41። ዘዳ.34፥1።



ሙሴ በሲና ተራራ ጽላት ሲቀበል ኦሪ.ዘጸ.34፥27–28

## ሐ. ቁጥራቸው ለምን አሥር ሆነ?

በዕብራውያን አሥር ቁጥር የምሉዕነት ምሳሌ ነው። አሠርቱ ትእዛዛትም ምንም እንኳን በቁጥር አሥር ቢሆኑ የሕግጋት ሁሉ ማለትም የትእዛዛት ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው። በቁጥር አሥር መሆናቸው የምሉዕነት ምሳሌ መሆኑን በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለማስረዳት እንሞክራለን።

አሥሩ ደናግል ማቴ.25፥1–12። በዚህ ምሳሌ አሥር ቁጥር መላውን ዓለም የሚያመለክት ነው። ጻድቃንንም ኃጥአንንም ጨምሮ ሁሉንም ያመለክታል። ተዘጋጅተው የቆዩት አምስቱ የጻድቃን የቀሩት አምስቱ ደግሞ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው።

ጌታቸው እስኪመጣ ድረስ ነግደውና አትርፈው እንዲጠብቁት አሥር ምናን የሰጣቸውን ባሪያዎችም ያመለክታል። ሉቃ.19፥13። እነዚህ ባሪያዎች የሰው ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው የጻድቃንም የኃጥአንም። ከእነዚህ ባሪያዎች መካከል የፊተኛውና በሚገባ ነግዶ ያተረፈው «ጌታ ሆይ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ» ብሎ ለጌታው መለሰ። ሉቃ.19፥17። ስለዚህም በተሰጠው ችሎታና ዕውቀት ሁሉ ተጠቅሞ በመሥራት የሚጠበቅበትን አደራና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ የተወጣ የፍጹም ሰው ምሳሌ ሆኖ እንመለከታለን። ይህ ባሪያ የተጠበቀበትን በሚገባ ፈጽሞ በመገኘቱ ከጌታው የተቀበለው ዋጋም ሙሉ ነው። ‹አንተ በጎ ባሪያ በጥቂት የታመንክ ስለሆንክ በአሥር ከተማዎች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ።» ሲል ጌታው አመስግኖታል። ሉቃ.19፥17።

የጠፋው ድሪም ታሪክም አሥር ቁጥር የምሉዕነት ምሳሌ መሆኑን ያስረዳል። በመጽሐፍ የተጠቀሰችው ሴት አሥር ድሪም ነበራት። አንዱ ጠፋ። በዚህ ታሪክ አሥሩ ድሪም የሴቲቱ ጠቅላላ ንብረት ምሳሌ ነው። ሉቃ.15፥8።

ስለ አሥራት የተሰጠው ትእዛዝም የሰውን መላ ንብረት በአሥር እጅ እንደመዘነው እንመለከታለን። ካለውም አንዱን እጅ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ ታዝዟል።

ነቢዩ ዳንኤልም «እኛን ባሪያዎችህን አሥር ቀን ያህል ትፈትነን ዘንድ እለምንሃለሁ» ሲል የመጨረሻና ከፍተኛውን የፈተና ጊዜ ለእርሱ አቅምም ፍጹም የሆነውን ማለቱ ነው። ዳን.1፥12።

ስለ አሥር ቁጥር የተነገረው ሁሉ በመቶና በሺዎች ለሚነገሩ አሥሮችም ሊተረጐም ይችላል። ለምሳሌ የጠፋውን በግ ተከትሎ ስለሄደው መልካም እረኛ የተነገረው ይህን ሊያስረዳ ይችላል። በዚህ ታሪክ ውስጥ «መቶ በጎች» የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ ነው። እንግዲህ አሥር ቁጥር ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የምሉዕነት ምሳሌ ነው። ቅዱስ አውግስጢኖስ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21፥11ን በተረጐመበት ድርሳኑ «አሥር ቁጥር በአሠርቱ ትእዛዛት የተገለጡት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሕግጋት ሁሉ ምሳሌ ነው» ያለውም ለዚህ ነው። በእርግጥም አሠርቱን ትእዛዛት በጥሞና ብንመረምራቸው በእያንዳንዷ ውስጥ ያለው ምሥጢራዊ ትርጉም የተቀሩትን ሕግጋት ሁሉ የሚያጠቃልል ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁን እንጂ ሁሉም ደግሞ ተጠቃለው በአንድ ትእዛዝ ይካተታሉ። ይህም ቆየት ብለን በሰፊው የምንመለከተው ፍቅር ነው።

### መ. ሁለቱ ጽላት

አሠርቱ ትእዛዛት ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የያዘ ነው። የመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን አምልኮታዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ሦስት ትዕዛዛትን ያቀፈ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች እርስ በርሳቸው ስለሚኖራቸው ግንኙነት የሚያወሱትን ስድስት ትእዛዛት የያዘ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ሕግ ዐዋቂ ሊፈትነው ሽቶ «መምህር ሆይ ከሕግ ማንኛይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት» ብሎ በጠየቀው ጊዜ መድኃኒታችንም መልሶ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርሷም ‹ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ› የምትለው ናት ኦሪት እና ነቢያትም በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተዋል።» ማለቱ ለዚህ ነው። ማቴ.22፥35–40።

በእነዚህ ጽላት ላይ በመጀመሪያው ነገረ አምላክን የሚያወሱት ትእዛዛት የተጻፉ ሲሆን በሁለተኛው የተጻፉት ደግሞ ፍቅረ ቢጽን የሚያስተምሩት ተጽፈዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው ጸሎትም በመጀመሪያ የተቀመጠው ነገረ ሃይማኖትን የሚያወሳው ነው። «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በምድር ይሁን...» ካለ በኋላ ነው ስለ ፍቅረ ቢጽ የሚያወሱት ቃላት የተከተሉት። ማቴ.6፥9።

### ሠ. ሕገ ልቡናን ያስታውሱናል።

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉና በጽላት ላይ የተቀረጹ ቢሆኑም በሰው ዘንድ ያልነበሩና የማይታወቁ አዲሶች አይደሉም። ከሙሴ እና ከጽላቱም መቀረጽ በፊት የነበሩ ናቸው። በመሆኑም ሳይጻፉ በሕገ ልቡና አበው ሲመሩባቸው የነበሩትን ቀደምት ሕግጋት ያስታውሱናል። ለዚህም የሚከተሉትን ማረጋገጫዎች እንመልከት።

1. አትግደል:- መግደል ቀድሞም ቢሆን በሰው ልጆች ዘንድ ኃጢያት ነበር። ቃየል አቤልን በገደለው ጊዜ እግዚአብሔር ቃየልን በከባድ ቅጣት እንደ ቀጣው ተጽፏልና። ዘፍ.4፥13። ስለዚህ ይህ ትእዛዝ በጽላት ተቀርጾ ለሙሴ ከመሰጠቱ በፊት በሕገ ልቡና ዘመን በሰዎች አእምሮ የሚታወቅ ነበር።

2. አታመንዝር:- ሰዎች ዝሙት ኃጢአት መሆኑን ያወቁት ከሙሴ ዘመን በፊትም ነበር። ከሙሴ በመቶ በሚቆጠሩ ዓመታት ቀድሞ የነበረው ጻድቁ ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት በኃጢአት ወጥመድ ለመያዝ በፈተነችው ጊዜ «እንዴት ይህን ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» በማለት እምቢ ማለቱ ዝሙት ከሙሴ በፊትም በሕገ ልቡና በኃጢአትነቱ የሚታወቅ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ዘፍ.39፥9። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር በጥፋት ውኃ ዓለምን ያጠፋው የሰው ልጅ ለክፉ ሥራ የተገዛና ኃጢአት የሠለጠነበት በመሆኑ ነው። ዘፍ.6፥5–8። ዘፍ.7፥19። እነዚህ የምኞትና የፍትወት ሥራዎች ሁሉ ኃጢአት መሆናቸው ከሙሴ በፊት በሕገ ልቡና ዘመንም የሚታወቁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

3. አትስረቅ:- መስረቅ ክፉ ሥራ (ኃጢአት) እንደሆነ ቀደም ብሎ የሚታወቅ ለመሆኑ ያዕቆብ ከላባ ጋር ሲከራከርባቸው የነበሩት የተሰረቁ የላባ አማልክት ታሪክ ምስክር ነው። ዘፍ.31፥30–39።

4. አትመኝ:- መመኘትም ኃጢአት መሆኑ ቀደም ብሎ ከሙሴ በፊትም መታወቁ ኢዮብ «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ሲል ከተናገረው ቃል ግልጥ ሆኖ ይገኛል። ኢዮ.31፥1።

5. ሰንበትን አክብር:- ይህም አሠርቱ ትእዛዛት ለሙሴ ከመሰጠታቸው በፊት የሚታወቅ ነው። እሥራኤል መናን እንዲለቅሙ በተነገራቸው ጊዜ ሰንበትን ደግሞ እንዲያከብሩ ታዝዘው ነበር።

«እግዚአብሔርም የተናገረው ይህ ነው። ነገ እረፍት ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው።» ዘጸ.16፥23–29። በተለይም እጅግ ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ማረፉ ሰንበትን ማክበር ከሙሴ በፊትም የሚታወቅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ዘፍ.2፥2–3።

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ማስረጃዎች አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች ተጽፈውና በጽላቱ ተቀርጸው ለሙሴ ከመሰጠታቸው በፊት በሕገ ልቡና በሰው ልጆች አእምሮም የነበሩ በመሆኑ እነዚህን ቀደምት ሕግጋተ ልቡና የሚያስታውሱን ናቸው ለማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ ደግሞ እነዚህን ትእዛዛተ እግዚአብሔር ከእርሱ የተሰጡና በእርሱና በሰው ልጆች መካከል የተደረጉ ኪዳናት መሆናቸውን እያሰቡ የፈጸሟቸውና የተመሩባቸው በረከትን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙ ሲሆን፣ የናቁአቸውና የተውአቸው ደግሞ መርገምን ይቀበላሉ። እነዚህን ትእዛዛተ እግዚአብሔር ለመፈጸምና የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታም ለመቀበል ደግሞ እያንዳንዳቸውን በጥልቀት መመልከትና ማጥናት ተገቢ ነው። በሚቀጥለው እትም የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይዘን እንቀርባለን የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን። ✥

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «እሱ ራስህን ይቀጠቅጣል»

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ

ኤልሻዳይ ሁሉን ማድረግ የሚችል ልዑል እግዚአብሔር ከመጀመሪያዋ ዕለተ እሑድ ጀምሮ እስከ ስድስተኛዋ ዕለተ ዓርብ ድረስ ሰማይንና ምድርን፣ በገጸ ምድር የሚታየውንና የማይታየውን የሚበላውንና የማይበላውን፣ ረቂቁንና ግዙፉን፣ ጨለማንና ብርሃንን በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሰውንና በአየር የሚበርረውን ፍጥረት ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በመጨረሻ «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ» (ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር) አለ።

በዚህም ቃሉ አራት ባሕርያት (ጠባያት) የሚገኙበትን ሥጋንና ሦስት ጠባያት ያሏትን ነፍስን አዋሕዶ ሰውን ፈጠረ። አራት ባሕርያት የተባሉት የሥጋ ጠባይ ሀ. እሳት ለ. ነፋስ ሐ. ውኃና መ. መሬት ናቸው። ሦስት ባሕርያተ ነፍስ የተባሉትም፣

ሀ. ለባዊነት፤ ለ. ነባቢነትና ሐ. ሕያውነት ይባላሉ። ወንድና ሴት አድርጎም ፈጠራቸው።

በእነዚህ ሰባት ባሕርያት አጊጦ የፈጠረውን ሰው ከፍጥረታት ሁሉ በላይ አከበረው። ዘፍ.1፥26–28።

በአራት አፍላጋት በተከበበች፣ በልምላሜና በአበባ ባጌጠች በልዩ ልዩ ፍሪያትም በበለጸገች፤ ምንም ነገር በማይታጣባት ኤዶም ገነት ውስጥም አኖረው። በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሊኖር የሚገባውን ሕገ ልቡናዊንም በአእምሮው ሳለበት። ስለዚህም በገነት ውስጥ የሚገኘውን ሁሉ እንዲበላ ሲፈቅድለት፣ በገነት መካከል የምትገኘውን፣ ክፉንና በጎን ለይታ የምታስታውቀውን ዛፍ ፍሬ ግን እንዳይበላ አጥብቆ ከለከለው። ዘፍ.2፥7–25።

ዛፍዋ ለመብላት የምታስጐመጅ ያማረች የተዋበች ነበረች፤ ቢሆንም አዳም በመጽሐፍ ሳይሆን በቃል የተሰጠውን ሕግ ልቡናዊ ጠብቆ ሰባት ዓመት ኖረ። ታዲያ እኩይ ዲያብሎስ ከዐቅሙና ከችሎታው በላይ የሆነውን፣ ባሕርዩ የማይፈቅድለትን አምላክነት ሽቶ፣ ሳይሆንለት በመቅረቱ ሲቆጨው፣ የአዳምን ክብር ሲያይ፣ «ባለጌ እሱ በገበረ አያዝንም፣ ወንድሙ በቀረ እንጂ» እንዲሉ በቅናት በምቀኝነት እሳት ተቃጠለ፤ ርጎራጌ በማይታይበት የክፋት ጦር ተወጋ፤ አዳምን ከክብሩ ለማዋረድ ቆርጦ ተነሣ።

ስለዚህም ተንኮለኛ ከነበረችው እባብ ጋር ተዋሕዶ፣ እባብን መስሎ መጣና ሔዋንን በቃላት አታልሎ በእሷው አማካኝነት እንዳይበላት የተከለከለችውን ዛፍ ፍሬ እንዲበላ አደረገው። በዚህ ጊዜ አዳምና ሔዋን ሐፍረታቸው ተገለጸ፤ ክብራቸው ተገፈፈ፤ እርስ በርሳቸው ተፋፈሩና የበለስን ቅጠል ቆርጠው አገለደሙ። ምንም የሚሠወረው የሌለ አምላክም የሆነውን (የተደረገውን) ያውቃልና ኮቴውን እያሰማ ወዳሉበት ገነት መጣ። አዳምና ሔዋን ኮቴውን ሲሰሙ ደንግጠው ወደ አትክልቱ ውስጥ ገብተው ተሸሸጉ።

እግዚአብሔርም «አዳም! የት ነው ያለኸው?» በማለት ጠየቀ፤ ያሉበት ቦታ ጠፍቶት አይደለም፤ ዐውቆ ነውና ወደ እነሱ የኼደው፤ ነገር ግን እሱን ለማዳን ፍጹም ሰው የሚሆን ነውና በሰው ባሕርይ፣ በሰው አባባል ሲያነጋግረው መሆኑን ያመለክታል።

ታዲያ በዚህ ጊዜ የተሰማው የአዳም ድምፅ እጅግ አሳዛኝ ነበር፤ «በአታክልቱ ቦታ ድምፅህን ሰማሁና ፈራሁ ምክንያቱም ዕራቁቴን ነኝና!» የፈጣሪ መልስ «ዕራቁትህ መሆንህን ማን ነገረህ? በውኑ አትብላ ያልኩህን ፍሬ በላህ?» የሚል ነበር። የአዳም መልስ ደግሞ የሚያዋጣ አልነበረም፤ ነገር ግን ምክንያት ይሆነኛል መስሎት «አዎን ትሆንሃለች ብለህ የሰጠኸኝ ሴት አስታኝና በላሁ» አለ።

ሔዋንም «ለምን እንዲህ አደረግሽ» ስትባል «እባብ አሳተችኝ» የሚለውን ምክንያት ደረደረች። ይሁን እንጅ የአዳምም ሆነ የሔዋን ምክንያት ሊያዋጣ የሚችል አልነበረምና የሚከተለውን ፍርድ አስከተለ፤

## የእግዚአብሔር ፍርድ

1. <u>በእባብ ላይ፣</u>

ሀ. ከእንስሳት ሁሉ ተለይተህ በደረትህ ትሳባለህ፣

ለ. በሕይወት ዘመንህ ሁሉ መሬትን ትመገባለህ፤

ሐ. በዘርህ እና በሴቲቱ ዘር መካከል ጠላትነትን አቆማለሁ፤

እሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትነክሳለህ።

2. <u>በሔዋን ላይ፣</u>

ሀ. በፀነሽ ጊዜ መከራሽን አበዛለሁ፤

ለ. በመከራ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤

ሐ. እሱም (ባልሽ) ይገዛሻል።

3. <u>በአዳም ላይ</u>

ሀ. ባንተ ምክንያት መሬት የተረገመች ትሆናለች

ለ. እሾህና ኩርንችት ይበቅልባታል

ሐ. ወጥተህ ወርደህ፣ ወዝህን አንጠፍጥፈህ ትበላለህ

መ. መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ።

እንግዲህ ከዚህ ፍርድ መካከል «እሱ (የሴትዋ ዘር) ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኰናውን (ተረከዙን) ትነክሳለህ» የሚለው ኃይለ ቃል ነገረ መስቀል ሆኖ እናገኘዋለን። ዘፍ.3፥14–20።

አባታችን አዳም በዲያብሎስ አታላይነት ከከፍተኛ ስሕተት ላይ ቢወድቅም የምሕረትና የይቅርታ አምላክ ግን የሰው ልጅ እስከ መጨረሻው ድረስ የጠላቱ የዲያብሎስ ተገዥ እንዲሆን ስላልፈቀደ እሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ከሴትዋ ዘር ማለት ከሔዋን ከተገኘችው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በመስቀል ላይ ቆሞ የእባብ ዘር የተባለውን የዲያብሎስን ራስ እንደሚቀጠቅጥ፣ ማለትም ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ በዲያብሎስ እጅ የነበሩትን ነፍሳት «በሲኦል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመቃብር ያላችሁ፣ ውጡ፤ በጨለማም ያላችሁ ተገለጡ» በማለት የዲያብሎስን መንግሥት አፈራርሶ ነፃ እንደሚያወጣቸው አስቀድሞ በምሳሌ ተናገረ። በእውነትም ነቢዩ ኢሳይያስ «በእውነት ደዌያችን ወሰደ፤ ሕመማችንም ተሸከመ» እንዳለ እኛ በበደልን ስለ እኛ፣ እኛን ነፃ ለማውጣት የዲያብሎስ መሣሪያዎች በሆኑት በእኩያን አይሁድ እጅ ተይዞ መስቀሉን ተሸክሞ፣ በመስቀል ተሰቀለ፤ «ሰኰናውን ትነከሳለህ» በተባለውም መሠረት የጌታችን እግር በብረት ተቸነከረ። ኢሳ.53፥1–12፤ ዮሐ.19፥17–19።

የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መስቀል ከመውጣቱ በፊት «ሙሴ የነሐሱን እባብ (አርዌ ብርት) በምድረ በዳ እንደ ሰቀለው እንደዚሁ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ይሰቀላል» በማለት አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ዘኁ.21፥9፤ ዮሐ.3፥14።

ታዲያ እሰቀላለሁ፣ እሞታለሁ፣ እነሣለሁ፣ ማቴ.16፥21፣ ማር.8፥31–33፤ ሉቃ.9። በማለት አስቀድሞ በተናገረው መሠረት መጋቢት 27 ቀን ዓርብ ዕለት በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ሞተም። በሦስተኛው ቀን በመለኮታዊ ሥልጣኑ ተነሣ። አሁንም መስቀልን የምናከብረው የእኛ የሰው ልጆች ጠላት ዲያብሎስ ራሱን የተቀጠቀጠበት ድል የተነሣበት፤ እኛም የሰው ልጆች ነፃ የወጣንበት፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ነገረ መስቀል ሕማምና ሞትን የምናስታውስበት፤ ማንኛውንም ሥውር ጠላት ድል የምንነሣበት ስለሆነ ነው።

እኛ መስቀልን ስናከብር ኃጢአትን የምንማር መስሎ የሚታያቸው ሰዎች ሲያጋጥሙን ብዙ አንደነቅም፤ ሐዋርያው አስቅድሞ የመስቀሉስ ነገር (ባለማመናቸው) ለተጐዱት ስንፍና ነው፤ (በእምነታችን) ለዳንን ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» በማለት መልስ ሰጥቶልናልና። 1ቆሮ.1፥18፤ አይሁድ ተአምር ማየትን ይፈልጋሉ፤ አረማውያንም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ስለተሰቀለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በምናስተምርበት ጊዜ ለአይሁድ ኃጢአት የምንሠራ ለአረማውያን የሰነፍን (አእምሮአችንን ያጣን) ይመስላቸዋል። እኛ ግን ስለ ክርስቶስ እናስተምራለን እንጂ አልሰነፍንም። 1ቆሮ.1፥23–26።

አሁንም እኛ መስቀልን ስናከብር ባዕድ እንዳመለክን አድርገው የሚመለከቱ ካሉ የኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒትነት ያልተቀበሉ፣ ከክርስትና ሕይወት ውጭ መሆናቸውን ያስተውሉ፤ እኛ መስቀልን ስናከብር የክርስቶስን ሕማምና ሞት የምናስብ፤ የጌታችን በመስቀል መሞት፣ የእኛ ሕይወትና ትንሣኤ መሆኑን የምናረጋግጥ እንጂ ባዕድ የምናመልክ አይደለንምና።

በእግረ መስቀል ስንሰግድና ስንሳለም ሞት የማይገባው አምላክ የእኛ ፍቅር አገብሮት በዚህ ዓይነት ሞት መሞቱን እያሰብን ለእርሱም ያለንን ፍቅር ስንገልጽ ነው።

## የመስቀልን በዓል ለምን በመስከረም እናከብራለን

ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ መስቀል ልዩ ተአምራት በመሥራት አይሁድን ያሳፍራቸው ነበር፤ መስቀልን በመንካት፣ ሕሙማን ይፈወሳሉ፤ ለምጻሞች ይነፃሉ፤ ዕውራን ያያሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤ በዚህ ምክንያት አይሁድ ከማፈራቸው የተነሣ ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት፤ ማንኛውም በአካባቢው የሚገኝ አይሁዳዊ የቤቱን ጥራጊ በላዩ እንዲያፈስበት አዘዙና ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ጥራጊ ሲፈስበት ትልቅ ኮረብታ ሆነ።

በዚህ አኳኋን የመስቅሉ ነገር ደብዛው ጠፉ፤ ንግሥት እሌኒ ልጇን ቆስጠንጢኖስን አማክክና ከእሱም ድጋፍ አግኝታ፣ መስቅሉ የተቀበረበት በየት አካባቢ እንደሆነ በአንድ ኪራኮስ በሚባል አረጋዊ ጠቋሚነት አካባቢውን ከተረዳች በኋላ ዕጣን ከእሳት ጨምራ አጨሰችና፣ የዕጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ መስቀሉ ያለበትን ቦታ አመለከተ።

በዕጣኑ ጢስ ምልክትነት ቦታው ተቆፍሮ መስቀሉ መጋቢት አሥር ቀን ከጉድጓዱ ወጣ። የሁለቱም ወንበዴዎች መስቀል አብረው ተቀብረው ስለነበረ በመጀመሪያ የተገኘው የፈያታዊ ዘፀጋም ነበር፤ ተአምር ይሠራል ብለው በድውይም ሆነ በምውት ላይ ቢያኖሩት ምንም የማይሠራ ሆነ፤ የጌታ አለመሆኑ በዚህ በመረዳት እንደ ገና ቁፈራው ቀጠለና የፈያታዊ ዘየማን ተገኘ። በሕሙም ላይ ቢያኖሩት በሽተኛውን ፈወሰ፤ ከምውት ላይ ቢያኖሩት ግን ማስነሣት የማይችል ሆነ። የጌታ አለመሆኑ በዚህ ታውቆ እንደ ገና ቁፈራው ቀጠለ።

በመጨረሻ የጌታችን መስቀል ተገኘ፤ በድውይ ላይ አኖሩት ፈወሰው፤ በምውት ላይ አኖሩት አስነሣው፤ እንደ ፀሐይም አበራ።

ስለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድ መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም፤ «መስቀል አብርሃ፤ ሰገደ ጢስ በጎልጎታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል» በማለት በድጓ የዘመረው።

ታዲያ ይህች የቈስጠንጢኖስ እናት ቅድስት እሌኒ መስቀሉ በተገኘበት በጐልጐታ ቤተ ክርስቲያን በማሠራት በ335 ዓ.ም ታቦቱን አስገብታ ቅዳሴ ቤቱ የተከበረበት በመሆኑ በዚሁ በመስከረም 17 ቀን በየዓመቱ በዓሉ እንዲከበር ተደረገ።

ሁለተኛም ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ የብር ሣጥን አሠርቶ አስቀምጦት የነበረውን መስቀል በ614 ዓ.ም ፋርሶች ወስደውት ስለነበረ ክርስቲያኖቹ ኀርቃልን በመማፀን በ629 ዓ.ም ወደ ቦታው ስለመለሱት በዚያው መጀመሪያ በገባበት በዚሁ ቀን እንዲከበር በመወሰኑ ነው።

በመጨረሻ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት እንዲመለከቱ አንባብያን ይጋብዛሉ።

«ወንድሞቼ ሆይ!! የእኔን ምሳሌነት ለመከተል ተባበሩ፤ የእኛንም ምሳሌነት የሚከተሉትን ሁሉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ ከአሁን በፊት ብዙ ጊዜ እንደ ነገርኳችሁና አሁንም በኀዘን እንባዬን በማፍሰስ እንደምነግራችሁ ሁሉ ብዙዎቹ በአካኼዳቸው የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሁነዋል፤ የእነርሱ አምላክ ሆዳቸው ነው» ፊልጵ.3፥7:9።

ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ሲነገርና በዓሉ ሲከበር የሚያፈዙ ሁሉ ሆዳቸው አምላካቸው መሆኑን መረዳት ይገባል። ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው

አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ኪነ-ጥበብ

## ስደተኞች

(የመጨረሻ ክፍል)

በድንጋጤ በቦዙት (በፈዘዙት) ዓይኖቹ አንድ የሚያስደንቅ ነገር በደብዛዛ ይታየዋል። እየቀረበ እየቀረበ ወደርሱ ሲመጣ። ልቡ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

‹ማ–ር–ቆ–ስ›

አንድ የሚያውቀው የሚወደው ድምፅ ጠራው መንቃትና እንደገና አካባቢውን ማየት ሲጀምር ፊት ለፊቱ ታናሽ እኅቱ ሄለን ቆማለች። ዘላ ተጠመጠመችበት። ዙርያውን ደግሞ የአባትዋ ወታደሮች ከበዋቸዋል።

በክርስትና ጉዞ ሁል ጊዜ ወደ ፊት ብቻ መጓዝ አይቻልም። የፈተናው ብዛት የመከራው ክብደት ሲያይል ሳይወዱ በግድ እንደገና ወደኋላም ይመለሳል። ወደማይወዱት፣ ትተውት ወደሄዱት መንገድ ይገፈተራል። ጉዞውን የሚያረዝመው አንዱ ምክንያትም ይኼው ነው።

ሄለንና ማርቆስ በአባታቸው ወታደሮች ተይዘው፣ በሠረገላ ተጭነው ሌሊትና ቀን በወታደር እየተጠበቁ እንደገና ወደ ምዕራብ እንደገና ወደ ሲረናይካ ወደ ደራጉን አገር ተወሰዱ። መከራ ባይኖር የምናነባበትና የነዳዊትን የነማርታና ማርያምን በረከት የምናገኝበት መንገድ ባልተፈጠረም ነበር። ሥጋ እሺ ብሎ አያነባምና። ሄለንና ማርቆስ ቀኑን ሙሉ በዕንባ ሲራጩ ደረታቸውን እየደቁ ሲያለቅሱ አረማውያኑ ወታደሮች ይገርማቸው ነበር።

ከምላ ቤታቸው ከተከበረ ኑሮአቸው አፈናቅሎ ስደተኝነትን ያስመረጣቸውን የክርስቶስን ፍቅር አያውቁትምና የነሄለንና ማርቆስ ሁኔታ ለወታደሮቹ የጥጋብ ስሜት ነው።

‹እስቲ አሁን ምን ጎደለብን ተብሎ ነው›

‹ተዋቸው ወዳጄ ምነው እኔንም አንቀባርሮ የሚያኖረኝ ባገኘሁ።›

‹ጥጋብ ወደ ረሃብ ይነዳል ይሏል ይኼ ነው።›

ከሠረገላው ዙሪያ የሚጓዙት ወታደሮች የሚሉት ሁሉ ለነማርቆስ ይሰማቸዋል። ግን ጥጋብ ረሃብ፣ ረሃብም ጥጋብ ሆኖ በሚቆጠርባት ዓለም እየኖሩ የክርስቶስን ፍቅር መረዳት ይከብዳልና አላዘኑባቸውም።

‹ወይኔ እሜቴ ሞኒካ› አለና ማርቆስ ተንሰቀሰቀ።

‹ማናቸው እሜቴ ሞኒካ› ሄለን ዓይን ዓይኑን አየችው

‹እኔው ነኝ በደለኛው እኔው ነኝ ተጠያቂው›

‹ማ ር ቆ ስ – ም ን ድ ነ ው የምትለው?›

የእሜቴ ሞኒካን ታሪክ አጫወታት። ሆደባሻዋ ሄለን ጭኖቿ ላይ ተደግፋ እናትሺ ሞተች የተባለች ያህል ነበር ያለቀሰችው ‹ምናለ ለርሳቸው ሲል ቢምረን› በዕንባ በለቅሶ ያበጠው ከንፈርዋ መርገብገብ አቅቶታል።

‹ማርቆስ› አለችው ሄለን

‹ወይዬ የኔ እኅት›

‹ራሴን አዞረኝ›

እንደ ጥንቱ እንደ ልጅነቷ ፀጉሯዋን ያሻሽላት ጀመር። ሰውነቷ ሲተኩስ ሲግል ይሰማዋል። ደነገጠ። እጅዋ ከትከሻው ላይ ተዝለፍልፎ ወረደ። ራስዋን መሸከም አቃታትና ሠረገላው ላይ ተዝለፈለፈች። ማርቆስ ጮኸ። ዙርያውን የነበሩት ወታደሮች ጩኸቱን ሲሰሙ ሠረገላውን አቆሙና ወደነሄለን ሮጡ።

ሄለን ዓይኖቿ ተጨፍነዋል። ትንፋሽዋ የማቆም ያህል ነው ተዝለፍልፋለች። ማርቆስ በድንጋጤ የበረሃ እንጨት መስሏል። ወታደሮቹ ተረበሹ ተሸክመው ከሠረገላው አወረዱና ምንጣፍ አንጥፈው መሬት ላይ አስተኟት የወታደሮቹ አዛዥ ትከሻዋን እየነቀነቀ ጠራት መልስ ቀርቶ መንቀሳቀስ አላሳየችም።

ድንገት ማርቆስ ከደረቀበት ሕይወት ዘራና ‹እኅቴን – እኅቴን እኅቴን› እያለ በዚያ ጭው ባለ በረሃ ለቅሶውን ለቀቀው። ዙርያዋን እየዞረ በላይዋ ላይ እየወደቀ እየተነሣ። አሸዋው ላይ እየተንከባለለ። ብቻዬን ቀረሁ ሄለንዬ ብቻዬን ቀረሁ ...በመንገድ ላይ ብቻዬን ቀረሁ ሄለን – እኅቴ – እናቴ – አባቴ – መካሪዬ...› አታየውም አትሰማውም። መሬት ላይ ተንከባለሎ ወታደሮቹ ሲያነሡት እርሱም የበረሃው አካል መሰለ።

‹ምን ልሁን...የት...ልግባ... ምነው እመቤቴ...ምነው የአንድዬ እናት ሐዘኔን አበዛሽው፣ መከራዬን አበዛሽው እሜቴ ሞኒካ – ምነው በኖሩልኝ አብረውኝ በሆኑ።› በቁሙ ሲያል የወረደ መሰለው። የወታደሮቹ አዛዥ የሚያደርገው ጠፍቶታል። በወታደሮቹ መካከል ክርክር ይሰማል።

‹ምን ብለን ሬሳ ይዘን እንሄዳለን።›

‹እርሱን ገድለን የርስዋን ሬሳ ይዘን እንሂድ ያለበለዚያ መንገድ ላይ መሞቷን መናገሩ አይቀርም።›

‹ሬሳ ይዘን ሄደን ምን ልንል ነው? የአባቷን ፊት ልናይ ነው? በከተማው ገበያ ልንሰቀል?›



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

‹እኔ ምንም ያርጉኝ ምን ሬሳዋን ትቼ አልሄድም›

‹ቀረፈፍ – ተንቀርፈፉ›

‹ይልቅ ጊዜው ሳይመሽ አንድ ነገር እንብል።›

‹ነገርኳችሁኮ እርስዋ ከሞተች እርሱንም ገድለን አጣናቸው ለምን አንልም።›

‹ልክ ነው ሳይሻል አይቀርም። እንሽለማለን ብለን በአንገታችን ሽምቀቆ አናጠልቅም።›

‹እዚህችው እንሚሚታለን እንጂ እርሱን ስትገሉት ዝም ብዩ አላይም›

የወታደሮቹ ክርክር ወደ ጭቅጭቅና ዱላ ቀረሽ ንትርክ እያደገ መጣ። ማርቆስ አሸዋው ላይ ተዘርሯል። የሄለን ትንፋሽ መሰማቱን አቁሟል። ከብዙ ንትርክ በኋላ አንዱ ወታደር ወደ ማርቆስ ሲጠጋ የርሱም ሰውነት ዝሎ ላብ አጥምቆት ተመለከተ። ምግብ ከቀመሰ ብዙ ሰዓታት አልፈዋል። ከዚህ በላይ ደግሞ ቀኑን ሙሉ ሲያለቅስ ነው የዋለው ድካሙና የሐሩሩ ግለት የሞት ያህል ማርቆስን ወስዶታል።

‹እርሱም ወደርሷ እያዘገመ ነው› አለ ወታደሩ። ሌላኛው ወታደር ይህን ሲሰማ ዕንባው ቀደመውና ወደማርቆስ ሮጠ።

በአዛዡ መሪነት ማርቆስና ሄለን አለመገኘታቸውን ለመንገር ተስማምተው ወደ ሲረናይካ ጉዞ ተጀመረ። አንዱ ወታደር ብቻ እያለቀሰ ከማርቆስ አጠገብ ተቀምጦ ቀረ። አዛዡ ሌላ ሬሳ ደግሞ እንዳይወድቅ ስለፈራ ወታደሮቹ ከነርሱ ጋር መሄድ እንዳለበት ያነሡትን ሙግት ገታው።

ፀሐይ በጅብራልተር ኰረብታ ምዕራብ በመጥለቅ ላይ ናት። አካባቢው ራሱ ሞት የወረረው መስሏል። የሚዋደዱት እኅትና ወንድም መሬት ላይ ተዘርረዋል። ያለቅስ የነበረው ወታደር በመንቅሉ የያዘውን ውኃ ከፈተና ማርቆስ ላይ ግማሹን ረበረበው። ጥቂት ቆይቶ ማርቆስ ተንቀሳቀሰ። የወታደሩ ሐዘን ወደ ደስታ ተቀየረ። ዘወር ብሎ ወደ ምዕራብ ሲመለከት ወታደሮቹ በፍጥነት በመራቅ ላይ ናቸው። ፀሐይዋ ደግሞ ልትጠልቅባቸው ነው።

ማርቆስ ተገላበጠ።

ከዚያም ተነሥቶ ተቀመጠ።

ፀጥ ያለውን አካባቢ ሲቃኝ ግር አለውና መሬቱን ተደግፎ ተነሣ። አንድ የተቋጠረ ነገር ከኪሱ ሲወድቅ ወታደሩ ተመለከተና ሮጦ አንሥቶ ሰጠው።

‹እሜ–ቴ–ሞ–ኒ–ካ› ማርቆስ ጮኸ

ወታደሩ ግራ ገባው።

‹ውኃ አለህ?› ማርቆስ ወታደሩን ለመነው።

ከቅድሙ ያተረፈውን ውኃ በመንቅሉ ሰጠው።

ማርቆስ ቋጠሮውን ፈታና ውኃው ውስጥ ሺሮ የመሰለ ነገር ጨመረበት። ከዚያም ወደ ሄለን አመራና አንገቷን ቀና አድርጐ ከንፈርዋን በጣቱ ከፈተና ውኃውን–ጠብ–ጠብ–እያደረገ በአፍዋ ጨመረው። ትንፋሽዋ ትንሽ ትንሽ እንደበፊቱ መሰማት ጀመረ። ማርቆስ ማንጠባጠቡን ቀጠለ። ወታደሩ ደግፎ ይዞለታል። ሰውነቷ ሙቀት ተሰማው። ቆ–ይ–ታ ዓይኗን አስለምልማ ከፈተችው። በመጨረሻም አስታወካት። የተጥመለመለ የተቋጠረ ነገር ቡልቅ – ቡልቅ – እያለ መውጣት ቀጠለ።

ሄለን ነፍስ ዘራች። ጨለማው ያዝ ሲያደርግ ፀሐይዋ ስትጠልቅ በሄለን ላይ ግን ሕይወት ፀሐይ ዘራችባት።

‹እሜቴ ሞኒካ እግዚአብሔር ይስጥዎት›

ወታደሩ ባየው ነገር ሁሉ ተገርሟል። ምን እየተደረገ እንደሆነ አእምሮው መገንዘብ ተስኖታል። ሙተው የነበሩ ሁለት ሰዎች ሕይወት ዘሩ። እንደ ቀድሞ ሕይወት ዘራ ከዚያም ለሌላዋ ሕይወት ዘራባት። ምንድነው?

ማርቆስ ለሄለን መድኃኒቱን ሲያጠጣት ‹እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ› በማለት ደጋግሞ ሲጣራ ሰምቶታል። ‹እግዚአብሔር ምንድነው? ደግሞ ረዳውና ዳነችለት። ከዚያም ተነሥቶ ወደሰማይ አንጋጦ ‹እግዚአብሔር ሆይ ረድተኸናልና አድነኸናልምና እናመሰግንሃለን› አለ። እግዚአብሔር የሰማይ አምላክ ነው? ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ምንድናቸው? ለምንስ ስደትን መረጡ?›

‹ማርቆስ› አለው ወታደሩ ሄለንን ደግፎ እንደተቀመጠ ጠጋ ብሎ። ‹ሁኔታው ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም። ለመሆኑ እግዚአብሔር ምንድነው? ለምንስ እናንተ መሰደድን መረጣችሁ?›

ሄለን ቀና ብላ ትመለከታቸዋለች። ማርቆስ ረጋ ብሎ ከመጀመርያ ጀምሮ የሆነውን አስረዳው። ስለ ክርስትና ሕይወት አስተማረው። ወታደሩ እየደጋገመ ራሱን ይነቀንቃል። በመጨረሻ:-

‹አሁን የት ለመሄድ ነው የምትፈልጉት?› አለና ጠየቀው

‹ወደ ምሥራቅ›

‹ምሥራቅ ማለት የት ነው?›

‹ወደ ኢየሩሳሌም›

‹ኢየሩሳሌም ማለት ቅድም ክርስቶስን ሰቀሉባት ያልከኝ ሀገር ናት?›

‹አዎን? ግን እዚያ ብቻ አይደለም ሌላም ኢየሩሳሌም አለች።›

‹ይህ እግዚአብሔር ያልከው ለዚህ ነው ከእናንተ ጋር ያቆየኝ›

ሌሊቱ የሰላም ሌሊት ሆነላቸው። የወታደሩን ስንቅ ተቃምሰው አደሩ። በማለዳ ለጉዞ ሲነሡ ወታደሩም አብሯቸው ለመሄድ ታጥቆ ተነሣ። ሌሊት የክርስቶስን ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅርና ትናንት ወታደሮች ጓደኞቹ ሲባባሉ የነበረውን እያነፃፀረ ‹ሰው ማለት ከንቱ ነው ልግደልና ልኑር የሚል። እግዚአብሔር ግን ሙቶ አዳነን› እያለ ሲገረም ነበር ያደረው። ‹ከዚህ የበለጠ ለሰው ልጅ የሚገባ ሕይወት የት አለ?› አለው ማርቆስን በጠዋት። መንገዱ አስቸጋሪ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

መሆኑን ሄለን ስትነግረው ‹እናንተን ያስቻለ አምላካችሁ እኔን አያስችለኝም?› አላት ፈገግ ብሎ።

እናም ጉዞ ተጀመረ። ወደ ምሥራቅ።

እየተማማሩ እየዘመሩ እያረፉ እየተነሡ።

ማርቆስ እሜቴ ሞኒካ ትዝ እያሉት አንዳንዴ ሊያለቅስ ይዳዳውና ሄለንና ወታደሩን ላለማስጨነቅ ሲል ይውጠዋል። ሌሊትና ቀን ያለማቋረጥ ወታደሩ በያዛት ገንዘብ ስንቅ በየመንደሩ እየሸመቱ ወደ ኢየሩሳሌም። በታዕታይ ግብፅ በኩል አድርገው ወደ ጋዛ ዘለቁ። አሁን ምዕራቡ እየራቀ ነው አንድ ሰው በማዶ ከፊት ለፊቱ በቅሎ አስቀድሞ ሲጓዝ ይታያል። በቅሎዋ ሳጥን የመሰለ ነገር ተጭናለች። የሚጓዘው ረጋ ብሎ ሳጥኑን ደግፎ ነው አንድ የበረሃ ቁጥቋጦ ሲያገኝ በቅሎዋን እንዳቆመ ዐረፍ አለ።

እነ ማርቆስ ወደ ሰውዬው ሲቃረቡ ማርቆስ መጀመርያ ቆመ። ከዚያም ሮጦ አቀፈውና እየተላቀሱ ተሳሳሙ። ወታደሩና ሄለን ግራ ተጋብተው ቆመዋል።

‹ሄለን፤ እኔንና እሜቴ ሞኒካን ያስጠጋን ደግ ሰው ይህ ነው› አላት ማርቆስ። ሄለን ትከሻውን ሳመችው ወታደሩም እንዲሁ።

ከዛፍዋ ሥር ዐረፍ አሉና ስለአመጣጡ መንገደኛው ያጫውታቸው ጀመር። ‹እሜቴ ሞኒካ ከነ አንተ ከተለዩ በኋላ ደስተኛ አልነበሩም። እህል አልበላ አላቸው። የዘወትር ሥራቸው ዕንባ ብቻ ሆነ። ‹ልጄን ነጠቅከኝ› እያሉ ዘወትር ሲያለቅሱ ያድሩ ነበር። አንድ ቀን ሌሊት ተነሥተው ቀሰቀሱኝና ‹ነገ እኔ የዓለሙን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ። መቃብሬ ኢየሩሳሌም ነው። ካረፍኩ በኋላ ከማርቆስ ጋር እገናኛለሁ። አምላኬ ለዚህ ቃል ኪዳን ሰጥቶኛል። አደራ ሬሳዬን ወደ ኢየሩሳሌም ውሰድልኝ› አሉኝ። እኔም ደንግጬ አጠገባቸው በመቀመጥ አለቀስኩ። እሜቴ ሞኒካ ብዙ ነገር አስትምረውኛል። ሕይወቴን ለውጠዋታል። ከጊዜያዊነት ወደ ዘላለማዊነት። ላጣቸው አልፈልግም ነበር።› አለና መንገደኛው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ከዚያም ከማርቆስ ጋር ተያይዘው ተላቀሱ። «ነገር ግን እርሳቸው እንዳስተማሩኝ በወዲያኛው ዓለም እንገናኛለን። እግዚአብሔር እንዳልጠፋብኝ እናንተን ሰጠኝ» አለና ዝም አለ።

‹ታድያ ይኼ የእሜቴ ሞኒካ አስከሬን ነው?› አለው ማርቆስ ተገርሞ።

‹አዎ! አደራ አለብኝ። ከበቅሎ በቅሎ እያፈራረቅኩ ረጋ ብዬ በመጓዝ እዚህ አድርሼዋለሁ። በየመንገዱ ብዙ ፈተና ነበረብኝ ነገር ግን ቃል ኪዳኑን የማያጥፍ አምላክ ረዳኝ›

ማርቆስ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ሳጥኑን ሳመና

‹እሜቴ ሞኒካ ቀደሙን። ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ ያለው ቃል በዚህ ተፈጸመ አለ።›

‹ጉዞዋችን የሚደንቅ ነው ፊተኞችና ኋለኞች ሆነን ሁላችንም ወደ አንዲት ሀገር እንጓዛለን። መንገዱ ወጣ ገባ ነው ወደፊት ሙሄድ፤ ወደ ኋላ መጐተት፤ መከበብ፣ መያዝ፣ መታሠር፣ መራብ፣ መሞት፣ መነሣት። ከየአቅጣጫው መሰባሰብ፤ በአንዲት መንገድ መጓዝ፤ አንዲት ሀገር ለመግባት:- አይ ክርስትና› አለች ሄለን።

‹የእግዚአብሔር ረድኤት ባይኖር ኖሮ ማንም ዲያብሎስን ማሸነፍ ባልቻለ ነበር። የሰይጣን ፈተና ባይኖር ደግሞ ማንም የእግዚ.አብሔርን ቸርነት አይረዳም ነበር።›

እኔ ብቸኛ ስደተኛ ነበርኩ – በሲረናይካ–ሄለንን አስከተልኩ እኛ ደግሞ እሜቴ ሞኒካን፣ እሜቴ ደግሞ ባለመድኃኒቱን አመጡ። እኔና ሄለን ወታደራችንን ጨመርን። ሐዋርያትም ዓለም ያሳደደቻቸው ስደተኞች ነበሩ፣ እኛን ተኩ። እኛም ሌላውን። ክርስትና የቀደሙት ስደተኞች ኋለኞችን የሚያስከትሉበት መንገድ ነው። አሉና ጉዞዋቸውን ቀጠሉ። ከየሀገሩ የመጡ ሌሎች ስደተኞችም ወደመንገዱ እየገቡ ናቸው። ✣

## ከቅዱሳን ሕይወት

አንድ በጸሎቱ የሚመካ ጸዋሚ ተሐራሚ ባሕታዊና አንድ ታዛዥ ረድእ በአንድ ገዳም ይኖሩ ነበረ። ሁለቱም በቅተዋል። የሁሉንም መብቃት ማኅበረ መናንያኑ ያውቃል። ነገር ግን ይህ ረድእ ይበልጥ ወይስ ይህ ባሕታዊ? ሲሉ አበምኔቱ ሰምቶ «አንተም ረድእ፣ አንተም ባሕታዊ ለበዓል የምንጐዘጉዘው ቄጠማ አምጡ» ብሎ አዞዎች ካሉበት ባሕር ሰደዳቸው። ታዛዡ ረድእ አዞዎችን እየተራመደና እየጠቀጠቀ ከመሐል ገብቶ የነቅል ጀመር። ያ ባሕታዊ ግን ከዳር ቁሞ ሲመለከት «ምነው ወንድሜ ከመሐል ገብተህ አትነቅልምን?» ብሎ ረድኡ ጠየቀው። ባሕታዊውም «አንተ ከደረስህበት ማዕረግ ገና አልደረስኩምና እባክህ ተወኝ? አለው። ፊልክስዩስ 84። «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ።» ሮሜ.4፥20።

✣ ✣ ✣

## መታዘዝ ከመሥዋዕት

አንድ ረድእ መምህሩ ልኮት ሲሔድ በመንገዱ ምእመናን በሰማዕትነት ሲያልቁ አገኘ። ‹ከዚህ የበለጠ ምን አለ› ብሎ በሰማዕትነት ሙቷል። ከመከራው የተረፉ ክርስቲያኖች ዐፅመ ሰማዕታትን ሰብስበው በሳጥን አድርገው ከቤተ እግዚአብሔር አገቧቸው። ከነዚህ መካከል ግን የዚያ ረድእ አፅም ከሳጥኑ ወጥቶ ወድቆ ተገኘ። በሳጥን አኑሮት የነበረው ክርስቲያን ሳያገባው የቀረ መስሎት በድጋሚ አግብቶት ሄደ። በነጋታውም ቢሔድ እንደዚያው ወጥቶ ወድቆ አገኘው። ጌታ አልፈቀደለት ይሆንን ብሎ በጸሎት ቢጠይቅ «መፍቀድስ ፈቅጄለታለሁ ነገር ግን ፍቅር ጐድሎበታል ከመምህሩ አልተሰናበተምና ለመምህሩ ንገረው» አለው። ያም ክርስቲያን ለመምህሩ ሔዶ ቢነግርለት «ወደ በለጠ ቢሔድ ፈቅጄለታለሁ» አለው። ተመልሶ ወደ አፅሙ ቢሄድ ከሳጥኑ ውስጥ ገብቶ አገኘቶታል።

«ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።» 1ቆሮ.13፥3

ከፍቅረ ሥላሴ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

የመጽሔታችን አንባብያን በአ ዲሱ ዓመት ዋዜማና ማግሥት ይልኩልን የነበሩት ደብዳቤዎቻቸው አብዛኞዎቹ ስለቤተክርስቲያናችን የዘመን አቈጣጠር ታሪክ፣ ጥቅምና ሥርዓት እንዲሁም ከአውሮፓውያን ጋር ያለው ልዩነት ምን እንደሆነና እንዴት ሊከሰትም እንደቻለ እንድናስረዳቸው ነበር።

የዘመን አቈጣጠር ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን የቻለ የጥናት መስክ (field of study) ነው። ባሕረ ሐሳብ ይባላል።

## የዘመን አቈጣጠር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ትምህርቱ ሰፊና ጥልቅ ነውና። የሀ ታላቅ ጥበብ ቤተ ክርስቲያናችን የሥልጣኔ መሠረት የዕውቀት ምንጭ መሆንዋን የምንመሠክር ኢትዮጵያ ውያንን ሁሉ የሚያኰራ ሀብት ነው።

በመሆኑም ለአንባብያን ጥያቄ ትኲረት በመስጠት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኰ መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁንን አነጋገርን። መልአከ ሰላምም ጊዜያቸውን ሰውተው የአንባብያንን ጥያቄ ሁሉ በሚገባ አገላብጠው ተገቢውን መልስ ስለሰጡን እግዚአብሔር ረዥም ዕድሜ ከጤንነት ጋር ይስጥልን እያ ልን በአንባብያን ስም እናመሰግና ቸዋለን።

ሐመር – የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ምንጩ ምንድን ነው?

መልአከ ሰላም – የኢትዮጵያ የዘመናት አቆጣጠር መሠረቱ፣ ምንጩ የጥንቱ የግብፃውያን አቈጣ ጠር ሆኖ በኋላ በነዮሐንስ መደብር፣ በነድሜጥሮስና በነ አቡሻህር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና ከሌሎች እየተ ነፃፀረ የመጣው የ«ዩሊየስ ካላንደር» በመባል የሚታወቀው ነው።

ሐመር – የአመጣጥ ታሪኩን ቢገልጡልን?

መልአከ ሰላም – የአመጣጥ ታሪኩን አጠር ባለ መልኩ ለመግለጥ ግን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት 4000 ዓመት ከነበረው የግብፃውያን አቆጣጠር ተነሥቶ የመጣ ነው። ከዚያ በኋላ ይኸው አቈጣጣር በ45 ዓ.ዓ ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ በእስክንድርያ በዩሊየስ ቄሣር ዘመን ከ365 ቀናት ጋር በዓመት 6 ሰዓቶች (15 ኬክሮስ) ተጠራቅመው በየ4 ዓመቱ 24 ሰዓቶች እንደሚገኙ ታውቆ ቀመሩ ተስተካክሎ መሥራቱን ቀጠለ። ስሙም የ«ዩሊየስ ካላንደር» በመባል የታወቀ ሆነ። ከዚህ በኋላ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባዔ በተመረመረ ጊዜ በየ128 ዓመት 1 ቀን ወደ ኋላ እንደ ሚቀር ታወቀ። ይህን አስተካክሎ እንዲሠራበት ለማድረግ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓል በበልግ (በፀደይ) ወር ጨረቃ ሙሉ ሆና የቀኑና የሌሊቱ ሰዓት እኩል ከሚሆንበት ዕለት ቀጥሎ እንዲከበር፣ ነገር ግን ባጋጣሚ የአይሁድ ፋሲካ በዓል በዚህ ዕለት ቢውል ከዚያ ቀጥሎ በሚኖረው እሑድ እንዲከበር ተወሰነ። የአይሁድ ፋሲካ በኒሳን (ሚያዚያ) በተከበረ በ3ኛ ቀን የመጀመሪያው የትንሣኤ በዓል ተከበረ። የአይሁድ ፋሲካ ጌታ የተሰቀለበት በርባን የተፈታበት ነበር።

በዚሁ ድንጋጌ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የትንሣኤን በዓል በተመሳሳይ ዕለት ሲያከብሩ እስከ 1582 ዓ.ም ድረስ ቆይተዋል። በዚሁ ዓ.ም እንደገና በሮሙ ጎርጎርዮስ 13ኛ ጊዜ ከኒቂያው 10 ቀኖች ይጎድ ሉታል በሚል ሰበብ ሌላ መንገድ ተፈጠረ። ይህም በእያንዳንዱ 128 ዓመት 1 ቀን ይጎድላል ለማለት ነው።

በዚህ የተነሣ ሌላ ውሳኔ ሲሰጥ የጥንቱ (የመጀመሪያው) ልክ ነው። የትንሣኤን በዓል ከነበረው (ከኒቅያ ውሳኔ) አናዛንፍም ብለው በፀኑትና አዲስ ስሌት ባመነጩት በጎርጎርዮ ሳውያን አቆጣጠር ተቀባዮች መካከል ልዩነት ተፈጠረ። በዚህም የተነሣ ጉዳዩ ሁለት መሥመሮች ይዞ መጓዙን ቀጠለ። በመጨረሻ ደግሞ (እ.ኤ.ዘ.አ 1923) በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡ የቢዛንታይን መለካውያን ኦርቶዶክ ሳውያን የዩሊዮስንና የጎርጎርዮስን ካላንደር መርምረው 13 ቀኖች ያጎድላል ብለው ሦስተኛ አቆጣጠር ስለፈጠሩ ለዘመናት አቆጣጠር እንደ መሠረት ድንጋይ ሆኖ የተቀመጠው የትንሣኤ በዓል በሦስት የተለያዩ ዕለታት መከበሩን ቀጠለ።

በዚህ ሁኔታ የጥንቱ ውሳኔ ፈር እየለቀቀ እንዲሄድ በመደረጉ

- የዩሊዮሳውያን ካላንደር
- የጎርጎርዮሳውያን ካላንደር

የቁስጥንጥንያ የቀን አቆጣጠር እየተባለ በልዩነት ቀረ። ኢትዮጵያ ግን የምትከተለው ያንኑ የጥንቱን ነው። በዚህም ትኮራበታለች እንጂ አታፍርበትም። ብቻዋንም አይደ ለችም። በዚሁ አቆጣጠር የሚሠሩ አገሮች (አብያተ ክርስቲያናት) አሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊነትና የሀገራችን ሥልጣኔ ቀዳሚነትም የሚታየው ከተለያዩ ገጾች ስለሆነ ይህም አንዱ የጥንታዊነታችን ማረጋ



©ማኅበረ ቅዱሳን    www.eotcmk.org

ገሜ ነው። ሌሎችም ቢሆኑ ማን ከማን ያንሳል? በሚል ዘየ በየዘመኑ የተለዋወጠውን (ያውም መቶ በመቶ የተጣራና ከጥንቱ የሚለይበት ፍጹ ምነት አለው ሊባል የማይችለውን) ከመከተል የጥንቱን ይዞ መጓዙ አማራጭ የሌለው በመሆኑ ቢከተሉት መልካም ነበር።

ሐመር – ከሌሎች ሀገሮች አቈ ጣጠር ጋር ያለው ዝምድናና ልዩነትስ ምንድን ነው?

መልአከ ሰላም – ከሌሎች ሀገ ሮች አቈጣጠር ጋር ያለው ዝምድና ያው ከመሠረቱ በተመሳሳይ ሁኔታ አብሮ የመጣ መሆኑ ነው ልዩነቱም ከላይ በተራ ቁ.2 የተመለከተው ነው። በዘመን መለወጫ፣ በልደትና ትንሣኤ በዓላት አከባበር፣ በየዓመቱ መጨረሻ ተጠራቅመው በሚገኙ ቀኖች ጭምር እንለያያለን። ቀደም ሲል የጨረቃን አቈጣጠር ይከተል የነበረው የጥንቱ የግብፃውያን አቆጣጠር ከብዙ ጥናትና ምርምር በኋላ የጨረቃን አቈጣጠር ትቶ የፀሐይን አቈጣጠር በሚገባ አዘጋጀ።

በፀሐይም አቈጣጠር ስሌት አንድ ዓመት 30 ቀኖች ያሏቸው 12 ወራ ትንና 12ቱ ወራትም 365 ቀኖችን የያዘ ነበር። ኋላም ምርምሩ እየቀጠለና እየተጠራ የወሩ ቀኖችና የዓመቱ ወሮች ቁጥር ሳይጨምርና ሳይቀንስ የዓመቱ 6 ቀኖች ያሉት ትንሽ 13ኛ ወር ሲኖረው የሮማውያን አቈጣጠር ግን ከዚህ የሚለየው ይህን 365 ወይም 366 ቀኖችን በዓመቱ 12 ወራት ውስጥ አጠቃልሎ ወሮቹ በ30፣ 31፣ 28፣ እና 29 ተዛንፈው እንዲገጣጠሙ በማድረጉ ነው።

ሐመር – የዘመን አቈጣጠር ከኢ ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሕል ሥር ዓትና እምነት ጋር ያለው ግንኙነትና ትርጉም ቢብራራልን?

መልአከ ሰላም – የዘመን አቈጣጠር ምርምር፣ ጥናትና ስሌት፣ ሥርዓትና ድንጋጌ በአመዛኙ በቤተ ክርስቲያን ምሁራን የተዘጋጀ በመሆኑ ከሃይማኖት ትምህርት፣ ትውፊትና ሥርዓት ጋር በብዙ መልኩ የተያያዘ ነው። የባህልና የምሥጢራዊ ሂደት ገጽታም አለው። በየዘመኑ እንደነ በረው ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን የሚገኙ (የተገኙ) የሥልጣኔ፣ የትምህርትና የምርምር ውጤቶችን የመመንዘር፣ የመንቀፍና የማጥላላት ጠባይ በጊዜያችንም ያለ ቢሆንም፣ ባለብዙ ዘርፍ ከሆነው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የዕውቀትና የጥበብ ፍሬ አንዱ የዘመን አቈጣጠር ሥርዓትና ድንጋጌ ነው። የዘመን አቈጣጠር ከቤተክርስቲያን ባህል፣ ሥርዓትና እምነት ጋር መያያዝ ብቻ ሳይሆን የባለቤትነትም ባሕርይ የሚንፀ ባረቅበት ነው። በርግጥ የአንድ ሀገር ወይም በተመሳሳይ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ግንኙነት ያለው የዘመን አቈጣጠር ይህን ድንጋጌ የተቀበለው የማኅበረሰብ አባል ሁሉ በተፈጥሮ



ሕግ ክረምት ክጥቢ፣ በጋ ከበልግ የሚለዋወጡበትን ጊዜውንና ወቅቱን በማገናዘብ እንቅስቃሴውን የሚመ ራበት የጊዜ መሥፈርት ቢሆንም በዚሁ የጊዜ መለኪያ ዑደት (ዙረት) ውስጥ የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ከጊዜው መሥፈርት አኳያ በራሷ ክልል የምትከተለው መንገድ አላት። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ አጠቃላይ የክርስ ትናው እምነትና ትምህርት፣ የሥነ ፍጥረት እንቅስቃሴና ሂደት፣ የሰማያውያን አካላት አገልግሎት ምሥጢራዊ ገጽታ፣ የዜማው፣ የመልክዐ ምድር የአየር ጠባያትና ከሰው ጋር ያለው የሕይወት ትርጉም ሁሉ የሚገለጸው ከዘመናት አቈጣጠር ጋር በተያያዘ መልኩ ስለሆነ የላቀ ዝምድና አለው። የቅ/ያሬድን የዜማ አከፋፈል ስልትና ሥርዓት ሲመለ ከቱት ከወቅቱ ጋር እንደሚስማማ ኾኖ የተዘጋጀና ከዘመን አቈጣጠር ሂደት ጋር የተቀናበረ ኾኖ ይገኛል። የበዓላትና አጽዋማት ዐዋጆች ሁሉ የሚወጡት ከዘመኑ አቈጣጠር ጋር በተቀመረው ድንጋጌ ነው። የዓመቱ የምድር ፍሬ እንዲባረክ፣ እንዲበዛና ለተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ በሚበቃ ሁኔታ እንዲመገብ ጸሎትና ቡራኬ የሚቀርበው የዘመን አቈጣጠር ውሳኔና ዐዋጅ በሚነገርበት በዘመን መለወጫ (በአዲስ ዓመት መጀመሪያ) ዕለት ነው።

ሐመር – ስለአራቱ ወንጌላው ያን፣ አሰያየም ምሳሌያቸውና ከወ ቅቶች (መኸር፣ ፀደይ፣ በጋ፣ ክረ ምት) ጋር ያላቸው ግንኙነት፣

መልአከ ሰላም – ‹ዓመተ ዓለም ዓመተ ኩነኔ› በመባል ይታወቅ የነበረው የብሉይ ኪዳን ዘመን አልፎ ‹ዓመተ ምሕረት› የተባለው ዘመን ሲተካ የዘመናቱም ስያሜ አብሮ ተለውጧል። በኄኖክ መጽሐፍ አቆጣ ጠር ዓመታቱ ሄልሜሌክ፣ ምልኤል፣ ናርኤል፣ ብርኤል በሚባሉ ከዋክብት ይጠራ ነበር። እነዚህ ከዋክብት የፀሐይን ዑደት እየተከተሉ ዓለምን ሲመግቡ ኖረዋል። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን በኋላ ግን ዘመኑ በአራቱ ወንጌላውያን በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ይለወጣል፤ ይፈራረቃል። (የዚህን ሁሉ ድንጋጌና ሥርዓት በዮሐንስ መደብር፣ በአቡሻህርና በድሜጥሮስ የሀሳበ–ዘመን መጻሕፍት ይመለከቷል) ያረጀው ያለፈበትና አዲሱ የተተካበት የሕይወት ድንበር የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ስለሆነ ዘመናቱ በወንጌላውያን የተሰየሙት ወንጌላውያኑ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ (ሥጋዌ) ካስተማሩትና ከጻፉት ቃለ ወንጌል አኳያ የሚመሰጠር ትርጉም ያለው ነው። ከዚህም ጋር ወንጌላውያኑ የሚታወቁባቸው ስዕላዊ ገጽታዎች አሏቸው:-

1. ማቴዎስ ሀ. በገጸ ብእሲ (በሰው መልክ) ይመሰላል። ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም እያለ ከዳዊት ከአብርሃም ዘር በሥጋ የተወለደውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምድራዊ ልደቱን ስለሚጽፍ፣

ለ. በፀደይ ይመሰላል፣ ፀደይ ከ4ቱ ባሕርያት የመሬት ጠባይ የሚ ገለጽበት ወርኃ ዘር ነው። ወንጌላዊው ማቴዎስም ምድራዊ ልደትን ይናገ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ራል፤ ምሳሌ ዘርዕን (የዘርን ምሳሌ) ጽፏልና።

2. ማርቆስ ሀ. በገጸ አንበሳ ይመሰላል፤ በትምህርቱ አጋንንትን፣ መናፍቃንን (ወላዋዮች፣ ተጠራጣሪ ዎችን) ያስደነግጣል፤ ጣኦታትን፤ ይሰብራልና።

ለ. በክረምት ይመሰላል ክረምት የዝናም፣ የውኃ ጊዜ ነው እሱም ስለጥምቀት አብዝቶ ጽፏልና ነው።

3. ሉቃስ ሀ. በገጸ ላሕም (እን ስሳ) ይመሰላል፤ ሥጋውን ደሙን ለዓለም ሕይወት፣ መድኃኒት አድርጎ የሰጠ የወልደ እግዚአብሔርን ንጹሕ መሥዋዕትነት (በንጹሕ ፍሪዳ) አምሳል ገልጸ ምሳሌውን ጽፏል፤ ተረጉሟል።

ለ. መፀው ምሳሌው ነው፤ መፀው ወርኃ ነፋስ ነው። በአምሳለ ነፍስ የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስን ነገር ይናገራልና። መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ...እያለ የሥጋዌን ነገር ጽፏልና።

4. ዮሐንስ ሀ. በገጸ ንስር ይመሰ ላል። ንስር በእግር ይሸከረከራል፣ በክንፍ መጥቆ ይበራል። እሱም እንደሌሎቹ ወንጌላውያን የጌታን ከሰማይ መውረድ ይናገራል፣ በክንፍ እንደመብረር አካል ከህልውና ተገልጾለት፣ ንጽሐ ልቡና፣ ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ተሰጥቶት የቃለ እግዚአብሔር ወልድን ነገር ‹ቀዳ ሚሁ ቃል...ሥጋ ኮነ ወኀደረ ለዕሌነ› ብሎ ጽፏልና።

ለ. በሐጋይ በጋ ይመሰላል። በጋ ወርኃ እሳት የሙቀት ጊዜ ነው። እርሱም መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል ‹ቀዳሚሁ ቃል› እያለ ጽፏልና ነው። እነዚህ የሰው፣ የአንበሳ የላምና የንስር መልክ የተሰጣቸው ወንጌላውያን የልዑል እግዚአብሔርን የጌትነቱን ዙፋን (መንበር) እንደ ተሸከሙ ኾነው በሚታዩ፣ እሱ በወደ ደው ኀብር በሚገለጽባቸውና በጸጋ በሚያድርባቸው አራት ፀወርተ መንበር (ኪሩቤል) አኳያ የተያያዘ ምሥጢራዊ ትርጉም አላቸው። ሕዝ.1፥5–11።

ሐመር – ወቅቶቹም ከመንፈሳዊ ሥርዓት (ቅዳሴ፣ ማኅሌት፣ መዝሙ ርና ትምህርት) ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ቢገልጡልን?

መልአከ ሰላም – በቤተ ክርስ ቲያን ሥርዓትና ትምህርት በተለይም ቅ/ያሬድ በግዕዝ፣ በዕዝልና በዓራራይ ቃኝቶ ያዘጋጀውንና ያቀናበረውን የዜማ ስልቱን ከዓመቱ ክፍላተ አውራኅ የአየርና የመልክዓ ምድር ጠባይ አኳያ አስማምቶ የደረሰውና ያዘጋጀው ስለሆነ መዝሙሩ፣ ቅዳሴው ምንባቡና ትምህርቱ ሁሉ ከዘመናቱ ጋር በትርጉምና በምሥ ጢር ጣፍጦ ተዛምዶ፣ ተዋሕዶ የተዘጋጀ ነው።

ሐመር – የኢትዮጵያ የልደት በዓል ለምን ታኅሳስ 28 እና 29 ይከበራል?

መልአከ ሰላም – የጌታችን የኢ. የሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት በኢት ዮጵያ በታኅሣሥ 28 እና 29 የሚከበረው ከላይ በዘመን አቆጣጠር ሂደት እንደተገለጸው በየዓመቱ መጨረሻ 5 ቀን የምትሆነው ጳጉሜ በየ4 ዓመቱ 6 ስለምትሆን በወንጌላዊ ዮሐንስ ግን በ29 ይውላል። የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ይህ ነው። ጥንተ ልደቱን (29) መልቀቅ የለበትም የሚሉም አሉ።

ሐመር – በኢትዮጵያ አቈጣጠር ጌታ ከተወለደ 1987 ዓመት ነው በአውሮፓ ደግሞ 1996 ዓመት ነው ይህ ልዩነት እንዴት ተከሰተ? ትክክለኛው በማስረጃ ተደግፎ ቢቀርብልን?

መልአከ ሰላም – አዎ የኛንና የምዕራባውያንን ዘመን አቈጣጠር በ7 ወይም በ8 ዓመታት እንዲለያይ ያደረገው መሠረቱ ያው የቀን አቈጣ ጠራችን ልዩነት ነው። ስለጌታችን የልደት ቀን በተለያዩ ቀናት መታሰብ በኛ በኩል የሚሰጡ ምክንያቶች አሉ።

በምዕራባውያንና በኢትዮጵያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በተለያዩ ቀኖች እንዲከበር ያደረገው ያው የዘመናት አቈጣጠር መሠረታዊ ልዩነት መሆኑ ይታወቃል። የኛ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የቀን ልዩነት መሠ ረታዊ መነሻ የምታደርገው መጥምቁ ዮሐንስ የተፀነሰበትን ዕለት ነው።

ካህኑ ዘካርያስ የዮሐንስን መወ ለድ ብሥራት የሰማበት ዕለት በኦሪቱ እንደ ተጻፈው «በዓለ ሥርዓት» በመባል የሚታወቀው ነው። በኦሪቱ ሕግ «በሰባተኛው ወር ከወሩም በ10ኛው ቀን ራሳችሁን አስጨን ቁት፣ ያገር ልጅ፣ በናንተ መካከል የተቀመጠ እንግዳም ሥራ ሁሉ አት ሥሩበት በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢ አታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ፤ ታላቅ ሰንበት ይሆንላችኋል፤ ራሳችሁን ታዋርዳላችሁ የዘለዓለም ሥርዓት ነው። የሚቀባውም ካህን በአባቱ ፈንታ ካህን ሊሆን የሚካነው ካህን ያስተሥርይ» ዘሌ.16፥29–34፤ 23፥27–32፤ ዘኍ.29፥7–11።

ይህን በዓል ለማክበር መለከት የሚነፋበት ዐዋጅ የሚነገርበት፣ የተቀደሰ ጉባዔ የሚደረግበት፣ ከበዓ ሉም በኋላ ከአሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ ሳምንቱን ሙሉ የሚከበር የተቀደሰ ጉባዔ ነበር።

ካህኑ ዘካርያስ የልጁ የዮሐንስን ልደት ብሥራት ከመልአኩ የሰማው ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለቤተ እሥራኤል ሥርየት ወደቤተ መቅደስ በገባበት ዕለት ነበር። ዘሌ.16፥17፣ ሉቃ. 1፥8–10 ቁ.21 ይህንኑ ከጥንታ ውያን አበው እነዮሐንስ አፈወርቅ የሉቃስን ወንጌል ሲተ ረጉሙ ሰፋ አድርገው ገልጸውታል።

በታሰሪን (ጥቅምት 10) የሚከ በረው ይህ በዓል የነበረው በኢትዮጵያ አቈጣጠር መስከረም 27 ነው። የ5500 ዘመን መጨረሻ ዓመተ ዓለም በሊቃውንት በተሰጠው ስያሜ መሠረት ዘመነ ዮሐንስ ነው። ቅዱስ ያሬድ በድጓውና ሌሎችም ሊቃው ንት እንደገለጡት ዮሐንስ የተፀነሰው ከሁለት ቀን በኋላ ነው። (መስከረም 27+2=29) እንግዲህ ከፅንሰተ ዮሐንስ (መስከረም 29) ከ6 ወራት በኋላ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትፀንስ አበሠራት፣ ይህም በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መጥምቁ ዮሐንስ ከተፀነ ሰበት ዕለት ተቈጥሮ መጋቢት 29 ቀን ነው። ከመጋቢት 29 እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን 9 ወር ከ5 ቀን ይሆናል ቀኖቹም በዝርዝር 275 መሆናቸው በቍጥር ስሌት ሊደረስበት የሚችል ነው። (9 ወር ከ5 ቀን ኢሳ.9፥6፣ ገላ.4፥4) ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅዱስ ድሜጥሮስ ተካሌ ወይን

በ119 ዓ.ም ተወለደ ለእናትና ለአባቱ አንድ ልጅ ከመሆኑ የተነሣ የ15 ዓመት ወጣት እያለ በጋብቻ ሕግ እንዲወሰን ጠየቁት። ድሜጥሮስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ፍላጎቱ የድንግልና ሕይወት ስለነበር የወላጆቹን ፈቃድ ሳይቃወም ከወጥመዱ እንዴት ማለፍ እንደሚችል ማሰብ ጀመረ።

በመጨረሻም የእናትና የአባቱን ፈቃድ መፈጸም «እናትህንና አባትህን አክብር» የሚለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ማክበር እንደሆነ ስለተሰማው የወላጆቹን ሐሳብ ተቀብሎ ለጋብቻ ተዘጋጀ። ነገር ግን ለድሜጥሮስ የታጨችለትም ልጅ እንደርሱ በድንግልና ለመኖር የወሰነችና የወላጆቿን ቃል ለማክበር ብቻ ለጋብቻው የተዘጋጀች መሆንዋን ሲያውቅ እግዚአብሔር የለመነውን እንደሰጠው አመነ።

ሁለቱ ወጣቶችም በትዳር ዘመናቸው ሁሉ ያለ ተራክቦ በድንግልና ለመኖር ተስማሙ።

ድሜጥሮስና እጮኛው በአንድ ማዕድ እየበሉ፣ በአንድ ቤት እየኖሩ፣ በአንድ አልጋ እያደሩ በእግዚአብሔር መልአክ ጠባቂነት ለ49 ዓመታት ያህል ያለተራክቦ በድንግልና ኖሩ። በአካባቢው የነበሩ ሰዎችም በሁለቱ መካነንት የተነሣ ልጅ ለማግኘት ያልታደሉ ስለመሰላቸው ያዝኑባቸው ነበር።

ድሜጥሮስ የወይን ገበሬ ነበረ። ከዕለታት አንድ ቀንም በወይን እርሻው መሐል ሲመላለስ ያለ ጊዜው ያፈራ ሰባት የወይን ዘለላ ተመለከተ። በእግዚአብሔር ሥራ የተደነቀው ድሜጥሮስ የወይን ዘለላውን ቆርጦ ወደ ባለቤቱ ወሰደው። «ይህ የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ ነውና የሚገባው ለፓትርያርኩ ነው» በማለት ወደ አቡነ ቶርያኖስ ዘንድ እንዲወስደው ተማከሩ።

የእስክንድርያ 11ኛ ፓትርያርክ የነበረው አቡነ ቶልያኖስ በዕድሜ ገፍቶ ነበርና ጊዜው ደርሶ ሲያርፍ በመንበሩ የሚተካውን እግዚአብሔር ይገልጥለት ዘንድ ይጸልይ ነበር። ድሜጥሮስ የወይኑን ዘለላ ባገኘባት ዕለት አባ ቶልያኖስ ራእይ አይቶ ነበር። የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ መጥቶ «ካንተ በኋላ የሚተካው አባት ነገ ሰባት የወይን ዘለላ ይዞልህ ይመጣል» በማለት ነገረው። አባ ቶልያኖስም ከራእዩ ሲነቃ የሰማውንና ያየውን ሁሉ በዙሪያው ለነበሩት ጳጳሳትና ቀሳውስት ገለጠላቸው።

በነጋታው ድሜጥሮስ በእርሻው መሐል ያለ ጊዜው አፍርቶ ያገኘውን ሰባት የወይን ዘለላ ለአቡነ ቶልያኖስ ሊያበረክት መጣ። አባ ቶልያኖስና በዙሪያው የነበሩ ጳጳሳት ተደሰቱ። አባ ቶልያኖስም «ትናንት መልአከ እግዚአብሔር በራእይ ስለ እርሱ የነገረኝ ሰው መጣላችሁ ሲል አመለከታቸው።

ድሜጥሮስ ሳያስበው በአባ ቶልያኖስ እና በዙሪያው በነበሩ ጳጳሳት አሥራ ሁለተኛው ፓትርያርክ ለመሆን ታጨ። ቶልያኖስ እስከሚያርፍ ድረስም ወደ ወይን እርሻው ተመለሰ።

ልዑል እግዚአብሔር ለድሜጥሮስ አእምሮውን ስለከፈተለት ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ ተማረ። አባቶልያኖስ ሲያርፍም በ181 ዓ.ም በመንበረ ማርቆስ ተቀመጠ።

ልቡ የዋሕ ቅንና ትሑት ስለነበረ እግዚአብሔር አምላክ ልዩ ጸጋን አድሎት ነበር። ሲያስተምር ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት በቀላሉ የሚገቡ የሚሰሙዋቸውንም ከልዩ ልዩ የነፍስና የሥጋ ደዌያት የሚፈውሱ፣ ምሥጢር የሚገልጡ ስለነበሩ ሕዝቡ ለትምህርቱ ከየሀገሩ ይሰበሰብ ነበር።

በዚያ ዘመን በክርስቲያኖች ዘንድ የአጽዋማት መግቢያቸውና መውጫቸው፣ የበዓላትም መዋያ ዕለታት ተለይተው ባለመቀመጣቸው በአከባበሩ ላይ መለያየት ነበረ። አባታችን ድሜጥሮስ ይህንን ችግር ለመፍታት በማሰብ ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበረ። የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔርም የቀናት አቆጣጠር የባሕረ ሐሳብን ነገር ስለገለጠለት ዛሬ የምንጠቀምበትን ቀመር አዘጋጀ።

ይህንን ቀመርም በዚያ ዘመን ለነበሩት ለኢየሩሳሌሙ ጳጳስ ለቅዱስ አጋቢዮስ፣ ለአንጾኪያው ፓትርያርክ ለቅዱስ ማክሲሞስ፣ እንዲሁም ለሮሙ ፓትርያርክና ለሌሎችም አበው ላከላቸው። ይህንንም የድሜጥሮስ ቀመር በ325 ዓ.ም የተሰበሰበው የንቂያ ጉባዔ አጽድቆታል።

ድሜጥሮስ የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛለት፣ የኃጢአተኞችን በደል የጻድቃንንም ቅን ልቡና የመመልከት ጸጋ የተሰጠው አባት ነበር። በዚህም የተነሣ ሥጋወደሙን ሊቀበሉ ንስሐ ሳይገቡ በድፍረትና ያለዕውቀት የሚመጡትን ሰዎች እየለየ ንስሐ እንዲገቡና ከዚህ ታላቅ በደል እንዲመለሱ ይመክራቸው ይገስጻቸውም ጀመር።

ብዙዎቹ በምክሩና በተግሣፁ ተጠቅመው ለደገኛው ክብር ሲበቁ። አንዳንዶቹ ግን «ይህ ሰው አግብቶ በተድላ ደስታ እየኖረ እንዴት እኛን ኃጢአት አለባችሁ እያለ ከሥጋ ወደሙ ይከለክለናል» በማለት በሕዝቡ ዘንድ ማስወራት ጀመሩ።

ልዑል እግዚአብሔር የሕዝቡን በሐሜቱ መሸበር ሲመለከት ለድሜጥሮስ «ድሜጥሮስ ሆይ ያንተን መዳን ብቻ ብትመለከት፣ ሕዝቤ በሐሜት ሊጠፉ ነውና ንጽሕናህን ግለጥላቸው» ሲል በራእይ ተገልጦ ነገረው።

አንድ ቀን ቅዳሴውን ፈጽሞ ሲወጣ ሕዝቡ ሁሉ ወደ ቤት እንዳይሄዱ አዝዞ፣ ደቀ መዛሙርቱንም ደመራ እንዲደምሩ አደረገ። ከእንጨቱም ፍም በወረደ ጊዜ በቀሚሱ እያፈሰ ዙሪያውን ለነበረው ሕዝብ ካሳየ በኋላ በሚስቱ ቀሚስ ላይ አደረገው። እርስዋም እየዞረች ለሕዝቡ አሳየችው። ፍሕሙም ከቀሚሷ በተራገፈ ጊዜ ከሁለቱም ልብስ ላይ አንዳችም የተቃጠለች፣ የጠቆረችና የተበላሸች ክር አልነበረችም።

ከዚህ ድንቅ ነገር በስተጀርባ ያለውን ምሥጢር ለማወቅ ለጓጓው ሕዝብ የእርሱንና የባለቤቱን ነገር ገለፀላቸው።

በዚህም ሕዝቡ የድሜጥሮስንና የባለቤቱን ንጽሕና ተገነዘቡ፣ ሐሜቱን ያነሡትና ያስፋፉትም ሁሉ ንስሐ ገብተው ተመለሱ።

ድሜጥሮስ ሕዝቡን በኦርቶዶክስ እምነታቸው ጸንተው በምግባር በርትተው ለቅድስና ይበቁ ዘንድ ያለማሰለስ አስተምሮአል። ባረጀና መራመድ ባቃተው ጊዜ እንኳን ደቀ መዛሙርቱ ተሸክመው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስዱትና ሕዝቡን ያስተምራቸው ነበር።

በመጨረሻም ለ43 ዓመታት በመንበረ ማርቆስ አገልግሎ በተወለደ በ105 ዓመቱ በ224 ዓ.ም ዐረፈ።✣

ጸሎቱና በረከቱ በሁላችን ላይ ይደር።

አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዓምደ ወራዙት

በዚሁ ርዕስ ባለፈው መግቢያውንና ደካማ ጎናችንን ለማሸነፍ የሚረዱንን አምስት የመፍትሔ ነጥቦችን አንሥተን በዝርዝር መመልከት መጀመራችን ይታወቃል። ይኸውም ደካማ ጎንን ለይቶ ለማወቅ የሚረዱንን ሁለት የመጀመሪያ ነጥቦች ተመልክተን በይቀጥላል ለዛሬ ተላልፈናል። የቀሩትን ነጥቦች እነሆ:-

### 3. በትሕትና ራስን በመመርመር

ክርስትና መስናክል የበዛበት ጉዞ በመሆኑ ዓይናችንን ጨፍነን የምንጓዝበት ሳይሆን በማስተዋል ረጋ ብለን የምንራመድበት ሕይወት ነው። ኤፌ.5፥15። ይኸውም ዘወትር ትሕትናን ተላብሰን ወደ ልባችን በመመለስ ራሳችንን ስንመረምር፣ እስከመጨረሻው መጓዝ እንችላለን።

ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ ብዛት በትዕቢት እንዳይወድቅና ማንነቱን እንዳይረሳ ዘወትር መለስ ብሎ ራሱን ይመለከት ነበር። 2ቆር.12፥7፤ 1ጢሞ.1፥12–17።

የጠፋው ልጅ እየሠራ የነበረው ሁሉ ትክክል አለመሆኑን ዐውቆ ወደ አባቱ ለመመለስ የቻለው ወደ ልቡናው ተመልሶ ራሱን በመረመረበት ሰዓት ነበር። ሉቃ.15፥17።

ዛሬ ግን ብዙ ሰዎች በመንፈሳዊው ሕይወታቸው ጥሩ ደረጃ ይደርሱና ወደ ልባቸው ተመልሰው ራሳቸውን ስለማይመረምሩ ደካማ ጎናቸውን ማወቅ አይችሉም። ስለዚህም ‹እገሌ እኮ እንዴት ያለ ሰው ነበር› የሚል ዝናን ብቻ ትተው ያልፋሉ። አንዳንዶቹም ራሳቸውን መመልከት የሚጀምሩት ጥፋት ከደረሰ በኋላ ስለሚሆን ጸጸትን ያተርፋሉ።

ስለዚህ ክርስቲያን ዘወትር መለስ ብሎ በትሕትና ራሱን ይመረምራል፥ እየሠራ ያለውንም ይመለከታል። ደካማ ጎኑንም ለይቶ ለመፍትሔው ይጥራል።

### 4. የሌሎች በተለይም በክርስትናው ጎዳና የተጓዙትን ሰዎች ምክር በመስማት

መለስ ብለን ራሳችንን ስንመረምር መለየት ያቃተንን ደካማ ጎናችንን እግዚአብ ሔር በሌሎች አድሮ ሊያሳውቀን ይችላል።

ዳዊት በነቢዩ በናታን አማካይነት ሲነገረው ደካማ ጎኑን ዐውቆ ተመለሰ። 2ሳሙ.12፥1–15።

ነገር ግን ብዙ ሰዎች አሁን ያሉበትን ክብርና ደረጃ ብቻ በማየትና ራሳቸውን ፍጹም አድርገው በመቍጠር ሌሎች እንዲመክሯቸው አይፈልጉም። ቢነገራቸውም እንኳን ከክፋትና ከቅናት ወይም ከጥላቻ ስለሚመስላቸው አይቀበሉም። ለዚህም የኢዮርብዓምን ታሪክ ማስታወሱ በቂ ነው። 1ነገ.13፥1–6።

### 2. በታክቲክ (በጥበብ) ሳይሆን በእምነት

ደካማ ጎናችን የትኛው እንደሆነ ከታወቀ በኋላ ‹ይህ ባሕርዬ ነው›፤ ‹ምን ላድርግ ጥሉብኝ ነው› ብሎ ተቀብሎ ከመኖር ለማሸነፍ መጣር ያስፈልጋል። ይህንንም ማድረግ የምንችለው በጥበብና በብልጠት ሳይሆን ሁሉን ማድረግ የሚቻለው

## ደካማ ጎንን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

እግዚአብሔር መሆኑን በማመንና ራስንም ለእርሱ አሳልፎ በመስጠት ነው።

አንዳንድ ወጣቶች ደካማ ጎናቸውን ያውቁታል። ነገር ግን እንደ ክርስቲያንነታቸው ይህንን ደካማ ጎናቸውን በእምነት ለማሸነፍ አይጥሩም፤ ይልቁንም በታክቲክና በብልጠት ለመወጣት ይሞክራሉ እንጂ። አንድ በሲጋራ ሱስ የተጠመደ ወጣት ሱሱን ለማቆም ማስቲካ ማኘክ፣ ከረሜላ በአፍ ውስጥ መያዝ ወዘተ. እንዲሁም በቀን ውስጥ አንድ ፓኬት ሲጋራ ከማጨስ ወደ ግማሽ፣ ከዚያም ወደ ሦስት፣ ሁለት…እያለ በጥበብና በጉልበት ለመተው ይታገላል እንጂ በጸሎትና በእግዚአብሔር ኃይል ታምኖ ፍጹም ቆራጥ ሲሆን አይታይም። ስለዚህም ቶሎና ለዘለቄታው ማሸነፍ ይከብደዋል።

ክርስቲያኖች ግን በእምነት በእግዚአብ ሔር ኃይል ሁሉን ማሸነፍ ይችላሉ። ለጊዜው ሳይሆን እስከ መጨረሻው!

ሕፃኑና እረኛው ዳዊት ጎልያድን የሚያክል ኃያል ጀግና ለማሸነፍ ብዙ ጥበብና የረቀቀ የጦር መሣሪያ አላስፈለገውም፤ በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ኃይል እንጂ! 1ሳሙ.17፥41–49።

የይሁዳው ንጉሥ ሕዝቅያስ ኃያሉንና አስፈሪውን፣ በብዙህ ሺ ሠራዊት ተደራጅቶ የመጣውን የአሦር ንጉሥ ሰናክሬምን ያሸነፈው በእምነት እንጂ በጥበቡ አልነበረም። 2ዜና.32፥1–23።

ስለዚህ ደካማ ጎናችን ምን እንደሆነ ካወቅን በእግዚአብሔር ኃይል ለማሸነፍ በእምነት ወደ እርሱ ልንጮህና ፍጹም ቆራጥ ልንሆን ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ኃይል የማንሻገረው ባሕር (ዘጸ.14፥10–31)፤ የማናፈርሰው ግንብ (ኢያሱ.6፥20)፤ የማናፈልሰው ተራራ (ማቴ.11፥25)፤ የማናሸንፈው ጠላት አይኖርም (ሉቃ.10፥19)። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። ፊልጵ.4፥13።

### 3. መጠገን ሳይሆን ማሸነፍ

ብዙዎቻችን በክርስትናው ጉዞአችን ደካማ ጎን እንደሚኖርብን እናውቃለን። ችግሩ ግን ይህ ደካማ ጎናችን አብሮን እንዲኖር ጠጋግነንና ሸፋፍነን እንተወዋለን እንጂ እስከመጨረሻው ለመላቀቅና ለማሸነፍ አንጥርም። ስለዚህም ዘወትር ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ሰዓት ብቅ እያለና እያገረሸብን ያስቸግረናል። በጉዞአችንም እንቅፋት ሆኖ ያሰናክለናል።

አንድ አሮጌና ሊፈራርስ የደረሰ ቤት ለዘለቄታው እንዲያገለግል ከተፈለገ ደግቅ ቀለም ብቻ ቀብቶ ማደስ ሳይሆን እንደገና መሥራት የቤቱን እድሜ ያረዝመዋል፤ ውበቱንም ይጨምረዋል። «በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም፤ መጣፊያው ልብሱን ይቦጭቀዋልና፤ መቀደዱም የባሰ ይሆናል። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፤ አቁማዳው ይፈነዳል የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል።» ማቴ.9፥16–17።

በክርስትና ጉዞም ለጊዜው ብቻ ብለን ጠጋግነን የምናቆመው ወይም የምንተወው ነገር ሊኖር አይገባም። ሙሉ በሙሉ ማሸነፍ እንጂ። ኢያሱ ከጌልጌላ እየተመላለሰ በከነዓንና በአካባቢዋ ሰፍረው የነበሩትን አምስቱን የአሞራውያን ነገሥታት ድል ከአደረገ በኋላ ነገሥታቱን (አለቆቹን) በተደበቁበት በመቄዳ ዋሻ አልተዋቸውም። ከተደበቁበት ወጥተው እንደገና አንሰራርተው እንዳያስቸግሩት ከዋሻው አውጥቶ ከገደላቸው በኋላ መልሶ በዋሻው ውስጥ ጥሎ ዘጋባቸው። ኢያሱ.10፥16–27። እግዚአብሔርም እሥራኤላውያንን ወደ ምድረ ርስት በገቡ ጊዜ እንዲሁ እንዲያደርጉ አዝዟቸው ነበር። ዘኁ.33፥52–55።

ታዲያ እንዴት እስከመጨረሻው ማሸነፍ እንችላለን?

ሀ. በንስሐ እስከ ሰንኮፉ ነቅሎ በማውጣት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብዙ ወጣቶች ንስሐ ስንገባና ኃጢአ ታችንን ስንናዘዝ ከላይ ከላይ እየተናዘዝን የተወሰነውን እናስቀራለን። ይህም ያስቀረነው ኃጢአት ተመልሶ አድጎ ያስቸግረናል። በዚህ ሐናንያና ሰጲራን እንዲሁም ሲሞን መሠሪን ማስታወስ ይቻላል። የሐዋ.5፥1–11፤ 8፥18–23።

ስለዚህ ኃጢአትን በንስሐ ከነሰንኮፉ አውጥተን ልንጥል ያስፈልጋል። ቆርጠህ ጣላት ነውና! ማቴ.5፥30።

ለ. ደካማ ጎናችን እንዲያንሰራራ የሚያደርጉትን መንገዶች መዝጋት

በጣም ሲያስቸግረን የነበረውን ደካማ ጎናችንን ካሸነፍነው በኋላ እንደገና እንሰራርቶ የሚያስቃየን ሲለውም የሚጥለን መግቢያ ቀዳዳ ስለምንተውለት ነው።

እሥራኤላውያን የአረማውያንን አማል ክት፣ ጣዖታትን እስከማምለክ የደረሱት ልጆቻቸውን በማጋባታቸውና የጠበቀ ግንኙ ነት በመመስረታቸው ነው። 1ሳሙ.3፥5–6።

ስለዚህ አንድ ያሸነፍነው ደካማ ጎናችን እንደገና እንሰራርቶ እንዳያጠቃን ቀዳዳ ልንከፍትለት አያስፈልግም። 2ዜና.32፥5። አካባቢ መቀየርና ወዳጆችን መተው እንኳን ቢያስፈልግ ልናደርገው ይገባል። ‹ወደ መንደሩም አትግባ›። ማቴ.8፥26።

ሐ. መራቅ ወይም መሸሽ

ብዙ ወጣቶች ደካማ ጎናቸውን ሙሉ በሙሉ ማሸነፍ የሚሳናቸው አቅማቸውን ባለማወቅ እዚያው በሚጠቁበት ሥፍራ ሆነው ስለሚታገሉ ነው። በሰዶም ውስጥ ሆና ከጥፋት ለመዳን ከመታገል ቢያንስ በወላፈኑ መለብለብ ስለሚኖር መራቅ ወይም መሸሽ ያስፈልጋል። ዘፍ.19፥17።

ዮሴፍ ከዝሙት ፍላጻ ያመለጠው ቆሞ ከጲጥፋራ ሚስት ጋር በዝግ ቤት ተከራክሮ በማሳመን ሳይሆን ልብሱን ጥሎላት በመሸሽ ነው። ዘፍ.39፥12።

እኛም ዛሬ ያለ አቅማችን በደካማ ጎናችን በምንጠቃበት ሥፍራ ሆነን ከመታገል በመራቅ ወይም በመሸሽ ያቺን የፈተና ሰዓት ልናሳልፍ ያስፈልጋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ብዙዎቻችንን ደካማ ጎን በመሆን ከሚያስቸግሩን ሦስት ነገሮች እንድንሸሽ ይመክረናል።

1. ከዝሙት – 1ቆሮ.6፥18።
2. ገንዘብን ከመውደድ – 1ጢሞ.1፥11።
3. ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት – 2ጢሞ. 2፥22።

ይቀጥላል

# በጸጋው መዳን እንዴት ነው?

ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

‹በጸጋው መዳን› የሚለው ቃል የሚያ ስታውሰን ከቀራንዮ አደባባይ፥ በመልዕልተ መስቀል የተፈጸመውን፥ የክርስቶስን ቤዛነት ነው። የቀደመውን ኃጢአት (በውርስ ይተላለፍ የነበረውን) ስለመተው የተደረገውን የእግዚአብሔር ቸርነት ፍቅሩ የተገለጠበትን ምሥጢር መርሳት አይገባምና። «በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና።» 1ዮሐ.4፥9፤ ዮሐ.3፥16።

ለመሆኑ «ጸጋ» ማለት ምን ማለት ነው? ጸጋ ማለት፥ ቸርነት፥ ምሕረት፥ በጎነት ያለ ብድራትና ያለዋጋ የሚደረግ ስጦታ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ማናቸውም ከእግዚአ ብሔር የሚገኝ ሀብት ሁሉ ጸጋ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ቸርነት፥ ምሕረት፥ በጎነት፥ ስጦታ እያሉ የሚናገሩት ጸጋውን ነው። መዝ.15፥1፤ 32፥5፤ 50፥1፤ ዘጸ.34፥6፤ ሮሜ.2፥4፤ 8፥28።

ቅዱስ ጳውሎስ በጸጋው የመዳንን ነገር ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ሲጽፍላቸው በመል እክቱ እንዲህ አለ። «እግዚአብሔር በባሕርዩ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ፥ በክርስቶስ ሕይወትን ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን። ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» ኤፌ.2፥4–9። ይላል።

እምነት ያለ መልካም ሥራ ብቻውን አያድንም ያም ሆኖ የኛ ሥራ ከእግዚአብሔር ለምናገኘው ክብር ተመጣጣኝ ሊሆን ስለማይ ችል በይቅርታው በቸርነቱ የምናገኘው ሀብት መብለጡን ያስገነዝባል።

ሐዋርያው የተናገረውን ምሥጢር ለመረዳት እያንዳንዱን ኃይለ ቃል እየመዘዙ በማውጣት ዝርዝሩን ማወቅ ስለሚያስፈልግ እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

«ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን።» ሲል በክርስቶስ ቤዛነት ትንሣኤ ልቡና አስነሣን ማለቱ ነው። ይህም ከኃጢአት ወደ ጽድቅ መለሰን፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን አወጣን፥ ከሞት ወደ ሕይወት አሸጋገረን። ሕይወት አጥተን ለነበርን ሥጋውን በመቁረስ፥ ደሙን በማፍሰስ፥ ሕይወቱንም በመስጠት ሕይወት ሆነን ማለት ነው። ምክንያቱም የክርስቶስ ሞቱ ሕይወታችን፥ ትንሣኤው ደግሞ ክብራችን ነውና።

«በጸጋው ድናችኋልና» የሚለው ቃል መልእክቱ በቸርነቱ ከኃጢአት ከፍዳ አዳነን ማለት ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ለሕማም፥ ለሞት ተላልፎ የተሰጠልን፥ እኛ ጠላቶቹ ሳለን ነውና። የምሕረቱን ባለጠግነትና የፍቅሩንም ታላቅነት የሚያሳየው ይኸው ምሥጢረ ድኅነት ነው። «ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን።» ሮሜ.5፥10 ተብሏልና።

«ከእርሱ ጋር አስነሣን» ማለትም በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ በኃጢአት የሞት ነውን ሁሉ፥ ሕይወት ሆኖ ትንሣኤ ልቡና አስነ ሣን ማለት ነው። ትርጉሙ «ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን።» ከሚለው ጋር አንድ ነው።

«በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።» ማለት ደግሞ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፥ ትንሣኤ ልቡና አስነሥቶን፥ ከክር ስቶስ ጋር ተዋሕደን እንድንኖር፥ በሰማያዊ ግብር አኖረን። (የትሩፋትን ሥራ እንድንሠራ አደረገን።) ማለት ነው። ሰማያዊ ግብር የተባለው በጐ ምግባር ነው። የልጅነትን ጸጋ በጥምቀት ያገኘን ክርስቲያኖች፥ የክርስቶስን ሥጋውን በበላንና ደሙን በጠጣን ጊዜ እርሱ ተዋሕዶናልና። ዮሐ.6፥56።

«ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና። ...ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» ሲል:- ይህም በቸርነቱ ከሙስና መቃብር ድነ ናል፥ በቸርነቱ በሃይማኖት ድነናል፤ ያዳነንም የእግዚአብሔር ቸርነቱ ነው እንጂ በሙያችን በጉልበታችን አይደለም ማለት ነው። ከዚህም የምንማረው ድኅነተ ምእመናን በመልዕልተ መስቀል የተፈጸመው በእግዚአብ ሔር ቸርነት እንጂ በማንም ሥራ አለመሆኑን ነው። ትርጉሙ ይህ እንጂ በጐ ሥራ አያስ ፈልግም ማለት አይደለም።

ስለ በጐ ምግባርማ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» ያዕ.2፥17 በማለት ነግሮናል። እምነት የሚገለጠው በሥራ ነውና። «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።» ያዕ.2፥26። ጌታም በወንጌል «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።» ብሏል። ማቴ.16፥27። በዮሐንስ ወንጌልም «መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፥ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና።» ዮሐ.5፥29። በማለት መልካም ሥራ ዋጋ እንዳለውና፥ ለሕይወት ትንሣኤ እንደሚያበቃ ነግሮናል። ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ የሥጋ ሥራ በማለት የዘረዘራቸው ክፉ ሥራን ሲሆን፥ የመንፈስ ፍሬ በማለት ደግሞ የዘረዘራቸው መልካም ሥራን ነው። ገላ.5፥19። የኤፌሶን

ወደ ገጽ 25 ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

አዘጋጅ – ግርማ ወ/ሩፋኤል

1. ውድ የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ አዘጋጆች

ሀ. በዚሁ በአዲስ አበባ በልደታ የሠርክ መርሐ ግብር ተሳታፊና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ስሆን፣ በክርስቲያናዊው ሕይወቴ አንድ ችግር ስለገጠመኝ ልጽፍላችሁ ተገደድኩ። ይኸውም በምኞት የማመንዘር ኃጢአት ነው። ቤተክርስቲያን ስከታተልና አንገቴን ደፍቼ ስሄድ ላየኝ ቅዱስ እመስላለሁ። ነገር ግን ቀን በአጠገቤ የሚያልፉት ሴቶች ላይ ዓይኔን በመትከል በዝሙት መንፈስ በልቤ አመላልሳቸዋለሁ። ማታም በእንቅልፌ ከእነርሱ ጋር አመነዝራለሁ። ይህ ሁኔታ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እያሰቃየኝ ነው። «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኞትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል» የሚለውን የእግዚአብሔር ሕግ በመተላለፍ ፈጣሪዬን አሳዝነዋለሁ፤ በዚህም የውስጥ ሰላም ወይም ዕረፍት እያሳጣኝና የሞራል ውድቀት እያስከተለብኝ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔውን «ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ» 1ቆሮ.7፥9። የሚለውን ቃል አስቤ እንዳላገባ ገና ተማሪና በወላጅ ትከሻ ላይ ያለሁ ነኝ። በጾምም ለማስወገድ ብዙ ሞክሬ አልቻልኩም። ግራ ገብቶኝ ተጨንቄአለሁና ምን ትመክሩኛላችሁ?

ተማሪ እገሌ– ከአዲስ አበባ

ለ. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ «አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኞትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል» ብሏል። ማቴ.5፥25–28። በዚህም መሠረት አንዲትን ሴት አይቻት በልቤ ተመኝቻት ማግኘት እየቻልኩ ‹ወይኔ እግዚአብሔር ምን ይለኛል?› ብዬ ከተውኳት እንደአመነዘርኩ ይቆጠራል ወይ?

አ.ዳ – ከሰላም በር መድኃኔዓለም ቤ/ክ አ.አ

እንዲሁም ወንድማችን ተክለ ጊዮርጊስም ከመጀመሪያው ጋር የሚመሳሰል ጥያቄ ጠይቀውናል።

መልስ – የሦስታችሁም ጥያቄዎች ተመሳሳይነት ስላላቸው በአንድ ላይ ለመመለስ እንሞክራለን። በቅድሚያ ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ ከመመለሳችን በፊት ስለምኞት ምንነት የብዙ ሰዎች ችግር በመሆኑ ሰፋ አድርገን ብንመለከት መልካም ነው።

ምኞት፥ አንድን ነገር ከፍ ባለ ስሜት መሻትና መፈለግ ሲሆን፣ ሁለት ዓይነት ምኞት አለ።

1. የማይገባ ምኞት

ይህ ዓይነቱ ምኞት የአንድን ሰው ሀብት ንብረቱን ወይም ውበትና ጤናውን፣ ወዘተ. ከስግብግብነት የተነሣ ‹ምነው የእኔ ቢያደርገው!› ብሎ ማሰብ ነው። እንደዚህ ከራስ ወዳድነት የመነጨ ምኞት የመጨረሻ ውጤቱ ውድቀትና ሞት ነው። ኤፌ.5፥3፣ 1ጢሞ.1፥9። በብዛት ሰዎች በእንደዚህ ዓይነት ፈተና የሚጠቁትም ፍላጎታቸውና ዐቅማቸው ሳይመጣጠን ሲቀርና አንድ ነገር ያለጊዜው ሲፈልጉ ነው። ለምሳሌ:- አንድ ገና በወላጆቹ ላይ በጥገኝነት የሚኖር ተማሪ ቪላ ቤት፣ መኪና እና ትዳር እንዲኖረው ቢፈልግ ፍላጎቱና ዐቅሙ ስለማይመጣጠን እንደተመኘ ይኖራል። ይህ በክርስቲያኖች ሕይወት የማይገባ በመሆኑ የተከለከለ ነው። ዘጸ.20፥17፤ ምሳ.21፥26፣ ኤፌ.4፥18–20። ምኞት አብዛኛውን ጊዜ ከማየት የሚመጣ ስለሆነ ዓይን የማይረባ ነገር እንዳያይ መጸም አለበት ቅዱስ ያሬድም የሚመክረው ይህንኑ ነው። ምኞትን በተቻለ መጠን ወደመዳከም መለወጥ ነው።

2. መልካም ምኞት

በዕውቀታችን፣ በሥጋዊና መንፈሳዊው ሕይወታችን አሁን ካለንበት ደረጃ የተሻለውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደፊት ልሆን እችላለሁ ብሎ ማሰብና ያሰቡትንም ከዓላማ ለማድረስ መጣር መልካም ምኞት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ምኞት ከዐቅም በላይም አይደለም። በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያትና ደጋግ አባቶች ያን ሱባኤ የተቆጠረለትን፣ ትንቢት የተነገረለትን ጌታ ለማየት ይመኙ ነበር። ይህ መልካምና ወደ ቅድስና የሚያመራ ምኞት ነው። ማቴ.13፥17። እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ» ይላል። 1ጴጥ.2፥2–3።

ከዚህ አንፃር አንድ ወጣት አንዲትን ሴት ቁመናዋን ባሕርይዋን (ምግባሯን) ተመልክቶ፣ ይህች ወደፊት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከእኔ ጋር ብትኖር መልካም ነው ብሎ ለዘለቄታው በተቀደሰ ሕይወት አብሮ ለመኖር ማሰብ መልካም ምኞት ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ በአካላዊ ቅርጿና ውበቷ ብቻ ተማርኮ ለጊዜያዊ የሥጋ ፍትወት ማሰብ ደግሞ የማይገባ ምኞት ወይም ዝሙት ነው።

ምኞት ከምን ይመጣል?

ምኞት ብዙ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለይ ፈተና ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ይመጣል። እንደፈተናነቱ በበጐ መልኩ ለክብርና ለጽድቅ ዋጋ ለማሰጠት የሚመጣ ፈተና ሊኖር ይችላል። የሚመጣው ፈተና ግን ወድቀን የምንቀርበት፣





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ተሰነካክለን ከቤቱ የምንወጣበት አይደለም። በአንጻሩ እግዚአብሔር የሚፈትነን:-

1. ለክብር እንድንበቃ

ኢዮብ ተፈተነ። ፈተናውን በድል ከተወጣ በኋላ ግን በጸጋ ላይ ጸጋን በክብር ላይ ክብርን አገኘ። ያጣው ሁሉ በሁለት እጥፍ ተመለሰለት።

የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ ሁሉ በፈተናና በመሰናክል የታጠረ ነበር። ነገር ግን በድል ተወጥቶት የክ ብርን አክሊል ተቀዳጀ። 2ቆሮ. 11፥22–29፤ 2ጢሞ.4፥6–8።

ስለዚህ ሽልማት የሚገኘው ከድል በኋላ በመሆኑ ፈተናን ድል አድርገን ለክብር እንድንበቃ በምኞትም ቢሆን እንፈተናለን።

2. ለእርሱ ያለንን ፍቅር እንድንገልጽ

አብርሃም በእርጅናው ዘመን ያገኘውን አንድ ልጁን፣ ይስሐቅን፣ እንዲሠዋ ተጠየቀ። ምንም ነገር ሳያወላውል በእምነት ከልጅ ፍቅር የእግዚአብሔርን ፍቅር አስበልጦ የተባለውን በመፈጸሙ ለእግዚአብ ሔር ያለውን እምነትና ፍቅር ገለጸ። ፈተናውንም በድል ተወጣ። በዚህም ርእሰ አበው በመባል ሰው በበጎ ሲወሳ (ሲነሳ) ይኖራል ዘፍ.22፥12።

ዮሴፍ በዝሙት ተፈተነ። «እን ዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን እሠራለሁ» በማለት ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር በመግለጽ ፈተናውን በድል ተወጣ። ስለሆነም በፈርዖን ቤተ መንግሥት ታላቅ ሰው ሆነ። ዘፍ.39፥6–9።

ስለዚህም ክርስቲያኖች ኃጢአ ትን የምንተወው አቅቶን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፍቅር አስበልጠን ስለማንፈልገው ነው። ሮሜ.8፥35።

3. በእርሱ መንገድ በተጋድሎ እንድንጸና

«በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባ ችሁ፥ አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌ አለሁ» ዮሐ.16፥33። ብዙ ሰዎች የክርስትናን ጉዞ በተስተካከለ ጎዳና የሚደረግ ሽርሽር አድርገው ያስቡት ይሆናል። ነገር ግን የክርስትና ጉዞ ጠመዝማዛ አቀበትና ቁልቁለት የበዛበት ነው። በዚህም በመጓዝ ከተጋድሎ ብዙ ልንማር፣ ለሌሎችም ብርሃን ልንሆን እንዲሁም የእግዚአ ብሔር ጠበቃ ምን ያህል እንደሆነ ልናውቅ እንችላለን። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን በምኞትም ይሁን በሌላ ሊፈተንና መሰናክል ሊገጥመው ይችላል። «ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም። ፊልጵ.1፥29።

4. ዐቅማችንን እንድናውቅ

በክርስትና ጉዞአችን ሁሉም ነገር ሰላማዊና ያለፈተና ከሆነ ኃይለ እግዚአብሔርን እስከመኖሩም ልንዘ ነጋ እንችላለን። ሁሉንም እኛ በችሎታችን ያደረግነው ይመስ ለናል። ፈተና ገጥሞን በድል ስንወ ጣው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ምን እንደሆነ እንረዳለን። ትሕትናን እንማራለን። ዐቅማችንንም እናውቃ ለን። ዮሐ.21፥15። ለምሳሌ፥ አንዳንድ ወጣቶች ደናግል መሆና ቸው በራሳቸው ጥረትና ብርታት ብቻ የሆነ እየመሰላቸው። በሌሎች ላይ ይፈርዳሉ። ስለዚህ ትሕትናን ተላብሰው ዐቅማቸውን እንዲያውቁና ያለ እግዚአብሔር ኃይል ደካሞች መሆናቸውን እንዲገነዘቡና ወደ እርሱ እንዲጮኹ በምኞት ሊፈተኑ ይች ላሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ፈተና ወደ ንስሐ ይመራናል።

እንዲሁም በሌሎችም ምክንያ ቶች ልንፈተን እንችላለን። ነገር ግን ምንም ዓይነት ፈተና ቢሆን እግዚ. አብሔር ሰዎችን በክፉ አይፈትንም። ያዕ.1፥13።

በአንጻሩ በራሳችን ድክመትም ሆነ በዲያብሎስ የምንፈተንበት ጊዜ የበዛ ነው። ብዙ ሰዎችም ወድቀውና ተሰነካክለው የሚቀሩትም በእንደዚህ ዓይነት ፈተናዎች ነው። ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን ምክንያቶች ለመመልከት እንሞክራለን።

1. በመንፈሳዊ ሕይወት አለመብሰል

አንድ በክርስቲያናዊ ሕይወቱ ያልጠነከረ ወጣት የሚፈልገውን ሁሉ እርሱ የእግዚአብሔር በመሆኑ እግ ዚአብሔር እንደሚሰጠው ከማሰብ ይልቅ ከዐቅሙ በላይ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ሲመኝ ይታያል። ፍላጐ ቱም ውሉን አይሆንም። የሚያየው ሁሉ የእርሱ እንዲሆን ይፈልጋል። እንደዚህ ዓይነት ሰው ፈተና ቢደር ስበት እንኳን እንዴት መወጣት እንዳ ለበት ስለማያውቅ በጣም ይጨነቃል። እስከመውደቅም ይደርሳል። እንደ ዚሁም በክርስትና የጠነከሩት እንኳን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሚደክ ሙበት ወቅት በምኞት ሊፈተኑ ይችላሉ።

2. የሥጋ ምኞት ብቻ በማሰብ መዝናናት

ለሥጋዊ ምኞቱና ድሎቱ ብቻ የሚጨነቅ ሰው አእምሮው ከምኞት አይለይም ለፈተናም ይጋለጣል። ሰውነቱን ለማዝናናት ሲል አንድ ነገር ሊያገኝ ይፈልጋልና። ዳዊት ከታቦተ ጽዮን ተለይቶ ሲዝናና ነበር የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን አይቶ የተመኘው። 2ሳሙ.11፥2–5።

3. ሥራ ፈትቶ መቀመጥ

አንድ ምንም ሳይሠራ የሚቀመጥ ሰው አእምሮው በምኞት የተመላ ይሆናል። ለዚህ ነው ‹የሥራ ፈት አእምሮ የክፉ መንፈስ ቤተ· ሙከራ ነው› የሚባለው።

4. የምናዘወትራቸው ታሪኮች

ዛሬ በዓለማችን ወጣቱ ሰብአዊ ክብሩንና ንጽሕናውን ጠብቆ እንዳ ይኖር ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል ዘወትር በፊልም፣ በቪዲዮና በቴሌ ቪዥን፣ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን እና በመጻሕፍት በሚመለከታቸው፣ ከሚያደምጣቸውና ከሚያነባቸው አሉታዊ ነገሮች የተነሣ ነው። ያን በታሪኩ ውስጥ የሚያውቀውን ገጸ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባሕርይ ለመሆን ይጥራል ወይም እንደዚያ ዓይነት ሰው ለማግኘት ይመኛል።

ስለዚህ አንድ ክርስቲያን የተቀ ደሰ ሕይወት እንዲኖረው ምን ዓይነት ታሪኮችን መመልከት፣ ማዳመጥና ማንበብ እንዳለበት ሊመርጥ ያስፈልጋል።

5. ያለንበት አካባቢና የምናቀርባቸው ጓደኞች

ያለንበት አካባቢ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንካሬና ድክመት ወሳኝነት አለው። በምንውልበት አካባቢ የሚነገሩት ነገሮችና የምን መከረው ምክር ወደ ምኞትና ወደ መጥፎ አዝማሚያ እንድናመራ ሊያደርገን ይችላል። በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ጓደኞቻችን ወይንም በምንሠራበት አካባቢ የሥጋ ፍትወት የሚያነሳሱ ነገሮች የሚነገሩ ከሆነ የሕሊና ምኞት ይፈጠራል።

6. ከሰይጣን ፍላጻ

አንዳንድ ጊዜ ባላሰብነው ጊዜና ባልጠበቅነው ሰዓት የማንፈልገው ሃሳብ በሕሊናችን ይገባና ያንን ማሰላሰል እንጀምራለን። የማናውቀውንና በምድር ላይ ሊፈጠር የማይችል አይነት ስዕል በሕሊናችን እስከመሳል እንደርሳለን። ይህም የሰይጣን ፍላጻ ነው። በተለይም በክርስቲያናዊ ሕይወታችን እያደግን ስንሄድ ዲያብሎስ ተስፋ ለማስቆረጥ ብዙ ሊታገለን ይችላል። ታዲያ ልናውቀው የሚገባን ሰይጣን ምንም ያህል ቢፈትነን ሊያስገድደን አይችልም። እኛን የማዘዝ ኃይል የለውምና። እስከ መጨረሻው በእምነት ብንጸናና የበለጠ እየተጋን ስንቃወመው ይጠፋል። ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንትም ይቀርባል። ያዕ.4፥7።

አንግዲህ ይህን ያህል ምኞትንና መንስኤዎቹን ከተመለከትን በቀጥታ ወደ መፍትሔዎቹና ወደ ጥያቄዎች እንመለሳለን።

በቅድሚያ አንድ ክርስቲያን በፈተና ከተያዘ በኋላ «እንዴት እወጣው ይሆን?› ብሎ ከመጨነቅ አስቀድሞ መጠንቀቁ ይመረጣል። «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» ማቴ.26፥41።

ከዚህም ሌላ ፈተናው ከመጣ በኋላ እንኳን በድል ለመወጣት ራስን በመንፈሳዊ ሕይወት ማጠንከር ያስፈልጋል። ይኸውም በመንፈሳዊ መርሐ ግብሮች ራስን ማጥመድ፣ መጻሕፍት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ መዝሙር መዘመር ወይም ማዳመጥ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳይም ሆነ ስለአነበብናቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ከሰዎች ጋር መወያየት፣ ከተቻለ ቅዱሳት መካናትን መጎብኘት በመሳሰሉት ለምኞት ክፍተት አለመስጠትና አእምሮን ሥራ ማስያዝ ዋነኛው መፍትሔ ነው።

ወደ መጀመሪያው ጠያቂአችን መልስ ስንመጣ፣

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የምኞት ፈተና ምክንያቶች ብዙ እንደመሆናቸው አንተ «ለምን በእኔ ላይ እንደዚህ ይሆናል?» ብለህ አትጨነቅ ሌሎች በጣም ብዙ ወጣቶች እንደዚሁ ስለሚፈተኑ አንተ ብቻኛ አይደለህምና። ስለዚህ ፈተናውን ለመወጣት ረጋ ብለህ አንተ የሚፈለግብህን ለምሳሌ – የምትወዳቸው ታሪኮች እንዴት ያሉ ናቸው? አብረሃቸው የምትውላቸው ጓደኞችህስ ምን ዓይነት ናቸው? ክርስቲያናዊ ሕይወትህስ እንዴት ነው? ወዘተ. መለስ ብለህ ራስህን በመመልከት መስተካከል ያለበትን አስተካክል።

ከአንተ ዐቅም በላይ ከሆነ ዳግም ‹በጾምም ሞክሬ አልቻልኩም› እንዳልከው አንድ ሁለት ጊዜ ጾም፣ ጸልዮ ማቆም ሳይሆን የበለጠ በመትጋት ጾምንና ጸሎትን ሕይወትህ ማድረግ ይጠበቅብሃል። በተቻለ መጠን ከትምህርትህና ከጥናትህ ጊዜ ውጭ ያለውን ትርፍ ሰዓት ሁሉ በመንፈሳዊ ተግባር ለማሳለፍ ሞክር። ከሁሉም በላይ ሰማዕትነት የሥጋ ፍላጎትን ገዝቶ ራስን ለክብር ማብቃት በመሆኑ ይህንን እያሰብክ ድል እስክታደርገው መትጋት ያስፈልጋል። 1ጴጥ. 4፥12–15። የትዳሩን ጉዳይ ግን አሁን ካለህበት የኑሮ ደረጃ ጋር እያመዛዘንክ እንደገና ልታስብበት ይገባል። አሁን ጊዜው አይመስለንምና። አሁን የአንተ ሥራ መሆን አለበት ብለን የምናምነው መማርና ራስህን መቻል ሲሆን ከዚያ በኋላ ነው ትዳር የሚያምረው። አለበለዚያ ለፈተናና ለውድቀት ሊሆንብህ ይችላል። በተረፈ ከንስሐ አባትህ አትለይ።

የሦስተኛው ጠያቂአችንም ከዚሁ ጋር ስለሚመሳሰል በዚሁ እናልፈዋለን።

ሁለተኛው ጠያቂአችን ዋናው ነገር ያዩአትን ሴት ለምን ዓላማ ነው የተመኟት? ለዘለቄታው ትዳር መሥርቶ አብሮ ለመኖር ወይስ ለሥጋዊ ፍትወት? ለትዳር ከሆነ የተቀደሰ ዓላማ ነው። የሥጋን ፍትወት በማሰብ ከሆነ ግን ኃጢአት ነው። ከዚያስ በላይ ሴቲቱ የሌላ ሆና ብትገኝ ምን መልስ ሊኖር ይችላል? ስለዚህ ንስሐ መግባትና ከእንደዚህ ዓይነቱ ምኞት ከላይ በገለጽነው መሠረት ራስን ማራቅ ያስፈልጋል።

2. ውድ የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ አዘጋጆች:-

ግልጽ ያልሆኑልኝን ጥያቄዎችን ሳነሳ ለመልሱ እንደምትተባበሩኝ በመተማመን የሚከተሉትን ሦስት ጥያቄዎች እጠይቃለሁ።

ሀ. 3ኛ ዓመት ቁ.3 እትማችሁ ላይ ስለተክሊል ጋብቻ ተጠይቃችሁ መልስ መስጠታችሁ የሚታወስ ነው። በዚህም የተክሊል ጋብቻን ለመፈጸም ሁለቱም ደናግል መሆን አለባቸው ተብሎ ተመልሷል። ነገር ግን አንድ ሰው ከዚህ በፊት የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ከሌላ ሴት ጋር አድርጎ በኋላ ግን በንስሐ ተመልሶ ከአንዲት ድንግል ሴት ጋር ለመጋባት ቢፈልግ ይህች ሴት ያለተክሊል አላገባህም ብትለው ምን ማድረግ አለበት።

ለ. አንድ በዝሙት የወደቀ ወጣት ተመልሶ ንስሐ ቢገባ፣ መንፈሳዊ ሹመት (ሥልጣነ ክህነት) ሊቀበል ይችላል?

ሐ. እንደዚህስ ዓይነት ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በመድረክ ላይ ወጥቶ መስበክ ይችላል?

ዜና ገብርኤል

(አዲስ አበባ)

መልስ – ስለተክሊል ጋብቻ ባለፈው እትማችንና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 3 ‹ምሥጢሬን ላካፍላችሁ› ዓምድ በሰፊው የተመለሰ መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ ሦስቱንም ጥያቄዎች በአጭሩ ለመመለስ እንሞክራለን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሀ. ባለፈው እንደተባለው የተክሊል ጋብቻን ለመፈጸም ሁለቱም ተጋቢዎች ደናግል መሆን አለባቸው። አንደኛው ወገን ሆኖ የተቀረው ግን ካልሆንና ድንግሉ የግድ በተክሊል ማግባት አለብኝ የሚል ከሆነ እንደርሱ ድንግል መፈለግ አለበት። በተክሊል ለሚገኘው የጋብቻ ክብር ራስን ብድንግልና ጠብቆ ማቆየት የግድ ያስፈልጋልና። ይህ ቤተክርስቲያን ልጆቿ ራሳቸውን ጠብቀው እንዲያድጉ የደነገገችው ሕግ ነው። ያለበለዚያ ፍቅሩና መስማማቱ ካለ አንዳቸው በአንዳቸው ስለሚቀደሱ ጸሎተ መዓስባኑ ተፈጽሞላቸው ጋብቻቸውን በቅዱስ ቁርባን ማጽናት ይችላሉ። በተረፈ በአካባቢአችሁ ሥርዓተ ኖሎትን ጠንቅቀው የሚያውቁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቢያማክሩ ይመረጣል።

ለ. አዲስ አማኝ ሆነው ተምረው የተጠመቁ ከሆነ ከዚያ በፊት የሠሩት ኃጢአት በጥምቀት ይሠረይላቸዋል። በሐዋርያት ዘመንም ሲሠራበት ነበር። ነገር ግን የሥላሴን ልጅነት ከአገኙበት ጊዜ ጀምሮ ራሳቸውን በንጽሕና መጠበቅ ይኖርባቸዋል። አንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ካህን ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ መሆን አለበት። ምክንያቱም ካህኑ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበውና ሌላውንም ምእመን ሊያቀርብ የሚችለው ንጽሕና ቅድስና ያለው እንደሆነ ነው። ያለበለዚያ ክንፉን እንደተሰበረና መብረርም እንደተሣነው አሞራ ተግባሩን ሁሉ ለማከናወንና ግዳጁን ለመፈጸም የማይችል ሆኖ ይኖራል። ካህኑ የሌላውን በደል ሁሉ ይቅር ሲል የክህነት ማዕረግ ግን ከአደፈ ከተገደፈ በኋላ ይቅርታ የሌለው በመሆኑ አስቀድሞ በንጽሕና ለመያዝ ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ዘሌዋ.11፥44፤ 1ጴጥ.1፥16። እግዚአብሔር የቀደመ ኃጢአትን ይቅር ቢል የሰው ልጅ ግን ደካማ ነውና ንጽሕናውን ያልጠበቀ ሰው ቢያስተምረውና ኃጢአትህን ይቅር ይበልህ ቢለው «አንተስ ማን ነበርከና!» ማለቱ አይቀርም። ስለዚህ ምንም እንኳን ሰው ሆኖ ከኃጢአት የነፃ ባይኖርም ካህን ኃጢአቱ በሰው ፊት የተገለጠ መሆን የለበትም። ቅድስና የካህኑ የተለየና ከሁሉም የበለጠ መታወቂያ መመዘኛ ነውና በፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ አንቀጽ 9፥282 የተደነገገውም ይህንኑ ያመለክታል «ከዝሙት ምክንያት ወገን በማኖቸውም ምክንያት በእርሱ ከምዕመናን ወገን የከሰሱት ቢኖር በመዳራት በዓመፅ ከሚያሳፍር ሥራ ወገን የከሰሱት ቢኖር በመዳራት፣ በዓመፅ ከሚያሳፍር ሥራ ወገን ይህን በሚመስል በግልጽ የረቱት ሰው ከክህነት መዓረግ ወገን ምንም ምን አይሻም።»

ሐ. መስበክ ግን ይችላል። ሌላው ይቅርና እንደ ቅዱስ ጳውሎስ እኔም እኮ ኃጢአተኛ ነበርኩ። አሁን ግን በቸርነቱ ለዚህ አበቃኝ ብሎ መናገርና ማስተማር ነው። 1ጢሞ.1፥13 እንዲሁም በሰማዩ አባቴ ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔ ደግሞ በላይ በሰማዩ አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ። ማቴ.10፥32። የሚለውን አምላካዊ ቃል ሁሉም ሊፈጽም ይገባዋል። መግደላዊት ማርያም እንዲሁም ሳምራዊቷ ሴት ስለጌታ ሲናገሩ ሲመሰክሩ የኋላ ታሪካቸው እንቅፋት አልሆነባቸውም። ዋናው ነገር ለማስተማር የሚያስተምሩትን ማወቅ (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሐዲስትና ብሉያትን ወዘተ.) እንዲሁም የሚናገሩትን ሆኖ መገኘት ነው የሚያስፈልገው።

3. ስለ ትዳር ችግርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ስርዓት በ7 ገጽ ደብዳቤ የጠየቅሽን የመጽሔታችን አንባቢ መልሱን በጽሑፍ ለመስጠት ስለሚያስቸግርና አንቺም ከዚሁ ከአዲስ አበባ ስለሆንሽ በአካል ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ የሚገኘው ጽ/ቤታችን ብቅ ብትይና የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ አዘጋጆች ብለሽ ብታነጋግሪን የሚሆነውን ልንወያይ እንችላለን። ካልቻልሽም አድራሻሽን ላኪልንና በግል ይመለስልሻል።

<u>ማሳሰቢያ</u> 1. ከማኅበራዊ ኑሮ የገጠሟችሁን ችግሮቻችሁን በተቻለ መጠን ግልጽ አድርጋችሁ ጻፉልን፣ ምንም ነገር ልትፈሩም አይገባም።

2. ጽፋችሁ ያልተመለሰላችሁ በየተራ እየመለስን ነውና ታገሡን።

3. መውጣት የሌለበትን አድራሻ እኛው ራሳችን ስለምንተወው በግል መመለስ ያለበትን ጥያቄ እንድንመልስላችሁ አድራሻችሁን አትደብቁን። ✣

ከገጽ 21 የዞረ

መልእክቱም «እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ፤ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ።» ይላል ኤፌ.5፥7። እዚህም ላይ ፍሬ የሌለው የጨለማ ሥራ የተባለው ኃጢአት ሲሆን፥ ፍሬ ያለው የብርሃን ሥራ ጌታም ደስ የሚሰኝበት ደግሞ በጐ ምግባር ነው። ከእግዚአብሔር ልጆችም የሚጠበቀው ይኸው ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ እንደተናገረው፥ እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነ ካወቅን፥ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና። 1ዮሐ.2፥29። በአጠቃላይ ጸጋው ወደ መልካም ሥራ ይመራናል እንጂ መልካም ሥራን እንዳንሠራ የሚያዘናጋን አይደለም። ሕዝ.36፥25። ዋናው ነገር በሥራ መመካት አይገባም እንጂ መልካምንስ ሥራ መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጸጋ የሚለው ቃል አያሌ ምሥጢሮችን አዝሎ እናገኘዋለን።

1. ወንጌልን ጸጋ ይላታል። ሀ. ከኃጢአት እንድንለይና ፍትወተ ሥጋን እንድንተው፤ በዚህ ዓለም በንጽሕና በፍቅር እና በቅድስና እንድንኖር፤ ከክርስቶስም በጌትነት እንደ ሚመጣ እና ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋ እንደሚከፍል ተስፋ አድርገን እንድንጠብቅ፤ ራሱን ስለ እኛ ለሕማምና ለሞት የሰጠው ከኃጢአት ሊለየንና ከፍዳ ሊያድነን መሆኑን የምታስተምረን፤ ወንጌል ጸጋ ትባላለች። «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና።» ቲቶ.2፥11። የተባለው ለወንጌል ነው። ትርጉሙም ጸጋው ወንጌል ለሁሉ ታውቃለች ተረድታለችና ማለት ነው።

ለ. «ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፥ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና።» ዕብ.13፥9። የተባለውም ለወንጌል ነው። ትርጉሙም ልባችሁ በሕገ ወንጌል ጸንቶ ቢኖር መልካም ነው፥ ማለት ነው።

ሐ. ቅዱስ ጳውሎስ ዕለተ ሞቱ በቀረበ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን አበው ሰብስቦ «ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።» ሐዋ.20፥32። በማለት ጸጋ ያላት ወንጌልን ነው። ጌታ በለጋስነቱ የሠራትን ሕገ ወንጌልን አትካዱ ሲላቸው ነው። ከዚህም የምንማረው እንዲያው በባዶ ሕይወት «በጸጋው ድኛለሁ» ብሎ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን በወንጌል የተጻፈውን ትምህርቱን መቀበል ሕጉን ትዕዛዙን መፈጸም እንደሚገባ ነው። ምክንያቱም ሕገ ወንጌል እንድንባት ዘንድ የተሰጠችን ጸጋ ናትና።

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ንዝህላልነት እና ቸልተኝነት በክርስቲያናዊ ሕይወት

ክርስቲያን ጠንቃቃ ነው። ‹ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጐልምሱ፤ ጠን ክሩ› እያለ ቅዱስ ጳውሎስ የሚመ ክረን በትጋት በብርታት እንመላለስ ዘንድ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። 1ቆሮ.16፥13። ንቁ ክርስቲያን የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ያለንዝህላ ልነትና ያለቸልተኝነት እንደሚገባው ያከናውናል።

ምክንያቱም በሚሠራው ሥራ ሁሉ ከሚያገኘው ጊዜያዊ ጥቅም፤ ከሚለገሰው ምድራዊ ክብር ይልቅ የሰማያዊ አባቱን በረከት ተስፋ ያደርጋልና። በሚያከናውነው ሁሉ ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ያየኛል ይሰማኛልም ብሎ ስለሚያስብ የግዴለሽነትና የቸልተኝነት ጠባያት አይታዩበትም።

በሌላም በኩል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹እኔ ክርስቶስን እንደምመ ስል እናንተም እኔን ምሰሉ› 1ቆሮ. 11፥1። በማለት እንዳስተማረን ሰማያዊ አባታችን ልዑል እግዚአ ብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በሥራው ሁሉ መልካም ነገር እንጂ በሥራው ቸልታ የሌለበት አምላክ ነውና። እኛም ልጆቹ በዚህ ልንመስለው ይገባናል።

ንዝህላልነትና ቸልተኝነት በልዩ ልዩ መንገዶች ሊያጋጥም ይችላል።

1. በማኅበራዊ ሕይወት:- ክርስቲ ያኖች በምንሠማራበት ዕለታዊ ተግባር ሁሉ ታማኞች፤ ጠንቃቆች፤ ሥራ አክባሪዎች፤ የሚገባውን ርዳታ ለሚገባቸው የምንሠጥ፤ ኃላፊነታ ችንን በሚገባ የምንወጣ እንጂ በንዝህላልነት በቸልተኝነት ሥራች ንን እየበደልንና ሕዝቡን እያሳዘንን የምንኖር መሆን እንደሌለብን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል።

እያዩ እንዳላዩ መሆን:- አንድ ሰው ተርቦ፤ ተጠምቶ፤ ታምሞ ወድቆ ወይም ደግሞ አደጋ ደርሶበት እያጣጣረና ርዳታችንን እየፈለገ እኛ ግን እያየንና እየሰማን በቸልታ የምናልፈው ከሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል ‹የድኻውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደ ፍን ሰው እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰ ማለትምም።› ምሳሌ 21፥13።

አባታችን ቅዱስ ያዕቆብም በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢ አት ነው። ይላል ያዕ.4፥17። ዕውቀቱ ተሰጥቶት በሥራው ላይ ተሠማርቶ የተቸገረ ወገኑን የማይረዳ ማንኛውም የዕውቀትና የሙያ ሰው በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ እንደሚጠየቅበት ሊያስብ ይገባዋል በጎ ነገርን ለማድረግ ሲችል አላደ ረገለትምና።

ወዳጁ ታሞ አለያም ደግሞ ተቸግሮ፤ አጥቶና ነጥቶ በቁሙ ሲሞት እያየው በዝምታ አልፎ በሞት ከተወሰደ በኋላ ደረት እየደቃ ሙሾ እያወረደ የሚያልቅስ ዘመድ አዝ ማድም የድኻውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን ዘግቶአልና በጎንም ለማድ ረግ ሲችል በቸልታ አልፎአልና ከኀሊና ወቀሳው በተጨማሪ ቸልተኝ ነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስወ ቅሰዋል።

እግዚአብሔር ሀብት ንብረትን የሚሰጠን ለብቻየ ለማለት፤ ለትዕ ቢትና ለትምክህት ሳይሆን እንደ አብርሃምና ኢዮብ ለድኾች እየራራን እየመጸወትንና ለበጐ ምግባር እያዋ ልን ሰማያዊ ርስት እንድንወርስበት ነው።

እኔም እላችኋለሁ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበ ሏችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ። ሉቃ.16፥9።

በሉቃ.16፥19። ላይ የምናገ ኘው ባለጸጋው ነዌ በልዑል እግዚአብ ሔር ከተጠየቀበት ሥራው አንዱ በደጁ ወድቆ፤ ቁስሎቹን ውሾች እየላሱለት፤ በረሃብ አለንጋ ይገረፍ ለነበረው አልዓዛር ምንም ሳይራ ራለትና እጁን ሳይዘረጋለት በመቅረቱ ነው።

ነዌ ሕንጻ እግዚአብሔር የሆነው የአልዓዛር ሰውነት በቁስል ተወርሶ ሲፈርስ በቸልታ በማለፉ እንደተጠ የቀ ሁሉ በዘመናችን በየሥፍራው ወድቀው የሚታዩ የበዙ አልዓዛሮችን ሕይወት እያዩ በዝምታ ማለፉ የመርዳት ችሎታ ያላቸውን ሁሉ የሚያስጠይቅ ነው።

ኃላፊነትን መዘንጋት:- በዓለማ ችን ላይ በቸልታና በዝንጉነት የሚ ገባንንም ኃላፊነታችንን ባለመወጣ ታችን ብዙ ሕይወትና ንብረት ሲጠፋ ይስተዋላል። አንድ ሰው በአንድ የሥራ መስክ ሲሠማራ ሥራው የሚ ጠይቀውን ኃላፊነት በሚገባ በመረ ዳት ጠንቃቃና ታማኝ ሥራውም ጥራት ያለው እንዲሆን ጥረት ማድ ረግ ይጠበቅበታል። መጽሐፍ ቅዱስ ኃላፊነትን በመዘንጋት ከሚደርሰው አደጋ እንድንጠበቅ በየምዕራፉ ያስተምረናል።

ዘጸ.21፥28-29። በሬው አስቀድሞ ተዋጊ ቢሆን ሰዎችም ለባለቤቱ ቢመሠክሩለት ባይጠብቀ ውም ወንድም ወይም ሴትን ቢገድል በሬው ይወገር፤ ባለቤቱ ደግሞ ይገደል።

ምንም እንኳ አደጋ ያደረሰው በሬው ቢሆን ዋናው ተጠያቂ ሆኖ የቀረበው ግን በሬውን በሚገባ ያልጠበቀው የበሬው ጌታ ነው። ውሻ እያረባ ባለማስከተቡ የተነሣ በበሽታ የተለከፈው ውሻ ብዙ ሰዎችን ለክፎ ቢገድል ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው የውሻው ባለቤት እንጂ ውሻው አይደለም። ኃላፊነቱን በሚ ገባ አልተወጣምና።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዘጸ.21፥33። ሰውም ጉድጓድ ቢከፍት ወይም ጉድጓድ ቢቆፍር ባይከድነውም በሬ ወይንም አህያ ቢወድቅበት የጉድጓዱ ባለቤት ዋጋቸውን ለባለቤቱ ይክፈል።

ዛሬ በታላላቅ ከተሞች ያልተከደኑ ወይንም ያልተደፈኑ የውኃ ጉድጓዶች የቆሻሻ መውረጃዎች፣ ያልተጠገኑ ድልድዮች ወዘተ. በየመንገዱ ይገኛሉ። እነዚህ ቦታዎች ለአዛውንትና ሕፃናት፣ ለዓይነ ሥውራንና በምሽት ለሚጓዙ መንገደኞች ከአካል መጉደል እስከ ሕይወት ማለፍ የሚያስከትሉ መሠናክሎች ናቸው። እነዚህ ሥፍራዎች ለዚህ መሠናክልነት የበቁት ኃላፊነታችንን ባልተወጣን ሰዎች ነው። ይህ ቸልተኝነት በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቀን መሆኑን አጢነነው ይሆን?

ዘዳ.22፥8። አዲስ ቤት በሠራህ ጊዜ ማንም ከርሱ ወድቆ ደሙን በቤትህ ላይ እንዳታመጣ በጣራው ዙሪያ መከታ አድርግለት። በንዝህላልነት የተሠራው ግንብና ድልድይ ለሚያደርሰው አደጋ የእግዚአብሔር ቃል ቸልተኛውን መሐንዲስና አናፂ ተጠያቂ ያደርገዋል። ኃላፊነቱን በሚገባ አልተወጣምና። ተኝቶ፣ ሠክሮ አለያም የቀለጠ ወሬ ይዞ መኪናውን ገደል የሚለቅ የሚያጋጭና የሚገለብጥ ሾፌር ንዝህላልነቱ የሚያደርሰው ጥፋት በሕግ ፊት ብቻ ሳይሆን በሰማያዊው ፍርድም ሊያስጠይቀው እንደሚችል ሊያውቅ ይገባዋል።

የኤሌክትሪክ ባለሙያው በሚለቀው መጠነ አልባ ኃይል፣ የተበላሸ አለያም የማይገባ መድኃኒት የሚሰጥ ሐኪም፣ ቡታጋዙን ሳያጠፉ የሚቀሩ ንዝህላልነታቸው የሚያስከትለው መዘዝ ቀላል አይደለም።

ስለዚህም በዕለት ተዕለት ተግባራችን በምንሠራው ሥራ ከምድራዊ ቅጣት ይልቅ ሰማያዊውን ፍርድ፣ ከጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ ቸልተኝነታችንና ንዝህላልነታችን የሚያደርሰውን ጉዳት አስቀድመን ልናስብ ይገባል።

2. በመንፈሳዊ ሕይወት:- መንፈሳውያን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕገ እግዚአብሔርን፣ ትምህርተ ሃይማኖትን ሳናዛንፍና ሳንበርዝ የመጠበቅ ኃላፊነትና አደራም አለብን። ይህን ኃላፊነት በቸልታ አይተነው ንዝህላልነት ካጠቃን ግን የሚደርሰው ጉዳት በዕለት ተግባር ላይ ከሚደርሰው ይብሳል። በዚያኛው ሰዎችን በሥጋ እንጐዳለን በዚህ ግን በዘላለማዊ ሕይወታቸው።

መንፈሳዊ አባት ልጆቹን ለንስሐ የማይጠራ፣ የማይጐበኛቸው፣ ቀድሶ የማያቆርባቸው የማይመክራቸውና የማይከታተላቸው ከሆነ ‹ግልገሎቼን አሠማራ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ፣ በጐቼን አሠማራ› ዮሐ.21፥15–16። የተባለውን አደራ በቸልተኝነት አልፎታልና እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል።

‹እኔ ኃጢአተኛውን ብእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ አንተም ባታስጠነቅቀው፣ ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል። ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ። ሕዝ.3፥19።

ካህናተ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኞች ናቸው። በጐች የተባሉ ምእመናንን ለምለም ሥፍራ በሆነ በምግባርና በሃይማኖት መስክ የሚያሠማሩ፣ ከተኩላ መናፍቃንና ከከሃድያን መርዝ የሚጠብቁ፣ የቃለ እግዚአብሔር ምግብ አጥተው ጠውልገው በነፍስ ረሃብ እንዳይሞቱ ዘወትር ሊጠብቋቸው ይገባልና። ነገር ግን የተረከቡትን ኃላፊነት ረስተው በጐች በተኩላ ሲነጠቁ በቸልታ ከተመለከቱ እረኝነታቸውንም ቢዘነጉት እግዚአብሔር በነቢዩ በሕዝቅኤል አንደበት እንዲህ ይላል።

እረኛ ስለሌለ እረኞቼም በጐቼን ስላልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ በጐቼን ስላላሠማሩ በጐቼ ንጥቂያ ሆነዋልና በጐቼም ለአራዊት ሁሉ መብል ሆነዋል። ሕዝ.34፥7–10።

መምህራነ ወንጌል ዕውቀቱና ጥበቡ ተሰጥቷቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ሞግዚትነት አድገው፣ የአባቶችን ሃይማኖት ጠንቅቀው እያወቁ ነገር ግን የተሰጣቸውን ሳይሰጡ፣ ሕዝቡንም ሳያስተምሩ ቀርተው በቸልታ ካለፉት ሕዝበ እግዚአብሔርም ያለዕውቀት በኃጢአት አረንቋ ሲዳክር በቸልተኝነት ከተመለከቱት የልዑል እግዚአብሔር ቃል:-

‹ሕዝቤ ዕውቀት በማጣት ጠፍቷልና አንተም ዕውቀትን ጠልተሃልና የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን ረሳለሁ› ይለናል። ሆሴዕ.4፥6።

በተለይ መምህራን ለሚያስተምሩት ትምህርት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያሻቸዋል። ከሕገ እግዚአብሔር፣ ከአበው ትምህርተ ሃይማኖት፣ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው በራሳቸው ሃሳብና ፍላጐት፣ ትርጉምና አመለካከት በመመራት ሕዝበ እግዚአብሔርን እንዳናሳስት ‹ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም› ሲል መድኃኒዓለም ክርስቶስ ያስተምራል።

በርትዕት ሃይማኖታችን በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የክህደትና የኑፋቄ ክርዳድ ሲዘሩ በቸልታና በንዝህላልነት ማለፍ አይገባንም። እውነትን ከሐሰት፣ ብርሃንን ከጨለማ ለይተን ለምእመናን ማሳወቅ ይገባናል እንጂ! መናፍቃንና መስሕታን በቤተክርስቲያን ላይ ሲዘምቱ በአፍ በመጽሐፍ፣ በጾም በጸሎት፣ በሕግ በሥርዓት ከመጋደል ይልቅ ዝም የምንል ከሆነ እንደ ትያጥሮኑ የቤተክርስቲያን አለቃ ያስወቅሰናል፣ ያስፈርድብናልም።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነቢይ ነኝ የምትለውን ባርያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያቺን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ። ራእይ 2፥20። ይህ ወቀሳ ለጴርጋሞኑ ቤተክርስቲያን አለቃም ደርሶታል።

ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንደሴስኑ በእሥራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ካንተ ጋር ስላሉ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ። እንዲሁም የኒቆላውያንን ትምህርት የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ። ራእይ 2፥14።

ወላጆች ለልጆቻችን ታላቅ አደራ አለብን። በጥበብ በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድጉ ዘንድ። ሉቃ.2፥52። አንዳንድ ወላጆች የራሳቸውን ድሎትና ምቾት ብቻ ሲጠብቁና ለየዕለቱ ፋሽን፣ ማብዣና ቅንጦት ሲሯሯጡ ልጆቻቸው ምን አይተው፣ ምን ሰምተው፣ ምን ቀስመውና ምን ዐውቀው እንዳደጉ ሳያስተውሉት ዕድሜያቸው ያልፋል።

ነገር ግን ልጆቻችንን በንዝህላልነት ያለ ሥርዓትና ሥነ ምግባር፣ ያለ ሃይማኖትና ግብረገብነት ካሳደግናቸው ‹ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ› መባላችን አይቀርም። ሕዝ.3፥18።

ልጆችን በመንፈሳዊ ሕይወት፣ በጥበብ መንፈሳዊ፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር ኵትኵተን ካላሳደግናቸው ዘወትር ለቁመታቸውና ለውፍረታቸው፣ ለልብሳቸውና ለጫማቸው ብቻ እየተጨነቅን በአካለ ሥጋ ብቻ ካሳደግናቸው ነፍሳቸውን በሥጋቸው ውስጥ እንደቀበርናት አንዘንጋ እኛና በግአርቢው በምን እንለያያለን? ሁለታችንም የሚጠፋን እያረባን ነው።

ካህኑ ኤሊ:- ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርክ?...እነሆ ለቤትህ ሽማግሌ እንዳይገኝ ክንድህን የአባትህንም ቤት ክንድ የምሠብርበት ዘመን ይመጣል።

1. ሳሙ.2፥27–36። ተብሎ ሊወቀስና በመጨረሻም አሟሟቱ ሊከፋ የቻለው ልጆቹን በሕገ እግዚአብሔር ቀጥቶ ባለማሳደጉና ሲነገረውም በቸልተኝነት በማለፉ ነው።

ስለሆነም ወላጆች ስለልጆቻቸው መንፈሳዊ ዕድገት ጭምር ሊጨነቁ እንጂ በቸልታ እየተመለከቱ አለያም ደግሞ በምንግዴ ካሳደጉዋቸው በልጆቻቸው የሥነ ምግባር ጉድለት መጠየቃቸው ራሳቸውም መሠቃየታቸው አይቀሬ ነገር ነው።

በተጨማሪም ደግሞ እያንዳንዳችን በመንፈሳዊ ሕይወት ንዝህላል ልንሆን አይገባም። አስበን ንስሐ የምንገባ፣ ሥጋወደሙን የምንቀበል፣ ቃለ እግዚአብሔር የምንማር፣ የምንጾምና የምንጸልይ መሆን አለብን። ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑን አንዘንጋ። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ቸልተኞች እና ንዝህላሎች ሆነን ከምሥጢራት ሱታፌ በመራቅ፣ ከቃለ እግዚአብሔር በመለየት ክርስትናችንን የምንዘነጋው ከሆነ በኃጢአት ቤተ መቅደስ ሰውነታችንን እናፈርሰዋለን። የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ለዚህ መሰል ንዝህላሎችና ቸልተኞች:-

‹ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ› ይለናል። 1ቆሮ.3፥17።

ጥንቃቄው ለራሳችን ብቻ አይደለም። የምንሠራው ሥራ ሌሎችን እንዳያሰናክልም ጭምር እንጂ ‹እግዚአብሔር የልቤን ያውቃል፣ ዋናው የልበንጽሕና ነው ወዘተ.› እያልን በንዝህላልነት የምንፈጽማቸው ድርጊቶች ሌሎችን ለኃጢአት ሊጋብዛቸው ሊያሰናክላቸውም ይችላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

‹ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሠናከያ አትሁኑ› ሲል ያስተማረው ይኼንኑ ነው። 1ቆሮ.10፥33።

በሌላ ሥፍራ ደግሞ

መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም ብንበላም ምንም አይጎድለንም:- ብንበላም ምንም አይተርፈንም። ዳሩ ግን ይህ መበታችሁ ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ። አንተ ዕውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ብትቀመጥ አንድ ሰው ቢያይህ፣ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት ሕሊናው አይታነጽበትምን? እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው። እንግዲህ ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ። እንግዲህ መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።

1ቆሮ.8፥8–13። በማለት የመከረን ንዝላልነት ከሚያስከትለው መሠናከልነት እንድንርቅ ነው።

በአጠቃላይ ንዝህላልነትና ቸልተኝነት የሌሎች ኃጢአቶች መግቢያ በሮች፣ አያሌ አደጋ የሚያስከትሉ ጠንቆች፣ በምድርም በሰማይም የሚያስጠይቁ በደሎች መሆናቸውን ተገንዝበን በኑሮአችን ሁሉ ታማኞች፣ ጠንቃቆችና ንቁዎች ልንሆን ይገባናል።

ለዚህም የልዑል እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁንልን። ቅዱሳን በተራዳኢነታቸው አይለዩን። አሜን። ❖



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

ባለፈው ዕትማችን የሥርዓተ ምንኵስናን የት መጣ የገለጽን ሲሆን ዛሬም ካለፈው የሚቀጥለውን ክፍል ይዘን ቀርበናል። አባ ጳውሊ የጀመረውን ሥርዓተ ምንኩስና አጠናክሮ ያስፋፋው አባ እንጦንስ ነው።

በሥርዓተ ምንኵስና ታሪክ ሌላውን ታላቅ ሥፍራ የያዘው ደግሞ የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር የነበረው አባ ጳኩሚስ ነው። (230–346 ዓ.ም)

አባ ጳኩሚስ ግብፅ ውስጥ ኤስና በምትባል መንደር ከአረማውያን ቤተሰቦች በ290 ዓ.ም ተወለደ። በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ለውትድርናም ተመልምሎ አገልግሎት ሰጥቷል። በውትድርናው ዘመን የክርስቲያኖችን ቁራጥነት፣ ደግነትና ርኅራኄ በማየቱ ልቡ ስለተነካ ግዳጁን ፈጽሞ ሲመለስ በ313 ዓ.ም የክርስትናን እምነት ጠንቅቆ በመማር አምኖ ተጠመቀ።

የአባ ጳኩሚስ ልቡና የቅዱስ እንጦንስ ደቀ መዝሙር በነበረው በአባ ጴላሞን ኑሮ ስለተማረከ ወደ በረሃ ወርዶ የብሕትውናን ኑሮና ሥርዓት ሲማር ከቆየ በኋላ በ320 ዓ.ም በዓባይ ወንዝ አጠገብ ታቤኒስ ከተባለው ቦታ የራሱን ገዳም መሠረተ።

በዙሪያው ለተሰበሰቡት መነኰሳትም የአንድነት ኑሮ ሕግ አወጣላቸው። በአባ እንጦንስ ለተጀመረው የማኅበረ መነኰሳት ኑሮ የተጠናከረ ሥርዓት አውጥቶ የበለጠ ከማስፋፋቱም በተጨማሪ ዘጠኝ የወንድና 2 የሴቶች ገዳማት መሥርቶአል።

አባ ጳኩሚስ ያወጣው የመነኰሳት የአኗኗር ሕግ ዋናው ቅጂ ሲጠፋ ወደ ላቲን የተተረጐመው ግን እስከዛሬ ድረስ ይገኛል። ከሕግጋቱ መካከልም:-

- መነኰሳት ጠዋትና ማታ በማኅበር እንዲጸልዩ
- በኀብረት በአንድነት እንዲሠሩ
- ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘውትረው እንዲመለከቱ
- የቃም ጽሕፈት እንዲማሩ፤
- ገቢና ወጪአቸው አንድ ላይ እንዲሆን፤
- በአንድነት እንዲመገቡ፤
- አንድ ዓይነት ልብስ እንዲኖራቸው፤
- ንጽሕ ጠብቀው እንዲኖሩ
- ደግነት፤ ፍቅርና ታዛዥነት እንዲኖራቸው፤ የሚሉት ይገኙበታል።

አንድ ሰው ወደ ገዳማቱ ሲወጣ የሦስት ዓመት አመክሮ ይሰጠውና ጠባዩና ፍላጐቱ ይገመገማል። ከዚያ በኋላም ብርታቱና ጽናቱ ታይቶ ወደ ማኅበረ መነኰሳቱ ይቀላቀላል።

## መላእክት በምድር ላይ

(ክፍል 2)

ከባስልዮስ ዘቂሳርያ

አባ ጳኩሚስ በዚሁ ዓይነት መንገድ ሥርዓት ሠርቶ ሕግ አጽንቶ ገዳማትን ካስፋፋ በኋላ በተወለደ በ56 ዓመቱ በ346 ዓ.ም ዐረፈ።

ይህን ሥርዓተ ምንኵስና በሌላው ዓለም ያስፋፉ ሌሎች አበውም አሉ።

### አትናቴዎስ ሐዋርያዊው

(295–373 ዓ.ም)

ቅዱስ አትናቴዎስ ከታላቁ ርዕሰ ገዳማውያን ከአባ እንጦንስ ዘንድ ሥርዓተ ምንኵስናን ተምሮ ፈጽሟል። የአባ እንጦንስን የሕይወት ታሪክ የጻፈውም እርሱ ነው። አርዮሳውያን በቅዱስ አትናቴዎስ ላይ በግፍ በተነሡበት ጊዜ ወደ ሮም በመሰደድ ከ339–346 ዓ.ም ተቀምጧል። የሮም ክርስቲያኖች አትናቴዎስና ተከታዮቹ የለበሱትን የመነኰሳት ልብስና ቆብ ተመልክተው ተገረሙ። እርሱም በቆየባቸው ሰባት ዓመታት ከአባ እንጦንስ የተማረውን የመነኰሳት ሕግና አኗኗር አስተምሯቸዋል። በሮማ ምድርም ሥርዓተ ምንኩስናን ለማስፋፋት የመጀመሪያው አባት አትናቴዎስ ሐዋርያዊው ነው።

### ቅዱስ ባስልዮስ ታላቁ

(330–379 ዓ.ም)

ባስልዮስ በግብፅ ገዳማት በብሕትውና ከቆየ በኋላ ከ360 ዓ.ም ጀምሮ በታናሿ እስያ (ዛሬ ቱርክ በሚባለው አካባቢ) የምንናን ኑሮ በመመሥረት ዛሬ የግሪክ፣ ሩሲያ፣ ወዘተ. አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉበትን የመነኰሳት ሕግ ያወጣው እርሱ ነው።

### ዮሐንስ ካዝያን

(360–435 ዓ.ም)

ግብፅ ውስጥ በቴብያድና በኒትራን በሚገኙት ገዳማት ለሰባት ዓመታት በብሕትውና ከቆየ በኋላ ወደ ፈረንሳይ በመመለስ በ415 ዓ.ም በፈረንሳይ ማርሴይ አጠገብ ሁለት ገዳማትን መሠረተ። በግብፅ ያጠናውን ሥርዓተ መነኰሳት መሠረት አድርጎ ሁለት መጻሕፍትንም አዘጋጅቷል።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ በአባ ጳውሊ የተጀመረው የምንኵስና ሕይወት በመላው ዓለም ሊስፋፋና ወደሀገራችንም ለመድረስ በቅቷል። የመጀመሪያውን የሴቶች ገዳም የመሠረተችው ደግሞ የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያም ነች።

### ሥርዓተ ምንኵስና በኢትዮጵያ

ሥርዓተ ምንኵስና ወደ ሀገራችን የገባው በኢትዮጵያ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በአባ ጳኩሚስ ዘመን ቢሆንም የብሕትውና ኑሮ ግን በሀገራችን ከዚያም ቀድሞ እንደነበረ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ።

<u>አባ አሞንዮስ</u>:- ሥርዓተ ምንኵስና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት አሞንዮስ የተባሉ ባሕታዊ ብተንቤን ቆላ ደብረ አንሣ በተባለው በረሃ በጾም በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ነበር።

<u>አባ ዮሐኒ</u>:- በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በትግራይ ተንቤን አውራጃ በሀገረ ሰላም ቀበሌ ተወለዱ። በዚያን ዘመን ሥርዓተ ምንኵስና ወደ ኢትዮጵያ ባይገባም አበው በምናኔ በበረሃ ይኖሩ ነበር። የአባ ዮሐኒ ቤተሰቦች ድሆች ስለነበሩ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

አባ አሞንዮስ ወስደው አሳደጉዋቸው። ካደጉ በኋላም ከአባ አሞንዮስ ተለይተው ወደ በረሃ ለብቻቸው በመውረድ በተጋድሎ ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ30 ዓመታቸው ኅዳር 5 ቀን እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን በመላእክት እጅ እንደወሰዳቸው ገድለ አባ ዮሐኒ ይገልጣል።

ሥርዓተ ምንኵስና በኢትዮጵያ ለመስፋፋት የበቃው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው።

1. ከውጭ ወደ ሀገራችን በገቡ ቅዱሳን

2. በኢትዮጵያውያን ቅዱሳን

1. ወደ ሀገራችን የገቡ ቅዱሳን:- ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከታናሿ እስያና ከሮማ ግዛት ወደ ሀገራችን በልዩ ልዩ ምክንያት ገብተው ሥርዓተ ምንኵስናን ያስፋፉ ገዳማትን የገደሙ አበው አያሌ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. አባ ሊባኖስ:- በቁስጥንጥንያ አጠገብ ሩም በተባለች ቀበሌ ተወለደ። በልጅነቱ በዲቁና ሲያገለግል ቆይቶ ወደ ግብፅ በመምጣት በአባ ጳኩሚስ እጅ ሥርዓተ ምንኵስና ተፈጸመለት። ወደ እስክንድርያ በመጓዝም እስከ ቁምስና ማዕረግ የደረሰ አባት ነው።

አባ ጳኩሚስ የእጅ መስቀሉንና መጽሐፈ መነኰሳትን ሰጥቶ ወደ ኢትዮጵያ ላከው። እርሱም በ486 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት 80 ዋሻዎች አንፆ ሥርዓተ ምንኵስናን አስፋፍቶ በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ጥር 3 ቀን ዐርፏል።

2. ተሰዐቱ ቅዱሳን

በኬልቄዶን ጉባዔ ያልተስማሙትን አባቶች ሮማውያን በግፍ በሚያሳድዱበት ዘመን ከሮም፣ ከታናሿ እስያና ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ግብፅ በመውረድ በዚያም ሥርዓተ ምንኵስናን ፈጽመው ተምረው በአንድነት በ480 ዓ.ም ወደኢትዮጵያ በመምጣት ሥርዓተ ምንኵስናን የበለጠ ያስፋፉ አበው ናቸው። ገዳማቱ እስከዛሬ ድረስ የሚገኙ ሲሆን፤

| ስም | ገዳም | የዕረፍት ቀን | ሀገራቸው |
|---|---|---|---|
| አባ አሌፍ | ብኁዛን (አህስአ) | መጋቢት 11 | ቂሣርያ |
| አባ አረጋዊ | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት 14 | ሮም |
| አባ አፍጼ | የሃ/ዩሐ | ግንቦት 12 | እስያ |
| አባ ሊቃኖስ | ደብረ ቆናጽል | ኅዳር 21 | ቁስጥንጥንያ |
| አባ ገሪማ | መዱራ | ሰኔ 29 | ሮም |
| አባ ጉባ | ገርዓልታ | ግንቦት 29 | ኪልቂያ |
| አባ ይምዓታ | ገርርዓልታ | ጥቅምት 23 | ቆሲያ |
| አባ ጰንጠሌዎን | አኵስም (አጠገብ) | ጥቅምት 6 | ሮም |
| አባ ጽሕማ | ጼዴንያ | ጥር 16 | አንጾኪያ |

## አባ ዮሐንስ (ዘጉንድ ተ/ሃይማኖት)

የትውልድ ሀገራቸው ፍልስጥኤም ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በ1100 ዓ.ም ነው። አባ ዮሐንስ በተለይ ከአፋር ክልል ደብረ አዘሎ፣ ደብረ ደንኖ፣ ደብረ ፀገ፣ ደብረ ገሮ፣ ደብረ አሳራ በተባሉ ሥፍራዎች ሥርዓተ ምንኵስናን አስፋፍተዋል። በመጨረሻም በለሳ በረሃ ወርደው ጉንድ ገዳምን በመመሥረት ሐምሌ 29 ቀን በተወለዱ በ500 ዓመታቸው በ1500 ዓ.ም ዐርፈዋል።

3. ጻድቃን

ተሰዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት በግልና በኅብረት እየሆኑ አያሌ መነኰሳት ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ገብተው ነበር። እነዚህም ቅዱሳን ‹ጻድቃን› እየተባሉ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተገለጡ ሲሆን በቅርቡ መጽሐፈ ገድላቸው እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ስለነርሱ የሚታወቀው እጅግ ጥቂት ነበር። እነርሱም በኤርትራ ቆላማው ሥፍራ ሥርዓተ ምንኵስናን ያስፋፉ መሆናቸው ታውቋል።

4. አርባሐራ:- አቡነ ሐራ የተባሉት ቅዱስ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በአኵስም ከቆዩ በኋላ አያሌ መጻሕፍት እና ንዋያተ ቅድሳት ይዘው ወደ መንዝ ማማ ምድር በመምጣት በዋሻ ውስጥ ተቀመጡ። የዮዲት ዘመን ካለፈ በኋላ ደግሞ 40 ቅዱሳን ከግብፅ ከገዳመ አስቄጥስ መጥተው ከአቡነ ሐራ ጋር 4 ሰዓት የሚያስኬድ ዋሻ ፈልፍለው ማኅበረ መነኰሳት አቋመው መኖር ጀመሩ።

ከነዚህም መካከል 20ዎቹ ዞረው ሲያስተምሩ 20ዎቹ ደግሞ የተማባር ቤቱን ሥራ ያከናወኑ ነበር።

በአካባቢውም ትምህርተ ወንጌልንና ሥርዓተ ምንኵስናን ካስፋፉ በኋላ አስቀድመው 40ው ቅዱሳን በኋላም አቡነ ሐራ በተወለዱ በ220 ዓመታቸው በ1100 ዓ/ም ዐረፉ። የእርሳቸውንም ፈለግ አባ ፍሬሠናይ የተባሉ አባት ተከተሉዋቸው። ይህም ሥፍራ ዛሬ አርባራ መድኃኔዓለም ገዳም በመባል ይታወቃል።

በአሁኑ ወቅት ይህ ቦታ በተለያየ አፀፍ የተከፈኑ እና የተገነዙበትም ማሠሪያ ክር በእጃቸውና በእግራቸው ጣት ላይ የሚታይ ብዙ አፅሞች ይገኙበታል። ምንም እንኳን ዋሻው በአፅም የተሞላ ቢሆንም ከአካባቢው የሚወጣው መዓዛ ግን ከሙታን መንደር የሚገኝ መጥፎ ሽታ ሳይሆን ‹አልባብ አልባብ› የሚል መልካም መዓዛ ነው።

የአካባቢው አረጋውያን እንደሚናገሩት ከሆነ ከኢጣሊያ ፋሺስት ወረራ በፊት ዘወትር የማኅሌት፥ የከበሮና የዕልልታ ድምፅ ይሰማበት ነበረ። በተጨማሪም እጅግ ግዙፍ የሆነ ነጭ አሞራ እየበረረ ወደ ዋሻው ሲገባ ማየት የዘወትር ክስተት ነበረ። ከዚያ ወዲህ ግን ይህ ነገር ብዙም አይታይም።

ቦታውን ከአካባቢው ምእመናን ጋር የሚያገናኘው ሌላው ነገር ደግሞ መሬት ሰብል እንዳትሰጥ ሰብል አጥፊ ተባይ ሲነሣ፣ እንስሳቱ ወተት መስጠታቸውን ሲቀንሱ ገበሬዎቹ አፅሞቹ ካረፉበት ቦታ አፈሩን በመዝገን በማሳቸው ላይ ይበትናሉ እንስሳቱንም ያሻሹበታል። እንደ እምነታቸውም እንደሚያደርግላቸው በየዓመቱ ጥር 13 ቀን የሚገባው የእንስሳትና የሰብል ውጤት ምሥክር ነው። ከዋሻው የሚወጣው መልካም መዓዛም አሁንም ያልተቀየረ መሆኑን ሄዶ የሚመለከት ምሥክር ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## አባ ኖብ

ትውልዳቸው በሶሪያ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከአቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ ጋር ተገናኙ የኢትዮጵያ ውያንን ቋንቋና ባሕል ካጠኑ በኋላ በትግራይ ተንቤን ፀፀራ ወረዳ ከሚገኘው ዋሻ ላይ ቤተክርስቲያን ተክለው ገዳም መሠረቱ። ከዚያም ቀጥለው በመላ ኢትዮጵያ በመዘዋወር ገዳማትን መሥርተው 1100 ዓ.ም ኅዳር 8 ቀን ዐረፉ።

## አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ትውልዳቸው በግብፅ ሲሆን ገና በሕፃንነታቸው በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በ1100 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሥርዓተ ምንኩስናን ያስፋፉ አባት ናቸው። እግዚአብሔር በሰጣቸው የ562 ዓመት ዕድሜ አያሌ ገዳማትን የገደሙ ሲሆን በተለይም የዝቋላና የምድረ ከብድ ገዳማት እስከዛሬ የፀኑ ናቸው።

በኢትዮጵያ የምንኩስናና የገዳማት ታሪክ ውስጥ ከ3ኛው– 12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ በአብዛኛው ከውጭ በመጡ አበው ሥርዓተ ምንኩስና የተስፋፋበት ሲሆን ከ12ኛው–15ኛው ያለው ደግሞ ከመላ ኢትዮጵያ በተነሡ አበው ቅዱሳን ሥርዓተ ምንኩስናና የገዳማት ትክል ከሰሜን ወደ ምዕራብ፣ ምሥራቅና ደቡብ የተስፋፋበት ወቅት ነው። ✤

---

### ምንጭ


1. ትንሣኤ ቁ.99/1978
2. ገድለ አባ ሊባኖስ
3. ገድለ አባ ዮሐንስ
4. ዜና መንዝ
5. የአንኮበር መሳፍንት የታሪክ መጽሐፍ
6. ትንሣኤ ቁ.11/79
7. ትንሣኤ ቁ.22/80
8. Conti Rossini, Storia PL.XLIV
9. ሉሌ መላኩ፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ ኢ.አ 1986
10. አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ
11. አባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ


# መጽሐፍ ቅዱስ

ትርጉም:- መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በጥሬ ትርጉሙ የተቀደሰ መጽሐፍ ማለት ነው። ቅዱስ የሚለው ቃል ‹በዕብራይስጥ ቅዳሺ በሱርስት ቃዲሽ በዐረብኛና በግዕዝ ቅዱስ ይባላል። ትርጉሙም ‹የተለየ› ማለት ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስም ‹የተለየ መጽሐፍ› ማለት ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርገው

1. የሚያስተምረው ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ:- በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ እንኳን ከ2000 ጊዜ በላይ ‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል› የሚል ቃል ተጽፎአል። ይህም መጽሐፍ ቅዱስን ያጻፈው እግዚአብሔር ባለቤቱም እርሱ መሆኑን ይመሰክርልናል።

2. የጻፉት ሰዎች ቅዱሳን መሆናቸው:- መጽሐፍ ቅዱስ በታወቁ ፈላስፎች፣ ጠቢባን ሳይንቲስቶች፣ አልያም ደግሞ በደራሲያን የተቀመረ አይደለም ‹በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ› 2ጴጥ.1፥21። ስለዚህም የሚተረጉመው በቅዱሳን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በገለጠላቸው አበው እንጂ በጥበብ ብዛት አይደለም።

3. ሰሚዎቹን፣ አንባብያኑንና ተከታዮቹን ወደ ቅድስና የሚመራና የሚቀድስ መሆኑ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የሚሰሙት የሚያነቡትና የሚመሩበት ቅድስናን ያገኛሉ ምክንያቱም:-

ሀ. የመንፈስ ምግብ ነው። ‹ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ› በማለት ጌታችን እንዳስተማረን መጽሐፍ ቅዱስ ለነፍስ ምግቧ ነው። ሰው እንጀራን ብቻ ተመግቦ የእግዚአብሔርን ቃል ከተራበ የበለጠው ሕይወቱ በረሃብ እየማቀቀ መሆኑን ሊረዳው ይገባል። ማቴ.4፥4። ኤር.15፥16።

ለ. የመንገዳችን መብራት ነው:- ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው› መዝ.118፥105። እንዳለ ቅዱስ ዳዊት መጽሐፍ ቅዱስን የማይማርና የማያነብ ሰው የኃጢአትን ጨለማ ከጽድቅ ብርሃን ለመለየት ያዳግተዋል። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያመራውን መንገድ ለመለየት አያስችለውም።

በተጨማሪም ሕይወቱን በአግባቡ ለመምራት ቅዱስ መጽሐፍ ያስፈልገዋል።

ሐ. ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ ነው:- የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም፣ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው። ዕብራ.4፥12። ስለዚህም እውነትን ከውሸት፣ ደግነትን ከክፋት ይለያል፤ የችግራችንን ሠንሠለት ይበጣጥሳል። የእግዚአብሔርን ቃል የሚማር ሰው ለችግሩ ሁሉ መፍትሔ ያገኛል። ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ ነውና ሰባኪውንም ተሰባኪውንም ይመረምራል ይፈውሳልም፤ ሥጋውያንና መንፈሳውያን ጠላቶችን ድል እንነሣበታለን። ያለ እግዚአብሔር ቃል ኃጢአትንና ጠላትን ድል መንሣት አይቻልም።

መ. ያነፃል:- እናንተ ግን ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ። ዮሐ.13፥3። የሰው ልጅ በጥበቡ በዘዴውና በቴክኒኩ ራሱን ከበደልና ከኃጢአት፣ ከሱስና ከጥገኝነት ሊያነፃ አይቻለውም። ይህንን ኃይል የምናገኘው በእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት ነው።

ሠ. ያለመልማል:- ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋንም በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል። መዝ.1፥3። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነብ፣ የሚማርና የሚያስበውም ፍሬ ሃይማኖት ያፈራል። ጌታው በጉበኘውም ጊዜ ቅጠል ብቻ ሆኖ አያፍርም። ዘወትር በቃለ እግዚአብሔር የማይጐበኝ ሰው ግን ይደርቃል፤ መድረቁንም አያውቀውም።

4. መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዘመን በአንድ ቦታ በአንድ ሰው ተጽፎ ያለቀ አይደለም። የሄኖክ መጽሐፍ ከተጻፈበት ከ4000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ በ90 ዓ.ም የዮሐንስ ራእይ እስከተጻፈበት ዘመን ድረስ ወደ 4000 ዓመታት ዐልፈዋል። ጸሐፊዎቹም ከ40 በላይ ሲሆኑ መጻሕፍቱም የተጻፉት:-

በሲና ምድረ በዳ:- የአሪት መጻሕፍት

በምድረ ከነዓን:- የመጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጽሐፈ ነገሥታት፣ ወዘተ.

በምርኮ:- (ፋርስና ባቢሎን) መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዳንኤል፣ ወዘተ.

በታናሿ እስያ:- ለምሳሌ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት፣ የዮሐንስ መልእክታት፣ የዮሐንስ ራእይ እንዲሁም በልዩ ልዩ ሥፍራዎች ተጽፈዋል። ነገር ግን የሁሉም ሃሳብ፣ ዓላማ፣ እምነትና ትምህርት አንድና የማይጋጭ የማይፋለስም መሆኑ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፋቸውን ያረጋግጣል።

በሌሎችም ይህን በመሰሉ ምክንያቶች ቅዱስ ተብሏል።

### መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም መድረክ

ሀ. ረዥም ዕድሜ ያለው መጽሐፍ ነው

ለ. መጀመሪያ የታተመ መጽሐፍ ነው



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሐ. ብዙ ሚሊዮን ጥራዝ ታትሞ የተሠራጨለት መጽሐፍ ነው

መ. ወደ ብዙ ቋንቋ የተተረጐመ መጽሐፍ ነው

በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች በብዛት ተተርጉመዋል ብለው የሚገምቷቸው የሼክስፒር ሥራዎች እንኳን የተተረጐሙት በ40 ቋንቋዎች ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመሆኑ ለመረዳትም ቅዱስ ፈቃዱና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያሻል። ስለዚህም እንደማንኛውም መጽሐፍ ከጠርዝ–ጠርዝ የሚሸመድዱት፣ በተፈለገ ጊዜ እንደዋዛ አንሥተው የሚያነቡት ነገር ሳይሆን አስቀድሞ እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅ ሊነበብ የሚገባው መጽሐፍ ነው። ለምሳሌ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በሥርዓተ ቅዳሴ ካህኑ ዲያቆኑና ሕዝቡ ከጸለዩ በኋላ በክብር ወንጌሉን ያነባሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚና መሪ ያሻዋል። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወንጌላዊው ፊልጶስን ባገኘው ጊዜ ‹የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል› በማለት የመለሰለት መጽሐፍ ቅዱስን የሚገልጥ እና የሚያስተምር መሪ ስለሚያስፈልግ ነው። የሐዋ.8፥30። መጽሐፍ ቅዱስን በሁለት መንገድ መማርና መረዳት ይቻላል።

1. ከመምህራን በአካል በመማር:- የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቀው፣ በቋንቋዋ ከሚናገሩ ድምጿን ከሚያሰሙ፣ መምህራን ቀርቦ በመማር መረዳት ይቻላል።

2. በቅዱሳት መጻሕፍት:- ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ስለመጽሐፍ ቅዱስ የጻፉዋቸው ድርሳናቶቻቸውን በመመርመር የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል መረዳት ይቻላል።

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የተጻፈበት ዘመን፣ ባሕል፣ የተጻፈበት ቦታ ሁኔታ እንደ ተጻፈላቸው ሕዝቦች ታሪክ መሠረት በማድረግ ነው። ስለዚህ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ለማወቅ በቅድሚያ

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ሕዝብ ባሕል ማወቅ ያሻል:- የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል በተጻፈላቸውና በጻፉት ሰዎች ባሕል ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ በምንማርበትና በምናስትምርበት ጊዜ ይህንን ልናጤን ይገባል።

ለምሳሌ:- ወንድም የሚለው ቃል በእሥራኤል ባሕል

- ከአንድ እናትና አባት ለሚወለዱ፣
- ለዘመዳሞች፣
- በእምነት አንድ ለሆኑ፣

ለሀገር ልጆች፣ ወዘተ. ሁሉ ይሰጣል። በምዕራባውያን ባሕል ግን የእናትና አባት ልጅ ብቻ ወንድም ይባላል። ምዕራባውያኑ የጌታ ወንድሞች የሚለውን ከላይ ባለው የዕብራውያን ባሕል ከመተርጐም ይልቅ በራሳቸው ባሕል በመተርጐማቸው የእናቱና የአባቱ ልጆች የሥጋ ወንድሞቹ ናቸው በማለት ያለዕውቀት በመተርጐምና በማስተማር በስሕተት መንገድ ተጉዘዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዮሐ.10 ላይ የተጻፈውን የአንቀጸ አባግዕ (የበጐች መግቢያ) ትምህርት ስናነብ እረኛው ከፊት በጐቹ ከኋላ ሆነው ድምፁን በመስማት ሲከተሉት እንመለከታለን። ይህ ግን ለምሳሌ በእኛ ባሕል ሊተረጐም አይችልም። በሀገራችን በግ ከፊት እረኛ ከኋላ ነውና።

2. የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ማወቅ:- መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት ታሪክ አለው።

ሀ. የራሱ ታሪክ:- መጻፍ ከተጀመረበት እስከ ተጠናቀቀበት ብሎም ተሰባስቦ በአንድ ላይ እስከተጠረዘበት በልዩ ልዩ ቋንቋም ተተርጉሞ ለኛ እስከደረሰበት ድረስ ያለው ታሪክ።

ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ ውጭ የተተረጐመው ወደ ዕርዕ (የጥንት ግሪክ ቋንቋ) ሲሆን ይኸውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው። በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት በፊት ባጥሊሞስ በተባለው የግብፅ ንጉሥ ሰባ የዕብራውያን ሊቃውንት በእስክንድርያ ከተማ ተቀምጠው ወደ ፅርዕ ቋንቋ መልሰውታል። ይህም የሰብዓ ሊቃናት (ሰፕቱአግንት) ትርጉም በመባል ይጠራል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እስከ 2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ተነጣጥለው ይገኙ ነበር። በዚህ ዘመን የተነሡት ግኖስቲኮች የተሰኙት መናፍቃን በሐዋርያት ስም የራሳቸውን መጻሕፍት እየጻፉ ስላስቸገሩ ቤተክርስቲያን በቀኖና የመጽሐፍቱን ቁጥር ወስና አስቀምጣለች።

በ1228 ዓ.ም መጻሕፍቱን በምዕራፍ፣ በ1551 ዓ.ም ደግሞ ምዕራፎቹን በቁጥር መከፋፈል ተጀመረ።

ለ. የተጻፈላቸው ሕዝቦች ታሪክ:- መጽሐፍ ቅዱስ የመካከለኛው ምሥራቅ የታናሽ እስያንና የአውሮፓን ታሪክ ይዞአል። በተጻፈበት ዘመን የነበረውን ሕዝብ ሁኔታ ችግር፣ ጠባይ፣ ሥርዓት፣ ዓይነት ለይቶ ለማወቅ ታሪኩን ማጥናት የግድ ነው።

ለምሳሌ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጠቀሱት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ታሪክ በሚገባ ካልታወቀ ለመረዳት ያዳግታል።

3. መልክዐ ምድር:- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፋርስ እስከ ስፓኝ ያለው ምድር ተካትቷል። በመሆኑም የጌታን መዋዕለ ትምህርት፣ የሐዋርያትን ጉዞ ለማወቅ ይህንን ጥንታዊ መልክዐ ምድር ማወቅ ወሳኝ ነው። ለምሳሌ ጥንት ኤፌሶን በኤጅያን ባሕር ዳር የምትገኝ የወደብ ከተማ ነበረች። አሁን ግን የባሕሩ አሸዋ የጥንቱን ከተማ ሸፍኖታል። ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የላከው ዛሬ ብአሸዋ በተሸፈነችው ከተማ ይኖሩ ለነበሩት ሕዝቦች በመሆኑ የከተማዋን ጥንታዊ መልክዐ ምድር ለይቶ ማወቁ መልእክቱን ለመረዳት ይጠቅማል።

መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያናችን

አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችን በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን በባሕል ብቻ የምትመራ ይመስላቸዋል። እውነቱ ግን የተገላቢጦሽ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተክርስቲያናችን:-

- የእምነቷ መሠረት ነው:- የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት (ዶግማ) ዋና መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነውና።
- የሥርዓቷ ምንጭ ነው:- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
- ለምሳሌ የቤተ መቅደስ አሠራር፣ ልብሰ ተክህኖ መሠረቱ የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ሲሆን የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር አፈጻፀም ሥርዓት ደግሞ ሐዲስ ኪዳን ነው። ዘፍ.9፥29፣ 28፥40–42፣ ማቴ.26፥26፣ 1ቆሮ.11፥27።
- የባሕሏ ምንጭ ነው:- ለምሳሌ ሕዝበ ክርስቲያኑ ነጭ ልብስ የሚለብሰው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጐ ነው ማለት ይቻላል። ማቴ.28፥3፣ የሐዋ.1፥10።
- የጸሎቷና የዝማሬዋ ምንጭ ነው:- የቤተ ክርስቲያን ጸሎት (ውዳሴያቱ፣ ቅዳሴያቱ) መዝሙራቱ (ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ መዋሥዕት፣ ዝማሬ) የመነጨው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።
- በቤተ ክርስቲያን ጸሎት መጽሐፍ ቅዱስ የማይነበብበት ክፍል የለም:- በቅዳሴ፣ በሰዓታት፣ ወዘተ. በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማውጫ (ግጻዌ) መጽሐፍ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ይነበባል።
- ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የተቀበለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት 900 ዓመት በመሆኑ ስታነበው ስትተረጉመው ስትመራበት ኖራለች።
- መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ብቻ ሳይሆን በመጸለይ፣ በመሳለም በመዳሰስ ፈውስ እናገኝበታለን። የልዑል እግዚአብሔር ቃል ኃይል አለውና።
- ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን በቃል፣ በትርኢት፣ በምግባር ታስተምረዋለች። ሥርዓቷ፣ አሠራርዋ፣ አልባሳትዋ ሁሉ ትምህርተ ወንጌል ይዘዋልና።

እግዚአብሔር የቅዱሳት መጽሐፍትን ምሥጢር ይግለጥልን። ❖ አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

ለሰባኪያን መቆሚያ ከፍ ያለ ቦታና አትሮንስ በቤተ ክርስቲያን መጠቀም የተጀመረው ከ386 ዓ.ም አካባቢ ባለው በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚያስተምርበት ጊዜ ሕዝቡ በብዛት ይሰበሰብ ነበር። ነገር ግን የዮሐንስ ቁመት አጭር ነበርና ከፍ ብሎ ለሕዝቡ እንዲታይና ድምፁም እንዲሰማ መቆሚያ ሥፍራና የመጻሕፍት ማንበቢያ አትሮንስ ተሠራለት። ቤተ ክርስቲያንም ከዚያ ዘመን ጀምሮ አትሮንስን ትጠቀምበት ጀመር።

ኑዛዜ በቤተ ክርስቲያናችን የተጀመረው ሕጋዊና ድንግል ከሆነው የእስክንድርያ 12ኛ ፓትርያርክ ከአባታችን ከቅዱስ ድሜጥሮስ ወዲህ ነው። አባታችንን በከንቱ አምተውት የነበሩት ምእመናን በእግዚአብሔር ፈቃድ ክብሩ በተገለጠላቸው ጊዜ «አባታችን ይቅር በለን» ብለው ንስሐ ሲገቡ «ይፍታሕ ይኅድግ» ብሎ ናዝዟቸዋል። ኑዛዜም ያን ጊዜ ተጀምሯል።

አንገት ላይ ማተብ ማሠር የተጀመረው በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሶርያ ያስተምር በነበረው በአባታችን በያዕቆብ ዘእልበረዲ ነው። አባታችን እያስተማረ በሚያጠምቅበት ጊዜ የተጠመቁትና ያልተጠመቁት እየተቀላቀሉ ቢያስቸግሩት፤ ለመለየት ይቻል ዘንድ ለተጠመቁት ምእመናን ማተብ ያስርላቸው ነበር። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ማተብ ለተጠመቁ ክርስቲያኖች መለያ ምልክት ሆነ።

መ/ር ቴዎድሮስ በየነ
ኢሉባቦር ቡሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ሰ/ት/ቤት

## አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

ርዕስ – ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

አዘጋጅ – የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል

ገጽ – 148

ዋጋ – 9.00 ብር ብቻ

ስለ ትውፊተ ቤተክርስቲያን፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሙሉ ጥናት እና በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለተነሡ ቅዱሳን ታሪክና ተጋድሏቸው ጥልቅ ትምህርት የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

## ማስተካከያ

ማኅበረ ቅዱሳን ለአዲስ ዓመት ባዘጋጀው የመልካም ምኞት መግለጫ ፖስት ካርድ ላይ ‹ጾመ ነቢያት ኅዳር 16 ቀን ይገባል› የተባለው ኅዳር 15 ቀን ተብሎ ይስተካከል ዘንድ በትህትና እናስታውቃለን።

## ምክክር

ባለፈው ነሐሴ 1987 ዓ.ም ለሥራ ጉዳይ ወደ ገጠር ወጥቼ ነበር። ከሥራዬ በኋላ ለመጸለይና መርሐ ግብር ካለም ቃለ እግዚአብሔር ለመማር ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራሁ። ነገር ግን እንኳን መምህር ኑሮ ሊያስተምር ይቅርና ጉልላት ባይኖረው ኑሮ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ከሩቅ ተመልክቶ ለመለየት ያስቸግራል።

ግድግዳው ፈርሷል። አጥሩ ምልክቱን ብቻ ትቶ አልፏል። በሩ ግድግዳውን ለቅቆ ለብቻው ቆሟል። የእግዚአብሔር ቤት እንዲህ ሆኖ ሲታይ የነቢዩ የሐጌን ዘመን ያስታውሰኛል። እኛስ እንዴት እንወቀስ ይሆን? በአካባቢው ያገኘኋቸውን አረጋዊ ካህን ስለሁኔታው ስጠይቃቸው የሚቀደስበት ዘቢብና መገበርያ፣ ዕጣንና ጧፍ ብሎም የካህናት አልባሳት የሉትም። በዚህም የተነሣ ካህናቱ አገር ለቅቀው ስለሄዱ ከተቀደሰበት ወደ አምስት ዓመታት አልፎታል።

በታላላቅ ከተሞች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ገንዘባቸው በባንክ ተቀምጦ ከሚኖር ማዕከላዊ በሆነ መንገድ በገጠር ለሚገኙትም የሚዳረስበት መንገድ ቢፈለግ፤ ካህናትም በተመጣጠነና በደረጃ ( ) የደመወዝ አከፋፈል ወጥና ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ቢመደቡ፤ ምእመናንም የሚገባንን አሥራት በኩራት በጊዜው ብናወጣ ኖሮ ነገ የማናገኛቸው አብያተ ክርስቲያናት በተንከባካቢ እጦት ባልፈረሱም ነበር።

እናም ሁላችንም ብናስብበት መልካም ነው እላለሁ።

መስፍን ይትባረክ
ከየካ ደ/ሣ/ቅ/ሚካኤል ቤተክርስቲያን።

## ይህች ባቄላ

ለሥራ ጉዳይ ወደ ወለጋ እንፍሌ ወረዳ ተጉገፎ ነበር። ቤተክርስቲያንን ሰላም ለኪ ልል ስሄድ አሳዛኝ ነገር ነበር የጠበቀኝ። የአንድ ደብር ሰ/ት/ቤት በቁጥር ወደ 54 (ሃምሳ አራት) የሚጠጉ ሰ/ት/ቤቶችን ጋብዞ «በመንፈስ እንድ ትሞሉ፤ በልሳን እንድትናገሩ፤ ተአምራትን እንድትሠሩ» እያለ አንዱ ጉልማሳ ቀኝ እጁን እየጫነባቸው ቤተ ክርስቲያን መሆኑ እስኪዘነጋ ድረስ ይጯጯሁሉ። በአካባቢው «ሀይ» የሚል አባት የለም እንዴ? ወጣቱ በኑፋቄ መንገድ ሲነጉድ ምነው በዝምታ ታየ! ይህች ባቄላ...

ክፍለ ጻድቅ ነኝ– ከአሦሳ

## አይዞህ ትለኛለች

ሆዴን ሆድ ሲብሰው
አልችል ሲል አንጀቱ
ስጨነቅ ሲጠበኝ ሲርድ ሰውነቱ
ባዶነት ሲሰማኝ ጠፍቶኝ እኔነቱ
ስሟን ሳነሣሣ ስላት ያንድዬ እናት
እጅግ ተጨንቄ በዕንባ ስማጸናት
ኀለቅስ ስተክዝ ስወድቅ ከደጇ
አይዞህ ትለኛለች እኔን እንደዋዳጇ
የማደርገው ጠፍቶኝ ባሳብ ስብከነከን
ሳነሣና ስጥል ስባዝን ስኳትን
ዕምባዩ ጠብ እስኪል እሷን ስማፀናት
አይዞህ ትለኛለች የአማኑኤል እናት።

ዘላለም ማሞ – ምዕ/ወለጋ ዞን –ደምቢ

## የመጽሔታችን ደንበኛ ቢሆኑ

አንዲትም እትም አታልፎዎትም።

| | አዲስ አበባ | ክ/ሀገር | ከሀገር ውጭ |
|---|---|---|---|
| የ6 መጽሔት | 18.70 | 19.20 | 12 ዶላር |
| የ12 መጽሔት | 37.80 | 38.40 | 24 ዶላር |

ለወ/ት ዓይናለም ታዬ ደመቀ

4 ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ

የሒሳብ ቁጥር 79808 – አዲስ አበባ

አድራሻዎንና የከፈሉበትን በፖ.ሣ.ቁ. 80078 ይላኩልን።


ዋጋው 3.00 ብር

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡